# ትግላችን - ዜና

ዓለም-አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራት ሕብረት



በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethiopian Students' Union in Europe
Editorial Board
P.O.Box 3198, 10364 Stockholm,3
SWEDEN


# የአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 19ኛ ጠቅላላ ጉባዔ የፖለቲካ ውሳኔ


ነሐሴ 1971 ቅጽ 7- ልዩ እትም

## የአኢተማ 19ኛ ጠቅላላ ጉባዔ ሪፖር

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 19ኛ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ በበርሊን ከተማ /ምዕራብ ጀርመን/ ከ11–8–79 እስከ 17–8–79 እጅግ ከፍተኛ የትግል መንፈስ በተሞላበት አኳኋን ተካሂዷል።

19ኛው ጉባዔአችን የተካሄደው በኢትዮጵያችን የፀረ–አብዮት ሃይሎች በየሉበትና አብዮቱ በተከላካይነት በሚገኝበት ወቅት ነበር። በየካቲት 66 የተቀጣጠለው አብዮታዊ እንቅስቃሴ ከሞላ ጎደል ተቀልብሶ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ለረሃብና መራራ ትግል በሚዘጋጅበት ወቅት የተካሄደው ጉባዔአችን ያንፀባርቅ የነበረው የትግል መንፈስ ሰፊው የማህበራችን አባላት ቆርጠውና ታጥቀው ለተነሱለት የነፃነት ትግል ዛሬም ባለማወላወል መቆማቸውን ያመለክት ነበር።

ጉባኤአችን እንዳይካሄድ ከየአቅጣጫው የተጠመደው ሤራ ብዙ ነበር። የደርግ ኤንባሲዎች ፓስፖርት አናድስም በለው ጓዶቻችን ካሉበት እንዳይንቀሳቀሱ ለማድረግ ሞከሩ። "እገርህ ስትመለስ ከተገኘህ ታገኛታለህ" በለው አስፈራሩ። ከምሥራቅ አውሮፓ መንግሥታት ጋር በመስማማት አያሌ የማህበራችን አባላት በቁም እስር እንዲያዙ ተደረገ። ምድር ቢንቀጠቀጥ ሰማይ ቢገለበጥ፣ የማህበራችንን ጉባዔ ግን እንደተለመደው ከማካሄዱ አላገደንም። በበኩላችን ለወዳጅም ሆነ ለጠላት ከዚህ ተነስተን የምናስተላልፈው መልእክት ግልፅ ነው። የታሪክ ትቢያ በአኢተማ ላይ ተረባረበና አኢተማ አዩዋ ከምም ይጠናከራል እንጂ አንሳቸቀለን። ደርግና ግብረአበሮቹ በዚህ ድርጊታቸው አፍረት ተከናነቡ፣ ሰፊው የማህበራችን አባላት በኩራትና ምንጊዜም እያደገ በሚሄደው ታታሪነታቸው መራራውን ትግል ግቡ ለማድረስ መታጠቃቸውን አሳይተዋል።

በ11–8–79 የአኢተማ 19ኛ አመታዊ ጉባዔ ተከፈተ። በምሥራቅ አውሮፓ እንዳይወጡ የተከለከሉ አባሎቻችን በጉባዔው ስላልተገኙ ቁጥራችን ከበፊቱ አነስ ይል ነበር። ሆኖም እያንዳንዱ ተካፋይ የጓዶቹን አለመኖር በእጥፍ ድርብ ተሳታፊነት እንደሚተካው ጠንቅቆ ያውቅ ነበር። በምሥራቅ ታፍነው የቀሩት ጓዶቻችን በዚች ደቂቃ አብረውን ባይኖሩም በሃሳብና በመንፈስ ከጎናችን ቆመው እንደነበር በያንዳንዱ አባል ዘንድ ግልፅ ነበር።

በተባለው ቀን ጥዋት የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው የጉባዔውን ተሳታፊዎችና እንግዶች ካመሰገነ በኋላ በትግሉ ሜዳ ለተሰውት ጓዶች የአንድ ደቂቃ የህሊና ፀሎት እንዲደረግ ጠየቀ። መራራው ትግል የተሰኘው መዝሙር ተዘምሮ ወደ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው የመክፈቻ ንግግር አለፍን። በንግግሩ ውስጥ ስለ ኢትዮጵያ ሁኔታና ስለ ዓለም አቀፍ ሁኔታ ገለፃ ተደረገ።

ንግግሩ እንዳበቃ ከልዩ ልዩ ድርጅቶች ያንድነት መግለጫዎች ተሰሙ። ያንድነት መግለጫ ያሰሙ የላኩና እንዲሁም በቴሌግራም ያሳወቁ የሚከተሉት ነበሩ።

1. የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ /መኢሶን/
2. የኢትዮጵያ ሴቶች አብዮታዊ ንቅናቄ /ኢሴአን/
3. የኢትዮጵያ ወጣቶች አብዮታዊ ንቅናቄ /ኢወአን/
4. TOKUMMAA IJAARSA BARTOOTA OROMOO BIYYA AWROPPA / TIBOBA /

5. በአውሮፓ የኢትዮጵያ ሴቶች ዴሞክራቲክ ማህበር
6. አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ሕብረት
7. የተባበረ ተራማጅ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች አንድነት ማህበር በሰሜን አሜሪካ
8. በቻይና የኢትዮጵያ ተማሪዎች አንድነት ማህበር
9. በሱዳን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
10. በኬንያ የኢትዮጵያ ተማሪዎች
11. በግሪክ የሚገኙ የኢትዮጵያ ተማሪዎች
12. በዴንማርክ የኢትዮጵያ ተማሪዎች
13. የሃንጋሪ ቅ/ማህበር
14. የሩማንያ ቅ/ማህበር
15. Kommunistisher Bund Westdeutschland / KBW /
16. Comité d'Entraide Belgo-Ethiopien
17. AMADA / TPO Belgium.
18. Turkish Stude.ts Union in Bohum
19. Tomelilla Fclk High School For Developments studies / Sweden /
20. Liga Gegen den Imperialismus Eritreaarbeitskreis
21. Drapeau Rouge / France /

በዚሁ እለት የሊቀ መንበር፣ የፀሃፊዎች፣ የአጊተሮችና የውሳኔ አርቃቂዎች ምርጫ ተደረገና በ10-8-79 በተካሄደው የቅ/ማህበራት ወኪሎች ስብሰባ የተሻሻለው አጀንዳ ለጉባኤ ቀረበ። የተሻሻለው አጀንዳ ለድርጅት ጉዳዮች ይበልጥ ቦታ የሰጠና የቅ/ማህበራትን ሪፖርቶች ከድርጅት ጉዳይ ጋር አብረው እንዲቀርቡ የወሰነ ሲሆን ቤቱ ከተቀበለው በኋላ ወደ አዲሲቱ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ሪፖርት ተሸጋገርን። የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ሪፖርትም ሰፊና ብዙ ነጥቦችን ያዘለ ነበር። ሥ.አ. ኮሚቴው በአመቱ ውስጥ ስለወሰዳቸው የፖለቲካ አቋሞች ስለማህበሩ ችግሮችና ራሱ ስለገጠመው ችግር በሰፊው ከተነተነ በኋላ በተነሱት ተጥቦች ላይ ሰፊ ውይይት ተደርጎ ቤቱ ሪፖርቱን በሙሉ ድምጽ ተቀበለው። በተጨማሪ ሥ.አ. ኮሚቴው ምንም እንኳን በደረሰበት ተፅና አባላቱ ካሉበት ቦታ እንዲህ ታተኑ ቢሆንም በዓመት ውስጥ በታላቅ ታታሪነት ሥራውን በሚገባ በማገባደዱ ጉባኤው የተለየ ምሥጋናውን አቅርቦለታል።

በዚኑ ለት ማታ የመፅሔት ቦርድ ሪፖርት ቀረበ። መጽሔት ቦርዱ ስለኢትዮጵያ ሁኔታ ሰፊ ትንተና ካደረገ በኋላ በአመት ውስጥ ስላወጣቸው መጽሔቶች ተነተነ። ከዚሁ ጋር አያይዞ በአመት ውስጥ በመጽሔት ቦርዱ በኩል ለታየው ድክመት ተጠያቂ ራሱና በተጨማሪም የቅ/ማህበራት በፅሑፍና በገንዘብ አለመተባበር መሆኑን ካስታወቀ በኋላ አስፈሳዊውን ገለ-ሂስ አቀረበ። ጉባኤው ሪፖርቱን አዳምጦ ከ5 ድምጽ ነፈጊ በስተቀር በሙሉ ድምጽ ተቀብሎታል።

ከመጽሔት ቦርዱ ሪፖርት በኋላ በአንዱ ቅ/ማህበር የቀረበ ስላይዱ ከታየ በኋላ የእለቱ ስብሰባ ተበተነ።

ከ12-8-79 ጥዋት እስከ 13-8-79 ከሰዓት በኋላ ድረስ ጠቅላላ ጉባኤው በሁለት ኮሚሽኖች ተከፍሎ በተሰጠው አርእስት የጥናት ውይይቶች ተካሄዱ። የጥናቱ ዝርዝር አርእስት የሚቀጥለው ነበር።



## የ19ኛው ጠቅላላ ጉባኤ የጥናት አርእስት

### ክፍል 1. አድርባይነት በዓለም ወዛደሮች እንቅስቃሴ ውስጥ

1. የአድርባይነት ዋና ዋና ጠባዮች
   - ሀ. የአመጣጡ ታሪክ
   - ለ. የቀኝ አድርባይነት
   - ሐ. የግራ አድርባይነት
2. የአድርባይነት ታሪካዊ አስተዳደግ
   - ሀ. ከ1889-1914
   - ለ. ከ1914-1956
   - ሐ. ከ1956 በኋላ

### ክፍል 2. አድርባይነት በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ

1. አድርባይነት በቀደመ አብዮት ኢትዮጵያ በተማሪው ንቅናቄ የሁለትመስመር ትግል
2. የግራ አድርባይነት ዘመን ከየካቲት66-መጋቢት69
   - ሀ. የግራ አድርባዮች ዋና ዋና አቋሞች
   - ለ. ደርግና የግራ አድርባዮች
   - ሐ. አብዮታውያን ያካሄዱት ትግል
3. የቀኝ አድርባይነት ዘመን ከመጋቢት 69 እስከዛሬ
   - ሀ. የቀኝ አድርባዮችና የኢት. አብዮት
   - ለ. ደርግና የቀኝ አድርባዮች
   - ሐ. አብዮታውያን ያካሄዱት ትግል

### ክፍል 3. የኢት. ፖለቲካዊ ሁኔታና የተራማጆች ተግባር

1. የሁኔው የኃይሎች አሰላለፍ
2. የአብዮቱ አንገብጋቢ ጥያቄዎች
   - ሀ. የዴሞክራሲ መብቶች ጥያቄ
   - ለ. የብሔረሰቦች ጥያቄ
   - ሐ. የወዛደሩ ፓርቲ ጥያቄ
   - መ. የህዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ጥያቄ
   - ሠ. የብሔራዊ ነፃነት ጥያቄ
   - ረ. ደርግና የኢት. ተራማጆች
   - ሰ. የተማሪ እንቅስቃሴ ተግባራት ይዘት
3. ተጨባጭ ተግባራት
   - ሀ. የቅስቀሳና የፕሮፓጋንዳ ትግል

ለ. የኢት. አብዮት ዓለም አቀፍ ድጋፍ ለማስገኘት
ሐ. የገንዘብ ስብሰባ
መ. የተማሪውን እንቅስቃሴ ማስፋት
ሠ. ሌሎች ድርጅታዊ ጉዳዮች

በ13-8-79 ማታ የኮሚሽኖቹ መሪዎች በውይይት ውስጥ ስለተነሱት የአስተያየት ልዩነቶች ዝርዝር ሪፖርት አቅርበው ውይይቱ በጠቅላላ ጉባኤ ቀጠለ:: ሰፊ ትምህርት የተቀሰመበት ውይይት ተካሂዶ በብዙ ነጥቦች ላይ ስምምነት ስለተደረሰ በ15-8-79 የውሳኔ አርቃቂው ኮሚቴ ለቤቱ የውሳኔውን ረቂቅ አቀረበ:: በውሳኔው ላይ ማሻሻያዎች ቀረቡ:: አባላት በሙሉ በተሰበሰቡበት በአንድ ተቃዋሚና በሁለት ድምፀ ነፈጊዎች ጉባኤው የተሻሻለውን ውሳኔ በጋለ ጭብጨባ ተቀበሉት የእለቱ ስብሰባ በአብዮታዊ መዝሙር ተዘጋ::

በ16-8-79 የቀ/ማህበራት ሪፖርቶች ተራ በተራ ቀረቡ:: ተያይዞም የኦዲተሮች ሪፖርት ቀረበ:: በተነሱት ድርጅታዊ ችግሮች ላይ ቤቱ ሰፊ ውይይት አካሄደ:: ዋነኛው ነጥብ ማህበራችን የሚገፋበትና ሰፊውን ፀረ-ቦስት ሃይል የሚያስተባብርበትን መንገድ መፈለጉ ነበር:: በዚሁም አንፃር ለመጪው ሥራ አስኪያጅና የመፅሔት ቦርድ አንዳንድ መመሪያዎች ተላለፈ ::

በ16-8-79 ማታ ቤቱ አዲሱን የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴና የመፅሔት ቦርድ መረጠ:: አዲሱ ሊቀመንበር ንግግር አድርጎ 19ኛውን ጉባኤ ዘጋ:: የእለቱ ስብሰባ እንዳለቀ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ሴቶች ዲሞክራቲክ ማህበር ባዘጋጀው ምሽት ሰፊው የማህበራችን አባላት ተገኝተው ልዩ ልዩ የባህልና የኪነት ትርኢቶች ታዩ::

በ17-8-79 ጥዋት በአራት ሰዓት በስብሰባው የተገኙ ጓዶች ወደ ሃንጋሪ ቆንስላ ሄዱ:: አካሄዱ በሃንጋሪና በመታሰይ በምሥራቅ አውሮፓ በሚገኙት ጓዶቻችን ላይ የሚደረገውን ተፅዕኖ እንዲቋቋምበልና ተፅዕኖው እንዲቆም የሃንጋሪ መንግሥት ከደርግ ጋር የተፈራረመውን ውል እንዲሰርዝ ለመጠየቅ ነበር:: ያቀረብነውን የተቃውሞ ደብዳቤ ቆንስሉ አልቀበል ቢል እንኳን ለስድስት ሰዓት ያህል ጋዜጠኞች በተገኙበት ልዩ ልዩ መፈክሮችና መዝሙሮችን በማሰማት ተቃውሞአችንን ገልጸናል:: በመጨረሻም ፖሊስ ተጠርቶ ከቆንስላው እንድንወጣ ሆኗል:: ከሰዓት በኋላ በበርሊን ከተማ ረጅም ሰላማዊ ሰልፍ ተደረገ:: ወደ 5000 የሚሆኑ የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ የሚያስረዱ ወረቀቶች ተበተኑ:: በማግስቱ እንዳየነው ብዙ ጋዜጦች ስለ ተደረገው ተቃውሞና ሰልፍ ጽሁፍ አውጥተዋል:: ቢ.ቢ.ሲ በአፍሪካ ፕሮግራሙ ላይ ዜናውን አስተላልፏል::

19ኛው ጉባኤ በዚህ መልክ ተካሄደ:: ጉባኤአችን በትግል መንፈስ የተሞላ ከመሆኑ በላይ አኢተማ የሚደርስበትን ጥቃት ተጋትሮ ትግሉን እንደሚቀጥል በድጋሚ ያስመሰከረበት ጉባኤ ነበር:: ከሁሉም ይበልጥ ግን ራሱ ውሳኔው እንደሚያመለክተው 19ኛው ጉባኤአችን ለአዲሱ የትግል ምዕራፍ በአዲስ መንፈስ የተነሳንበት በአብዮቱ ጎዳናም ለመላው ተራማጅ ሃይል የአንድነት ጥሪ ያስተላለፍንበት ጉባኤ ነበር::



# በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር

# The Ethiopian Students' Union in Europe

## የአኢተማ 19ኛ አመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ የፖለቲካ ውሳኔ

### መግቢያ

የክፍለ ዘመናችን 60ኛው ዓመቶች በኢትዮጵያ ህዝቦች ታሪክ ውስጥ ከፍተኛና ሰፊ ስፍራ ይዘው ይኖራሉ:: ገና ብዙ ብዙ ይፃፍላቸዋል:: ገና ብዙ ብዙ ይነገርላቸዋል::

ከ1966-1969 አጋማሽ ድረስ የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች በምድሪቱ ላይ ፈንጥዘው የረባቸውን ታሪክ አረባቸው ብሥራት የዩ:: በከተማ ይሁን በገጠር ረባቸውን ተናገሩ አድርገው ቢረሙቱ፣ እነርሱ የታሪክ ባለቤት ለመሆናቸው ዘች፡ አያጠራጥርም ነበር:: እነርሱ የነቁትን፣ የተደራጁትንና የታጠቁትን ያህል ደግሞ፣ ህዝባዊትና ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ የምትመሠረትበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን ገልፅ ሆኖ ነበር::

ነገር ግን ከ1969 ዓ.ም. አጋማሽ በኋላ፣ በህዝባዊነቷ አያበበች መጥታ የነበረችው ኢትዮጵያ በጥቁር የፀረ-አብዮት ጉም ተሸፈነች:: ህዝቦቿና ታጋይ ልጆቿ፣ ከታፈነበት ጨለማ ለመውጣት "ዲሞክራሲ አሁኑኑ" እያሉ ሲጥሩ፣ አድሃሪያንና አደርባዮች "ዲሞክራሲ በትግል" እያሉ ፀረ-አብዮታዊነታቸውን ገለጡ:: ህዝቦቿና ታጋይ ልጆቿ: የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች አንድነት በእኩልነት ላይ እንዲመሠረት ሲጥሩ፣ አድሃሪያንና አደርባዮች ትምክህተኝነትን አነገሡ፣ በጭቁን ብሔረሰቦች ላይ በታሪካችን ውስጥ ተወዳዳሪነት የሌለውን ሰፊ ጭፍጨፋና የጥፋት ዘመቻ ከፈቱ:: ህዝቦቿና ታጋይ ልጆቿ ብሔራዊ ነፃነታችን እንዳይደፈር በተናጥነት ሲጧጧሩ፣ አድሃሪያንና አደርባዮች ብሔራዊ ነፃነታችንን አስገሠሡ፣ ይህችን በአለም ህዝቦች ሸንጎ ፊት ተገቢ ቦታዋን እንድታገኝ የምንታገልላትን ኢትዮጵያችንን አዋረዷት:: ህዝቦቿና ታጋይ ልጆቿ፣ ተራማጆች በዲሞክራሲያዊ መንገድ እንዲተባበሩ ሲታገሉ፣ አድሃሪያንና አደርባዮች እነርሱን ይምሰበው የረባቸውን የፀረ-አብዮት ፓርቲ ወደማቋቋም አመሩ::

የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ባንዱ በኩል ፀረ-አብዮት "ኢሠፓአኮ" ፓርቲ በሚል ሥልጣኑን ህጋዊ አድርጎ ለመደላደል የሚሯሯጥበት አገር ናት:: በሌላው በኩል፣ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ እንደገና በማመፅ የአዲሱን የካቲት የታሪክ ምዕራፍ ለመክፈት የሚዘጋጅበት አገር ነች::

በአኢተማ 19ኛ ጠቅላላ ጉባኤ የፖለቲካ ውሳኔ ደርቧቸው የሚያነሡት ሁሉ እንደኛ፣ ውሳኔው ሰፊና ትንተና አዘል መሆኑን፣ ሁለተኛ፣ እንደተመሳሳለ ስላለፈት ሁለት ዓመታ

ት እንደሚያወሳ ይገነዘባሉ፡፡ ይህ የሆነው፣ ከዚህ በላይ ያነሳነውን የታሪክ ምዕ
ራፍ በጥሞና ለማስገንዘብ በማሰት፣ ያለፈውን በየክፍሉ በሰፊው መገምገም አስፈላጊ
ስለሆነ ነው፡፡

ውሳኔው በአራት አቢይ ክፍሎች የተከፈለ ቢሆን፣ ዋና ዋና በሆኑት የፖለቲካ፣ የድር
ጅትና የሰብዓዊ መብቶች ጥያቄ ላይ ያተኩራል፡፡ ከ11-8-79 እስከ 17-8-79
በምዕራብ በርሊን ከተማ የተሰበሰበው በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 19ኛ
ጠቅላላ ጉባዔ የኢትዮጵያን ዛሬያዊ ሁኔታና የተራማጆችን ተግባር ከመረመረ በኋላ ከ
ዚህ በታች የሰፈረውን የፖለቲካ ውሳኔ እንዳጸደቀ ሲገልፅ፣ አንባቢያች ሁሉ እያንዳ
ንዱን ጉዳይ በጥሞና እንዲያነቡትና እንዲመለከቱት ጥሪውን ያቀርብላቸዋል፡፡

ነገር ግን ደግሞ አንድ የመጨረሻ ነጥብ፣

በአኢተማ 19ኛ ጠቅላላ ጉባዔ በሬና ዴሞክራሲያዊ ውይይቶችን አድርጐ ከዚህ በታች
የቀረበውን የፖለቲካ ውሳኔ ሲያሳልፍና በዳበረው የትግል ሞራሉ እርግጠኝነት ተሞና
ቢፈጽም፣ በዚያው ሰሞን በበርሊን ከተማ ተደርጎ የነበረው የፌዴሬሽን "ጉባዔ" ቢነ
ታሪክ ከርሞ ያለአንዳች ውጤት ተበትኗል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ በውጭ አገር የደ
ርግ/ሰደዱ ስላይ ሆና የተደራጁ የቀኝ አድርባዮች ቡድን፣ የቀኝ ሃይሎችን "ህብረ
ት ድምፅ" ለመገልበጥ በዕሩን በማሾል ላይ ይገኛል፡፡ በአኢተማ በአብዮታዊ መስመ
ሩ ፀንቶ ኢህአፓ-ፌዴሬሽንን እንደመከተ ሁሉ፣ የቀኝ አድርባዮችንም ውር ውር እንደ
ሚደመስስ የማንጠራጠር መሆናችንን በልበ ሙሉነት እንገልፃለን፡፡ ...........



## ክፍል 1

### 1. ስለ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲ አብዮት ፕሮግራም ጥያቄ

በኢትዮጵያ በመካሄድ ላይ የሚገኘው አብዮት አዲሱ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ነው፡፡ ይህ
ሀቅ በሚገባ ታውቆ ለዚህ ዓይነቱ አብዮት በአንድነት ሊሰለፉ የሚችሉ ኃይሎች ሁሉ
ተባብረው ቀንደኛ ጠላቶቻቸውን ፊውዳሊዝም ኢምፔሪያሊዝምና ቢሮክራሲ ካፒታሊዝም ይደመ
ስሱ ዘንድ የኢትዮጵያ ተራማጆች ከብዙ ዓመታት ጀምረው በግንባር ቀደምትነት ታግለዋል.
ማህበራችንና ሌሎች አብዮታዊ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ከቀድሞ አብዮት ኢትዮጵያ
ጀምረው ለዚህ አብዮት ግብ መምታት በታላቅ ቆራጥነት ታግለዋል፡፡

የየካቲት አብዮት ከፈነዳም በኋላ ሃቀኛ ተራማጆች የግራና የቀኝ አድርባይነትን ለማጋ
ለጥ ባደረጉት የርዕዮተ ዓለም ትግልና ለዚህ አብዮት ሰፊውን ሕዝብ በማንቃት፣ በማደ
ራጀትና በማስታጠቅ የተጫወቱት ሚና ታሪክ ምንጊዜም የሚረሳው አይደለም፡፡ ይህ የሃቀ
ኛ አብዮታውያን ትግል ተፈላጊ ፍሬውን በመስጠቱ ለብዙ ዘመናት የኢት. ተራማጆች የት
ግል ሰንደቃቸውን አድርገው የተዋጉለት ዓላማ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ጭቁን ህዝቦች ዘንድ
ተቀባይነት በማግኘቱ በመንግሥት ደረጃም እንደ መመሪያ ለመወሰድ በቃ፡፡ ሚያዚያ
13 ቀን 1968 ዓ.ም. የረጅም ጊዜ ትግል ውጤት የሆነውና ገና ለረጅም ጊዜ ለመላ
ኢት ተራማጆች የትግል መሰብሰቢያ መድረክ ሆኖ የሚቆየው የኢት. ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ
አብዮት ፕሮግራም ታወጀ፡፡

ከዚህ ወቅት አንስቶ በሀገራችን ምድር በአብዮትና በፀረ-አብዮት መሃከል የተካሄዱ
ትግሎች በዚህ ፕሮግራም ደጋፊዎች በአንድ በኩል ይህንን ፕሮግራም በቀጥታም ሆነ በተ
ዘዋዋሪ በሚቃወሙ ኃይሎች በሌላ በኩል ነው ማለት ይቻላል፡፡ ተደጋግሞ እንደተነገረ
ው ይህ ፕሮግራም የብሔረሰቦችን የመገንጠል መብት ካለማወቁ በስተቀር ለማንኛውም የአ
ብዮቱ ጥያቄ አርኪና የተሟላ መልስ አለው፡፡ በሰፊው የኢት. ሕዝብ ዘንድ እጅግ ከ
ፍተኛ የሆነ ተቀባይነት ሲያገኝ በዚያው ልክ ደግሞ ለከሃዲዎችና ለተንሸራታቾች ምንም
ዓይነት የማወናበጃ ፍንጭ ነስቷቸው ቆይቷል፡፡ ወደፊትም ከዚህ ፕሮግራም የሚንሸራተ
ቱ ኃይሎች አማራጭ የሌለው የታሪክ አተላነት ጽዋ እየተጎነጩ ውርደት ይከናነባሉ እንጂ
በኢት. ምድር ይህንን ፕሮግራም እየካዱ በአብዮቱ በፈር ቆመናል ለማለት የሚችሉ አይ
ሆኑም፡፡

የኢት. ጭቁኖች የዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብቶች ጉዳይ፣ የብሔረሰቦች እኩልነት ጥያቄ፣
የሀገራችን ክብርና ነፃነት ጥያቄ፣ የአዲሲቱ ኢት. የኢኮኖሚ መዋቅር ጉዳይ ወዘተ ሁ
ሉ እየተነሱ ተገቢ መፍትሄ አቅርቦላቸዋል፡፡ ዛሬ ምንም እንኳ በፀረ-አብዮት ማየል
የተነሳ እነዚህ ሁሉ ጉዳዮች እንደገና ከጥያቄ ውስጥ ቢገቡና እንዳልነበሩ ሆነው ቢሻ
ሩም ታጋይ ኢትዮጵያውያን በዚህ ፕሮግራም ዙሪያ የኢት.ን ሰፊ ሕዝብ ለማንቃትና ለማ
ደራጀት ያደረጉት ጥረት በምንም ዓይነት ጠርቦ የማይደመሰስበት አስተማማኝ ደረጃ ላይ
ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ለዚህ ፕሮግራም ወደፊት መረመዱ ቢሻል "ከፕሮግራማችን ጋር
ወደፊት" እያሉ የወደቁት ገበሬዎችና ወዛአደሮች፣ መለዮ ለባሾችና ወጣቶች፣ ሴቶች፣ የ
ጭቁን ብሔረሰብ ታጋዮች፣ ምሁራንና አገር ወዳዶች፣ ተራማጅ የፖሊስና የጦር መኮንኖች
ዴሞክራቶች፣ ነጋዴዎች ወዘተ.. ደም ይህን ፕሮግራም በኢት. ምድር ላይ ምንጊዜም እ
ንደማይፋቅ አድርጎ ጽፎታል፡፡ ታጋይ የኢት. ልጆች ደግሞ ያለአንዳች ማወላወል የዚ
ህን ፕሮግራም አርማ ከወደቁት ጓዶች ተረክበው ወደፊት ለመጓዝ በታሪክ ፊት ቃል ገብ
ተዋል፡፡ መላው የኢት. ሠራዊት ታልኪዓኑ ለዚህ ፕሮግራምና ለሰፊው ሕዝብ እንጂ ለ

ማንም ግለሰብ ወይም ቡድን እንዳልሆነ አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የፈጀውን ጊዜ ቢፈጅ የብሔረሰብ ጥያ. አብዮት ፕሮግራማችን ግቡን እንደሚመታ፣ የጠየቀውን መስዋዕትነት ቢጠይቅ በዚህ ፕሮግራም የተተለመችው ሃቀኛ ሕዝባዊት ዴሞክራሲያዊት ኢት. እንደምትገነባ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

ከላይ እንዳልነው ባለፉት ስድስት ዓመታት በኢት. ምድር የተካሄዱት ትግሎች በዚህ ፕሮግራም ደጋፊዎችና ተቃዋሚዎች መካከል የተካሄዱ ትግሎች ናቸው፡፡ ፀረ-አብዮት ኃይሎችና ከነሱ ተደባልቀው የአብዮቱን ሠፈር ማጥቃት የጀመሩት የቀኝ አድርባዮችና ከሃዲዎች በመጀመሪያ ላይ በአብዮቱና በፕሮግራሙ ስም ለመማል ለመገዘት ተገደው ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ መማልና መገዘታቸው የአብዮቱን ሠፈር ከማጥቃት ሃቀኛ አብዮታውያንን ከማሰር፣ ከመግረፍ፣ ከመረሸን፣ ሕዝባዊ ድርጅቶችን ከማፈራረስ፣ የፊውዳል ቡርዣውን ቢሮክራሲ መልሶ በኢት. ጭቁኖች ላይ ከመጫን፣ ጭቁን ብሔረሰቦችን ከማሳደድ፣ የሀገራችንን ብሔራዊ ክብርና ነፃነት ለባዕዳን አሳልፈው ከመሸጥ፣ ወዘተ.. ባጭሩ የፕሮግራሙን ይዘት አንቀጽ በአንቀጽ ከመካድ አላገዳቸውም፡፡ ዛሬ አድሃሪዎችና ከሃዲዎች ከዚህ አልፈው ሄደዋል፡፡ የዚህን ፕሮግራም ይዘት በድርጊት ከመካድ አልፈው ፕሮግራሙን እንዳለ በይፋ ለመሰረዝ ዝግጅት እያደረጉ ናቸው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፕሮግራሙ "የንዑስ ከበርቴዎች ፕሮግራም ነው' 'የማኦይስት መኢሶን ቅዠት ነው' 'አሁን የሚ. አብዮት ደረጃ ተጠናቆ ለሶሺያሊዝም ግንባታ ደርሰናል" መከተል ያለብን የአ.ኢ. ኢኮኖሚ ሳይሆን "ካፒታሊስት አልባ" የሆነ የልማት ጎዳና ነው ወዘተ በማለት በአድሃሪ ኃይሎች ፊታውራሪዎች በሆኑት በቀኝ አድርባዮች የተጀመረው ቅስቀሳ ለዚህ ለለየለት ክህደት መንገድ ጠራጊ እንደሆነ ባይታለም የተፈታ ነው፡፡ በዚህ አንፃር የኢት. ዴሞክራቶች አገር ወዳዶች፣ ሃቀኛ ማርክሲስቶች፣ በጠቅላላው በወደፊት ጊዜያት ዴሞክራት ታሪካዊና ኃላፊነት አለን የሚሉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ተግባራቸው ግልጽ ነው፡፡ በአውሮፓ የኢት. ተማሪዎች ማህበርን በሚመለከተው በኩል፣

1ኛ/ አብዮታዊት ኢትዮጵያ ጋዜጣ ገና ፕሮግራሙ ሲታወጅ በግልጽ እንዳስቀመጠችው" ይህ ፕሮግራም የረዥም ጊዜ የትግል ውጤት እንደመሆኑ መጠን ከሥራ ላይ እንዲውል ገና የረዥም ጊዜ መራራ ትግል ይጠይቃል፣ ይህ የኢት. ብ.ዲ.አ.ፕ. ገና በሚመጡት የረዥም የትግልና የመስዋዕትነት ዓመታት የኢት. አርሶ አደሮች፣ ወዛደሮች፣ ጭቁን ወታደሮች፣ ተራማጅ ምሁራን፣ ተማሪዎች፣ ተራማጅ መኮንኖች ነጋዴዎችና አገር ወዳዶች በጠቅላላው የሰፊው ሕዝብ ወገን የሆኑ ኃይሎች በሙሉ ተባብረው በመሰለፍ ገና ለብዙ ዓመታት የሚታገሉበት ፕሮግራም ነው፡፡" ባለችው መሠረት ማህበራችን እንኳን ዛሬ ገና ለሚመጡት ዘመናት ይህንን ፕሮግራም የትግል መመሪያ አድርጎ ይታገላል፡፡ ይህንን ፕሮግራም በማክበርና ለሰው እስከመጨረሻው ለመታገል የገባውን ቃልኪዳን ዛሬ በወደፊት ኢትዮጵያውያን ፊት ቃልኪዳኑን በድጋሚ ያድሳል፡፡

2ኛ. ከዚህ ፕሮግራም አንፃር ክህደታቸው እየጠመረ በሄደ ቁጥር ሰፊው ሕዝብ እየተፋቸው ቢሄድም የቀኝ አድርባዮችና ከሃዲዎች በተለያዩ ዘዴዎች ሕዝቡን ለማወናበድ ጥረታቸውን እንደሚቀጥሉ የታወቀ ነገር ነው፡፡ ስለሆነም ተራማጆች አሁንም በሆነ ፕሮግራሙን አንቀጽ በአንቀጽ እየተነተኑ ሃገራችን በሚያጋጥሟት የፖለቲካ፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ችግሮች ሁሉ የሚሰጠውን መልስ ማብራራት፣ አድርባዮችና ከሃዲዎች በፕሮግራሙ መማል መገዘታቸውን እስከቀጠሉ ድረስ ከያንዳንዱ ፀረ-ህዝብ ድርጊታቸው እየተነሱ ከፕሮግራሙ አንፃር የሚያደርጉትን ክህደት ማጋለጥ አለባቸው፡፡

3ኛ. የፕሮግራሙ ይዘት በበቂ ባይብራራላቸው ወደ ፀረ-አብዮት ሠፈር ለተደባለቁ ወይም ከዳር ቆመው የታጋይ ተመልካች የሆኑትን ኃይሎች ለሕዝባዊት ኢት. በሚደ



ረገው ትግል ማሰለፍ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም በተለይ ዴሞክራቶችን፣ አገር ወዳዶችን ንዑስ ከበርቴውንና በፕሮግራሙ ክልል ውስጥ ራሱን ጠቅሞ ሀገሩን ለመጥቀም ለመሰማራት ለሚፈልገው ብሔራዊ ከበርቴ ክፍል እስከአሁን ከተደረገው ቅስቀሳ ይልቅ በሩ ያለ የፕሮግራሙን ይዘት የማብራራት ዘመቻ ያስፈልጋል ብሎ ያምናል፡፡

4ኛ. ለፕሮግራሙ መቀልበስ ከሆኑት ምክንያቶች አንዱ ከተወሰነ ደረጃ በኋላ የአብዮቱ ጠላት እየሆነ በመጣው በወሳኙ ደርግ በመመራቱና የወዝአደር አመራር ባይኖረው በመቅረቱ ስለሆነ ከቀልበሳ አድኖ ለግብ የሚያደርሰው ሃቀኛ የወዝአደር ፓርቲ እንዲቋቋም ከሀቀኛ ማሌዎችና ከወዛደሩ ጋር ቆሞ ይታገላል፡፡

ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ግቡን ሊመታ የሚችለው በሃቀኛ የወዛደሩ ፓርቲ መሪነት ብቻ ነው፡፡ ይህን የተገነዘበው፣ የጭቁኖችን ዓብዮት የከዳው፣ ወደስርዓተ ቢሮክራሲያዊ ከበርቴነት በመለወጥ ላይ ያለው ስደዱ/ደርግ በብ.ዲ.አ.ፕ. ፈንታ "የከበርቴ አልባ እድገት" የሚለውን የከሳሾች ፍልስፍና በሥራ ለመተርጎም ሽር ጉድ በማለት ላይ ይገኛል፡፡ ይህ የከሳሾች ፍልስፍና ፀረ-ማሌነቱን ከብዙ በጥቂቱ በሚከተሉት መሠረታዊ ነጥቦች ላይ እራሱን ያጋልጣል፡፡

1. የዴሞክራሲያዊ አብዮት ያለወዛደሩ መደብ አመራር ግቡን ይመታል ስለሚል፣

2. በንዑስ ከበርቴው መደብ አመራር ሶሺያሊዝምን ለመገንባት ይቻላል ብሎ በማመኑ፣

3. ከፊውዳሊዝም ወደ ካፒታሊዝም ሳይታለፍ በቀጥታ ወደ ሶሺያሊዝም መሸጋገር ይቻላል ስለሚልና የኢኮኖሚን ዕድገት በውጭ እርዳታ ይሟላል በማለት፣ ራስን በራስ መቻል የሚለውን የማሌ አቋም በመካዱ፣

4. ወደ ሶሺያሊዝም በሰላማዊ መንገድ መሸጋገር ይቻላል ብሎ ስለሚያምንና ከትግል ስልቶች ውስጥ ትጥቃዊ ህገ-ወጥ መንገዶችን ባለመቀበሉ፣

19ኛው ጠቅላላ ጉባኤ ይህን የተባባተ ፍልስፍና አበጠርጥሮ ካጠና በኋላ የከሳሾች ፍልስፍና መሆኑን እያመነ፣ በደዱ/ደርግ የብ.ዲ.አ.ፕ.ን በዚህ ፀረ-አብዮት ፍልስፍና ለመተካት የሚያደርገውን ሽር ጉድ እያወገዘ፣ ይህ ፀረ-ማሌና ከሳሽ ፍልስፍና እንዳይስፋፋ በሰፊው ሕዝብ ፊት እያጋለጠ ይታገላል፡፡

## 2. የዴሞክራሲ መብቶች ጥያቄ

በዚህ ጥያቄ ላይ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ከሃቀኛ አብዮታውያን ጎን ተሰልፎ ከመታገል ያቋረጠበት ወቅት የለም፡፡ ከየካቲት በፊትም ሆነ በኋላ ማህበራችን ይህንን የኢትዮጵያ አብዮት አንገብጋቢ ጥያቄ በተደጋጋሚ አንስቶ ቅስቀሳ አካሂዶታል፡፡ የፊውዳል አገዛዝ ሰፍኖ በጨለማ ይኖር የነበረው ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብም በዚህ አንገብጋቢ ጥያቄ ላይ ከዳር እስከዳር ተንቀሳቅሶ የትግሉ ደረጃ በፈቀደለት መጠን የመናገር፣ የመጻፍ፣ የመደራጀት፣ የመሰብሰብ መብቶችን ከሥራ ላይ ለማዋል አብዮቱን ወደፊት ሲያራምድ ቆይቷል፡፡

ይህ ጥያቄ ከመጀመሪያ አንስቶ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ጭቁኖች የታገሉለት ጥያቄ ስለነበረ ወላዋዩ አድርባዮች ይቀሩና የለየላቸው አድሃሪያኖች እንኳን ቢሆኑ ዴሞክራሲ ለምን? ለማን? መቼ? በሚሉት ጥያቄዎች ላይ ለማወናበድ ሞከሩ እንጂ ጥያቄውን ፊት ለፊት ወጥተው የተቃወሙበት ወቅት አልነበረም:: ምንም እንኳን በዚህ ጥያቄ ላይ ከተካሄዱት ክርክሮች ጎልቶ የታየው ''ከገሬ''አድርባዩ ከኢሕአፓ ጋር የተደረገው ''ዴሞክራሲ ለማን'' ይል የነበረው ጥያቄ ቢሆንም በጊዜው የዚያን ያህል ክርክር ያልተደረገባቸውና ዛሬ በተያዘው ትግል ይበልጥ ዋናነት ያላቸው ሌሎች ሁለት ጥያቄዎች መሆናቸው ግልጽ ነው::

ዴሞክራሲ ለማን?የሚለው ጥያቄ በጊዜው የኢትዮጵያ አብዮታውያን ''ዴሞክራሲ ለጭቁኖች፣ ዴሞክራሲ ለፀረ-ፊውዳል፣ ለፀረ-ኢምፔሪያሊስት፣ ለፀረ-ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ሃይሎች በሙሉ''ብለው መልሰውት ነበር:: በወቅቱ ክርክሩ በዚህ ላይ ማተኮሩ ዴሞክራሲ ለምን? በሚለው ጥያቄ ላይ ዴሞክራሲ ለመናገር፣ ለመፃፍ፣ ለመሰብሰብ፣ ለመደራጀት ወዘተ.. እንደሆነ፣ ዴሞክራሲ መቼ ለሚለው ጥያቄ ደግሞ ለኢትዮጵያ አብዮት መገሩት፣ ዴሞክራሲ ባይውል ባያድር መሰጠት ያለበት መሆኑ መኢሶንና ሌሎች አብዮታውያን ከደርግ ገዥ ከበርቴዎችና ከተጎ አድርባዮች ጋር በተለይ በ1967 ዓ.ም.-1968 ዓ.ም. ከፍተኛ ትግል አካሂደዋል:: ዛሬ ለዴሞክራሲ የተደረገውን ትግል ታሪክ መለስ ብለን ስንመለከት ከኢሕአፓ ጋር ዴሞክራሲ ለማን? በሚለው ጥያቄ ላይ ክርክር በመካሄዱ ቀደም ብሎ የመኢሶንና የሌሎች አብዮታውያን ትኩረት አተኩሮ የነበረው የዴሞክራሲ መብቶችን ይዘትና አጣዳፊነት በማመልከተው መስክ ነበር:: የሆነውም በዚህ በዴሞክራሲ ጉዳይ በሦስቱም ጥያቄዎች ላይ በተካሄደው ትግል ሃቀኛው አብዮታዊ መስመር ሙሉ በሙሉ ድልን በመቀዳጀቱ ይህ መስመር የጸደቀበት የኢትዮጵያ ብ.ዲ.አ.ፕ. በሚያዝያ ወር 1968 ዓ.ም. ታወጀ:: በዚህም መሠረት የአብዮቱን ሰፊ ድል በማረጋገጥ በዚህ ጥያቄ ላይ ''ዴሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ ባስቸኳይ'' የሚለው መፈክር በኢትዮጵያ ምድር ከዳር እስከዳር ተስተጋባ:: ይህንንም መፈክር በተግባር የሚተረጉም ''ረቂቅ''አዋጅ በአብዮታዊው የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት ተሰናድቶ ቀረበ:: ነገር ግን ወላዋዩ ደርግ ከአድሃሪው ቢሮክራሲና ከውጭ ሃይሎች ጋር አብሮ የብ.ዲ.አ.ፕ.ን እየከዳ፣ አቋሞቹን ሁሉ እየከዳ የኢትዮጵያን አብዮት መውጋት ጀመረ:: ረቂቁ አዋጅም እንዳይታወጅ ተደረገ:: በኢትዮጵያም አንገብጋቢ የሆነው የአብዮት ጥያቄ እየታፈነ ዴሞክራሲ እየመነመነ ፀረ- አብዮት እያየለ መጣ::

በዚህ አንፃር ሰፊው የኢት. ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በእጁ እያስገባ በሄደ ቁጥር፣ አብዮቱን ወደፊት ለማራመድ የሚያስችለውን ያህል እንጂ ባልጠበቀው ፍጥነት ከአድሃሪያን ጋር በማበር የከዱት ወላዋዮች ዴሞክራሲን ሲያፍኑት ትግሉ ምን ያህል እንደሚጎዳና እንደተጎዳ ማየት የዚህን ጥያቄ ዋናነት ለመገንዘብ ይረዳል::

በመጀመሪያ የየካቲት ሕዝባዊ አብዮታዊ ማዕበል ከአድሃሪያን ሥርዓት ውጭ በተነሳበት ወቅት ሕዝቡ በገዛ ሃይሉ እየተሰበሰበ፣ በሰላማዊ ሰልፍ እያደረገ፣ በጋዜጦች ሃሳቡን እየገለጸ፣ ድርጅቶቹን ከዕለት ዕለት እያጠናከረ በጥሩ ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ከነጋሲው አገዛዝ ውጭ ከሥራ ላይ እያዋለ አብዮቱን ወደፊት ማራመድ ችሎ ነበር:: በነርገር ሥልጣን ጨብጦ የነበረው ፀረ-ሕዝቡ አንገዳልካቸው መኮንን ባይቀር ለጊዜው ከነ አክሊሉ ጋር ስለነበረው ግጭት አነቡን ለማግኘት ሲል ''ዴሞክራሲ ፈቅጃለሁ''እስከ ማለት ደርሶ ነበር:: ነገር ግን ህዝቡ በትግሉ በተቀዳጀው ዴሞክራሲ እየተጠቀመ የእንዳልካቸውን መንግሥት ሲዋጋና አብዮቱ እየገፋ ሲሄድ የእንዳልካቸው መንግሥት ም



ን ያህል ''አደገኛ''እንደሆነበት በመረዳቱ የህዝቡን መብቶች ለመገታት በባንኮር በብሔራዊ ፀጥታ ኮሚሽን፣ በእስራት፣ ለማስፈራረት የኢትዮጵያን ህዝብ ትግል ለመገታት ተፍጨርጭሮ ነበር:: በጊዜው የነበሩት አድርባዮች ህዝቡ ከአድሃሪያን ነጥቆ በተቀዳጀው ዴሞክራሲያዊ መብቶች እየተጠቀመ ለተሟሉ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሲታገል ''ለእንዳልካቸው ፋታ ስጡት''' ''ያለንም ዴሞክራሲ ኢሳወቀነበት ትጥር ይደረገብን''ወዘተ እያሉ የአብዮቱን ትግል ለመገታት ይፍጨረጨሩ ነበር:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በሃቀኛ ልጆቹ ግንባር ቀደምነት አብዮቱን እንደ እሳት ነበር እየተከሳከለ ወደፊት ገሰገሰ እንጂ በአድሃሪያኖችና በአድርባዮች ማወናበጃ ትጥቁን አልፈታም::

ሁለተኛ ይህንን ሰፊው ሕዝብ የሚያጠልበትን የዴሞክራሲ መብቶችንም በመገመትና ይህ ጥያቄ የህዝብ ወገን ለሆነው ሠራዊትና ዴሞክራት አገር ወዳድ መኮንኖች ዘንድ ያለውን ተቀባይነት የተረዳው የጦር መኮንኖች አስተባባሪ ደርግ ራሱን ሥልጣን ላይ ለማደላደል ሲል ፀረ-ህዝቡን እንዳልካቸውን ወገን ለመጣል በዚህ ህዝባዊ ጥያቄ ላይ ተመርኩዟል:: ይህ የዴሞክራሲ መብቶች ጥያቄ ሠራዊቱ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ላይ ሀ ብሎ ብቅ ሲል ይዞ የተነሳው ጥያቄ ትክክለኛ ጥያቄ በመሆኑ የጦር ሃይሎች አስተባባሪ ኮሚቴ ሐምሌ ሁለት ቀን 1966 ዓ.ም. ዓላማዬ ብሎ ባወጣው ባለ 13 ነጥብ ፕሮግራም ላይ የዴሞክራሲ መብቶችን ከሥራ ላይ ለማዋል ቃል ገብቶ ነበር:: ነገርግን መስከረም ሁለት ቀን 1967 ዓ.ም. ንጉሡን አውርዶ ሥልጣን ሲይዝ ደርግ ፀረ-ዴሞክራሲ አዋጅ አወጀ:: ነገርግን የእንዳልካቸው መፍጨርጨር አፍላውን የኢት. አብዮት ሊገታው እንዳልቻለ ሁሉ ይህም የደርግ ዴሞክራሲን የማፈን መከራ የሰፊውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል አልገታውም:: በደርግ እየታሰሩም ሆነ እየተረሸኑ የኢት. አብዮታውያንና ሠፊው ህዝብ ለመሬት፣ ለዴሞክራሲ፣ ለብሔራዊ ነፃነት የሚያካሂዱትን ትግል ቀጠሉ:: የደርግ ፀረ-ዴሞክራቲክ አዋጅና ማስፈራረት ሰፊውን ህዝብ ለተገቢ ጥያቄዎች በሰላማዊ ሰልፎችን፣ የሥራ ማቆም አድማዎችን፣ ከማድረግ አብዮታውያንን ደግሞ በህቡዕ ወረቀቶቻቸው አብዮቱን ፈር ለማስያዝ ቅስቀሳቸውን ከማካሄድ ሊያግዳቸው አልቻለም::

ሦስተኛ ሰፊው ህዝብ በአብዮታዊ ትግሉ ነፊት የዘመናት ትግሉና መሠዋትነቱ ፍሬ የሆነው የመሬት አዋጅ በየካቲት 1967 ዓ.ም. ከታወጀ በኋላ በያለበት አገሪቱን ባጥለቀለቀት የገበሬ ማህበራት አማካኝነት የዴሞክራሲ መብቶች ጥያቄ ከመቼውም ይበልጥ ተጨባጭና ግልጽ የሆነ ይዘት አገኘ:: የኢትዮጵያ ገበሬዎች የመሬትንና የነፃነትን ጥያቄ አያይዘው የሚመለከቱበት ከፍተኛ የንቃት ደረጃ ላይ ደረሱ:: የአድሃሪያኖችንና የነኢሕአፓን ሴራ እየተቋቋሙ በያለበት የተቋቋሙት ዴሞክራሲያዊ የሆኑት የገበሬ ማህበራት ድሉቸን ለማረጋገጥ የሚጠቀሙባቸው የአብዮታዊ ትግል መሣሪያዎችና አዲሱን ህይወት መልክ ለማስያዝ የሚጠቀሙባቸው የአስተዳደር አውታር ሆነው ተገኙ:: በዚህም አብዮታዊ ጠባያቸው የተነሳ የቀደሙ ስርአት አውታሮችን መደምሰሻና መተኪያ ሆነው በመገኘታቸው ከመወለዳቸው አንስቶ ከፊውዳል ቡርዧው ቢሮክራሲ ጋር የሞት ሽረት ትግል ማካሄድ ጀመሩ:: ከዚህን ወቅት አንስቶ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የተካሄደው ትግል በአጭሩ፣ በታጋዩና ሕዝባዊው ሥልጣን በአንድ በኩል በቀድሞው በቢሮክራሲያዊና በበሰበሰው ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ተቋሞች መካከል የተካሄደ ትግል ነው:: በከተሞችም በተለይ የቀበሌ ማህበራት፣ የወዛደር ማህበራትና የአብዮት ጥበቃ ኮሚቴዎች ከተቋቋሙበት ወቅት አንስቶ የተካሄደው ትግል አንዱ መልኩ ይኸው በታጋዩ ሕዝባዊ ድርጅቶች ሥልጣንና በበሰበሰው ቢሮክራሲያዊ ስልጣን መካከል የተካሄደ መሆኑ ነው:: በዚህም የተነሳ በተለይ 1968ና በ1969 ውስጥ በአብዮታውያን ግንባር ቀደምነት በሚሊዮን የሚቆጠሩት የኢትዮጵያ ጭቁኖች ለዴሞክራሲ ያደረጉት ትግል አዲስ ተጨባጭ የሆነ ይዘት ነበረው:: ለዴሞክራሲ መታገል ማለት ጭቁኖች እንዲነቁ እንዲደራጁና እን

ሊያዉቁ እንዲሁም ለሌሎች ኑሯቸው አስተዳደር በከፍተኛ መበዝበዝ የመሠረቷቸው ድርጅቶቻቸው እንዲያብቡ፣ አብቦዉም የተጀመረዉን የበሰበሰ ቢሮክራሲ እንዲጠናከሩ የተደረገ ትግል ነበር፡፡ በዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ እንቅስቃሴ እጅግ ከፍተኛው ደረጃ ደርሶባቸው በነበረት እመታት ለዲሞክራሲ የተደረገው ትግል ከፍተኛ ዉጤቶች አስገኝቶ ነበር፡፡ ከየካቲት 1968 ዓ.ም. እንስቶ የቅጥረኞቹ ቡድን በርዕዮተ ዓለም ትግል ሙሉ በሙሉ ተሸንፎ ''ከርክር በቃኝ''ብሎ እስከወረደበት እስከ ግንቦት 1968 ዓ.ም. ድረስ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ አብዮት መድረክ ላይ የተካሄደው ይፋ የርዕዮተ ዓለም ትግል ለሃቀኛ አብዮታዊያንና በመሠረቱ ግንባር ቀደምነት ይወክል ለነበረው አብዮታዊ መስመር ከፍተኛ ድልን ሲጎናጸፍ፣ ለአብዮቱም ጥራትና ምጥቀት ትልቅ አስተዋጽኦ አስገኘ፡፡

ከዚሁ ድል ጋር ተያይዞ፣ የዚህ ድል ዉጤት ሆኖ በሚያዝያ ወር 1968ዓ.ም. የታወጀዉን የኢትዮጵያ ብ.ዲ.አ.ፕ. ለህዝቡ ለማብራራትና በሁሉ ዙሪያ ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶችን ለማጠናከር ከአዲስ አበባ እንስቶ እስከ ገጠር ከተሞች ድረስ የተሰማሩት የህዝብ ድርጅት ጊዜያዊ ጽ/ቤት አብዮታውያን፣ የየካቲት 66 የፖለቲካ ት/ቤት መምህራን፣ የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ ወዘተ ከንዑስ ከበርቴው ደርግ ሳንሱርና ቁጥጥር ዉጭ ዲሞክራሲያዊ ዉይይቶችን በማካሄድ የዘመናት ፀረ-አብዮት አመጽ ሊፈቱ የማይችለው ነፃት አስገኝተዋል፡፡

እንግዲህ ሰፊው የኢት. ህዝብ በአብዮታውያን ግንባር ቀደሞች አማካይነት ዲሞክራሲን ከሥራ ላይ እያዋለ በነዚህ ሁለት ዓመታት ያደረጋቸው የወደፊት እርምጃዎች እጅግ ከፍተኛ ነበሩ፡፡ ወሳኞቹን ንዑስ ከበርቴ ደርግ እስበርግገው ወደ ፀረ-አብዮት ሠፈር ያሻገሩት፣ ተኝ አድርባዮችና የዲሞክራሲን ጥያቄ እንደጦር እንዲፈሩና እንዲክዱ ያደረጋቸው ሰፊው ህዝብና አብዮታውያን ግንባር ቀደሞች በነዚህ መብቶቻቸው ተጠቅመው እጅግ ወደፊት ስለተራመዱ ነበር፡፡ እንደዚሁም በመሆኑ ይህንን የዲሞክራሲ ጥያቄ ''የየካቲት ምሁራን ጥያቄ''አድርገው ለማቅረብ ቢፈልጉ ከራሳቸው በስተቀር ማንንም አላታለሉም፡፡ ሰፊው የኢት. ህዝብ በሚሊዮን እየተቆጠረ በዚህ በዲሞክራሲ ጥያቄ ባንዲራ ስርና ከሱም ጋር በተያያዘው በፀረ-ቢሮክራሲ ትግል የተሰማራው በነዚህ አመታት ዲሞክራሲን ከሥራ ላይ እያዋለ ያገኛቸውን ድሎች መሠረት ለማስያዝ ቢል ነው ፡፡

ይህ የዲሞክራሲ ጥያቄ በመላ ኢትዮጵያ ታላቁን ህዝባዊ ሥልጣን ለመንከባከብ የተረበ የአብዮት ጥያቄ ከመሆኑ በላይ የብሔረሰቦች ችግር ባላባቸው አካባቢያች ደግሞ የተጨቆኑን የነፍጠኞች ቢሮክራሲ ለመስበርና ለብሄረሰቦች ችግር መፍትሄ ለመስጠት ይችል የነበረ ባይነባዊ ጥያቄ ነበር፡፡ አሁንም ነው፡፡ እዚህም ላይ እንግዲህ ወሳቀዮችና አድርባዮችን ለት ተቀን ከሚያታዝዛቸው ''የካቲት ምሁራን''አልፍ ይህ የዲሞክራሲ ጥያቄ በጠቅላላው ለዲሞክራሲዊ ስልጣናቸው ትግል ለሚያካሂዱት የኢት. ጭቁኖች በተለይና በዘመናዊ ደግሞ የራባቸውን እዉል በረሃቸው ለመወበን ለሚታገሉ የኢት. ጭቁን ብሄረሰቦች የሞት የሽረት ጥያቄ ሆኖ ቀርቧል፡፡ የዚህ ጥያቄ ጋያልነት፣ የዚህ ጥያቄ አብዮታዊነት እዚህ ላይ ነው፡፡

ከዚህ በዘመናዊ ይህንን የዲሞክራሲ ጥያቄ ግንባር ቀደም አብዮታውያን በሃገራቸውና በአብዮታቸው ጉዳይ ሃሳብ ለሃሳብ ለመለዋወጥ እንዲችሉ፣ ልዩነቶቻቸውን እየፈቱ ሆነ እያቻቻሉ ሃይላቸውን ለማስተባበር፣ አወናባጆችን በሃቀኛ ርዕዮተ ዓለም ትግል እያጋለጡ ለአብዮቱ ሠፈር ጥራትን ለማምጣት፣ ሃቀኛ ማርክሲስቶች ደግሞ በሃቀኛ ርዕዮተ ዓለም ትግል የሚወለደውን የወዛደር ፓርቲ ለመመስረት እንደ ህይወት አስትንፋስ ለሚያስፈልጋቸው የዲሞክራሲ መብቶች ታገለዋል፡፡ አሁንም ይታገላሉ፡፡



ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ ምሁራን፣ ተራማጅ የጦርና የፖሊስ መኮንኖች፣ ነጋዴዎች፣ ባለኢንዱስትሪዎች፣ በጠቅላላው የኢትዮጵያን ብ.ዲ.አ.ፕ. የተቀበለ ፀረ-ፊውዳል፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ኃይል ሁሉ ለአብዮቱና ለእናት አገሩ ብሔራዊ ክብርና ነፃነት አለመደፈር የሚያደርገውን ትግል ፈር ለሚያስይዝለት የዲሞክራሲ መብት ተዋድቷል፡፡ እየተዋደቀም ነው፡፡

በዚህ ዓይነት ብዙ መዘርዘር ይቻላል፡፡ ባጭሩ ግን ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት በማካሄድ ላይና በዚህም ጎዳና ላይ እስከአሁን ብዙ ድሎችን የተቀዳጀቸው እናት አገራችን የዲሞክራሲ ጥያቄ የየካቲት ምሁራን፣ የመኢሶን ታጋዮች ጥያቄ ብቻ አይደለም፡፡ የመላው ኢትዮጵያ ህዝብና የግንባር ቀደም ልጆቿ ጥያቄ ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ሃይል የሚሰጠው የሞት ኢትዮጵያውያን በሚሊዮን የሚቆጠሩ በመሆናቸው ብቻ አይደለም፡፡ ከላይ ባጭሩ እንዳሳየነው የኢትዮጵያ ጭቁኖች ባለፉት ዓመታት በመስዋዕትነት በተቀዳጁቸው ድሎች አማካይነት ዲሞክራሲ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በመረዳታቸውም ነው፡፡ ግን ይህ ብቻ አይደለም፡፡ የኢት. ጭቁኖች፣ ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች በሙሉ በዲሞክራሲ መመንመን የተነሳ የዛሬ ሶስት ዓመት ደርሶበት ከነበረው ደረጃ ያደረጉት የኋሊ ጉዞ፣ በተለይ በመኢሶን ግንባር ቀደምነት ተነስቶ የነበረው የዲሞክራሲ ጥያቄ በርግጥ ምን ያህል ለኢት. አብዮት መገፋት አንገብጋቢ እንደነበር እየተረዱ ሄደዋል፡፡ በአንፃሩ ግን ደርግ/ሰደድ ወዘ ማሌሬድ ለቅልበባ ቢራቸው ያመቻቸው ዘንድ ''ያለው ዲሞክራሲ መቼ አነሰ'' ''ዲሞክራሲ ለጭቁኖች ያለገደብ አይሰጥም'' ''የንዑስ ከበርቴ መንግሥት የጭቁኖች ዲሞክራሲ ሊሰቅ አይችልም''በማለት ፀረ-ዲሞክራሲ ትግላቸውን በማፋፋም በዚህ መልክ የትግሉ ደረጃ በሚጠይቀው ሁኔታ ዲሞክራሲ እየሰፋ መሄዱ ሲገባው እየጠበበና እየመነመነ በመሄዱ የህዝባዊት ኢትዮጵያ ህዝባዊ ሥልጣን ጥንስስ የነበሩት ህዝባዊ ድርጅቶች በቢሮክራሲው ታፍነው ጠወለጉ፣ ቀስበቀስ ጠፉ፣ በነዚህ ድርጅቶችና በጠቅላላው ለአብዮቱና ለብሔራዊ ነፃነት ትግል ግንባር ቀደም የነበሩት በመቶ የሚቆጠሩ የህዝብ ተመራጮችና አብዮታዊ ካድሬዎች በፀረ-አብዮት ሃይሎች ተረሸኑ፣ ከ20 ሺ በላይ በየእስርቤቱ ተወረወሩ፣ በቦታቸው የለየላቸው አድሃሪያኖች፣ አድርባዮችና አንዳንዴ ደግሞ በዘኒያች ጭምር በህዝቡ ባይመረጡ የህዝባዊ ድርጅቶች መሪያች እየተባሉ ተሾሙ፣ በነዚህ ፀረ-ህዝቦች ግንባር ቀደምነት በስመ ''ቀይ ሽብር''የኢትዮጵያ ሃቀኛ ወጣቶች ከአንዳንዱ ፀረ- ህዝቦች ተደምረው በፋሽስታዊ ገፍ በገፍ ተረሸኑ፣ በስመ ''ወዝአደራዊ ዓለም አቀፋዊነት''በተለይ በሠራዊቱ ዉስጥና ከሱም ዉጭ በሚገኙ ለኢትዮጵያ ክብርና ለብሔራዊ ነፃነት ተቆርቋሪ አገር ወዳዶች ላይ ከፍተኛ ጭፍጨፋ ተካሄደ፣ ''በጠባብ ብሔርተኝነት''በሰበብ በዲሞክራሲ መታፈንና በህዝባዊ ድርጅቶች መጠውለግ ተጠቅመው አድሃሪ ቢሮክራቶች እንደገና መርዘኛ ፀረ-አብዮት ዱራቸውን በሀገራችን አደሩ፣ ባጭሩ የአብዮቱ ተቃዋሚና ደጋፊ ኃይሎች እየተመኮና እየተዳከሙ የአብዮቱና የአብዮቱ ፍሬዎች ጠላቶች የሆኑት በኢትዮጵያ ምድር በ1968-69 አጥተውት የነበረውን የበላይነት መልሰው ተጎናፀፉ ፡፡

ይህንን ሁሉ በመራራ ትግሉና መሥዋዕትነቱ የተማረው ሰፊው የኢት. ህዝብ ዛሬ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ የዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥያቄ ቁልፍና አንገብጋቢ ጥያቄ መሆኑን ተረድቶት መኢሶንና ሌሎች አብዮታውያን በሚያመለክቱት የትግል ጎዳና ላይ እየተሰለፈ ነው፡፡ ይህንን በመረዳት ከቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ እንስቶ በዲሞክራሲያዊ መብቶች መፈክር ስር ተሰልፎ የተዋደቀው ማህበራችን ዛሬ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ለዲሞክራሲ የሚደረገውን ትግል ማፋፋም እንዳለበት ያምናል፡፡ በዚሁም እምነት በመመሪት፣

1ኛ. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በዲሞክራሲ መብቶ

ች ጉዳይ ያለውን ትክክለኛ አቋምና ፀረ–ህዝብ ሃይሎች በዚህ አንፃር የሚያደርጉትን ክህደት ለማጋለጥ ከፍተኛ ቅስቀሳ ያካሂዳል::

2ኛ. የዲሞክራሲ መጥፋት ከህዝባዊ ድርጅቶች መጠውለግና መፈረረስ የአድሃሪው ቢሮክራሲ መጠናከር ከተራማጆች እየታፈሱ መረሸንና መታሰር፣ ከተራማጆች ህብረት መፈረረስ፣ ከብሔረሰቦች መብት መረገጥ፣ ከብሔራዊ ክብራችንና ነፃነታችን መደፈር፣ ባጠቃላይ ከኢትዮጵያ ብ.ኢ.አ.ፓ. መቀልበስና ከፀረ–አብዮት ሃይሎች ማየል ጋር ያለውን ግንኙነት አያብራራ በነሱ ዙሪያ ሰፊ ቅስቀሳ ያካሂዳል::

3ኛ. ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለሰፊው ህዝብ ወገኖች ያለአንዳች ገደብ የሚሰውን መፈክር በሥራ ለመተርጐም ከስስት ዓመት በፊት በአብዮታዊው የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት የረቀቀውን የዲሞክራሲ መብቶች አዋጅ በሰፊው በማሳወቅና አብዮታውያን በሱ ዙሪያ እንዲታገሉ ለመቀስቀስ ባስቸኳይ ሥራ ላይ እንዲውል ይታገላል::

4ኛ. የኢ.ወ.መ. አስከዛሬ ድረስ የወሰዳቸውንና የሚወስዳቸውን ፀረ–ዲሞክራሲያዊ እርምጃዎች በጥብቅ ያወግዛል::

## 2. ስለ ብሔራዊ ነፃነት ጥያቄ

ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ለብሔራዊ ክብሩና ነፃነቱ አጅግ ቀናተኛ የሆነ ህዝብ መሆኑን በታሪክ ያጋጠሙትን ወረራዎች ሁሉ ከባድ መስዋዕትነት እየተቀበለም ቢሆን እያባረረ በመመለስ ኩሩነቱን ደጋግሞ አስመስክሯል:: በዚህ ክቡር የሆነ የታሪክ ቅርስ አጅግ የሚኮራው የዛሬው የኢት. ትውልድ የሀገሩን ነፃነትና ክብር ከሚፃረሩ ሃይሎች ጋር ሁሉ እየተፋለመ ሲታገል ቆይቷል:: አሁንም እየተፋለመ ነው::

የኢት. አብዮታውያን ለሀገራችን ክብርና ለብሔራዊ ነፃነታችን የሚደረገውን ትግል አብዮትን ከግቡ ለማድረስ ከሚያደርጉት ትግል ነጥለው አይተውት አያውቁም:: በአንፃሩ ደግሞ ፀረ–አብዮት ሃይሎች በህዝቡ ላይ የጫኑትን ወይንም ለመጫን የሚፈልጉትን የጭቆና ቀንበር ለማደላደል ሲሉ ከውጭ ወራሪዎችና ሃይሎች ጋር ከመወገን፣ ታሪኬን ከመገባት፣ የሥልጣንና የብዝበዛ ጥማቸውን ለማርካት የሀገራችንን ክብርና ነፃነት ለባዕዳን ለማስረከብ አመንትተው አያውቁም:: ከዚህም የተነሳ የኢት. ክብርና ነፃነት ከባዕዳን ወራሪዎችና ጫልታ ገቦች ለመከላከል የተደረገው ትግል ከውጭ ሃይሎች ጋር ብቻ ሳይሆን ''አክክልኝ ልክክልህ''በመባባል ከነሱ ጋር ከተባበሩ ኢትዮጵያውያንም ጭምር እንደሆነ ለመረዳት የታሪክን ገጾች መለስ ብሎ ማንበቡ ብቻ ይበቃል::

የየካቲት አብዮት ከፈነዳ ወዲህም ቢሆን የህዝቡን ወገን መርጠው የተነሱት ሃቀኛ ተራማጆች ሁሉ ለኢት. አብዮት መገሩት ያደረጉትን ትግል የዚችን ጥንታዊና ኩሩ አገራችንን ክብርና ነፃነት ለማስከበር ከሚደረገው ብሔራዊ የሀገር ፍቅር ተጋድሎ ነጥለው አይተውት አያውቁም:: እንደዚህም በመሆኑ ''አብዮት አንድ ነገር እናት አገር ሌላ ነገር'' የሚለውን ፈሊጥ ለአየሳቸው አድሃሪዎችና አድርባዮች በመተው ''አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት''በሚለው መፈክራቸው ስር በሃቅ ተሰልፈዋል:: ሃቀኛ የኢት. አብዮታውያን በብ.ኢ.አ.ፓ. ዓርማ ስር ተሰልፈው በዚች ምድር ላይ ያፈሰሱት ደም ሁሉ በዚህ በሃገር ፍቅር ስሜት የፈሰሰ ደም ነው::



እንደዚህም በመሆኑ ከአብዮታችን የማይነጠለው የብሄራዊ ነፃነታችን ጉዳይ ''ከመሬት ለአራሹ'' ''ከዲሞክራሲ'' ''ከብሔረሰቦች እኩልነት''እኩል የትግል ስንደቅ በመሆኑ በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ ተገቢ ቦታው ተሰጥቶታል:: በሌላ በኩል ደግሞ ፀረ–አብዮትና ፀረ–ህዝብ ሃይሎች ዲሞክራሲን፣ የብሔረሰቦች እኩልነትን፣ መሬት ላራሹን፣ በተቃወሙት ሃይሳቸው የሀገራችንን ክብርና ብሔራዊ ነፃነት ለዚህ ወይንም ለዚያ ሃያል መንግሥት አሳልፎ ለመስጠት ሲታገሉ ቆይተዋል:: ዛሬም ለኢት. ብሔራዊ ነፃነት አለመደፈር የሚደረገው ትግል በአብዮትና በፀረ–አብዮት ሃይሎች መሃከል የሚካሄደው ትንንቅ መሆኑ ለዚህ ነው::

ከሁለት ዓመታት ወዲህ በብ.ኢ.አ.ፓ. የተተለመው የገለልተኛ ፓሊቲካ መሸርና ኢትዮጵያ ከሶቭየት ህብረትና ከሌሎች አገሮች ጋር ማንም ሃቀኛ ኢትዮጵያዊ የሚደገፈውን የተመጣጠነ ወዳጅነት በመታረጉ፤ የተቀጥላነት ፓሊቲካ ሥር መውደቅ አብዮታውያንንና አገር ወዳጆችን ሁሉ አጅግ ያሳዘነና ያሳሰበ ጉዳይ ነው:: ከሁለት ዓመታት ወዲህ የተከሰተው ይህ አዲስ ተቀጥላነት፣ ይህ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ክብር መዋረድ በሀገሪቷ ከታየው የፀረ–አብዮት ማየል ተነጥሎ የሚታይ ነገር አይደለም:: ሊሆንም አይችልም::

የዚህን የብሔራዊ ነፃነታችንን መደፈርና የፀረ–አብዮት መጠናከር ዲያሌክቲካዊ በሆነ ዘዴ የተያያዘ ሂደት ለመረዳት ብዙም መሄድ አያስፈልገም:: የሶቭየት፣ የኩባና የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች ዐርዓታ በገፍ ለደርግ/ሰደድ ከገባና ፊደል ካስትሮ በኢት. ጉብኝት ካደረጉበት ጊዜ ወዲህ በደርግ/ሰደድ አስር ቤት የሚማቀቁት የአብዮታውያንና የአገር ወዳጆች ቁጥር አጅግ አየጨመረ መጥቶ ባሁኑ ጊዜ ወደ 20 ሺህ ተጠግቷል:: ባንፃሩ ደግሞ ወደ 20 ሺህ የሚጠጉ የኩባና የሌሎች አገሮች ወታደሮች በኢት. ምድር ሠፍረው ይገኛሉ:: በኢት. አገር ወዳጆችና አብዮታውያን ላይ የተካሄደው የደርግ፣ የአድርባይ ድርጅቶችና የአድሃሪው ቢሮክራሲ ጥቃና ከነዚህ በአብዮት ስም ከገቡ የውጭ ኃይሎች ሥር መሰደድ ጋር እየተጠናከረ መጣ እንጂ ገብ አላለም:: የደርግ/ሰደድ ከሰፊው ህዝብ እየተነጠለ መሄድ በአድሃሪው ቢሮክራሲ ቁጥጥር ውስጥ ይበልጡን እየወደቀ እንዲሄድ ያደረገውን ያህል ህልውናውን ለማረጋገጥ በውጭ ሃይሎች ላይ ይበልጡን እንዲመረኮዝ፣ ስለዚህም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ነፃነት እንዲያስደፍር አድርጓታል:: በዚህም በያዝነው ዓመት የሀገራችንን የኢኮኖሚ የፖለቲካና ወታደራዊ አቋም የሶቭየት ህብረት ተቀጥላ የሚያደርገው የ20 ዓመት ''የወዳጅነት ውል''መፈረም፣ በደቡብ ምሥራቅ እስያም /ቬየትናምና ካምቦዲያ/ ሆነ በሌላ ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ ዓይን ያወጣ የተቀጥላ አቋም መውሰድና እንዲሁም የህዝባዊት ቻይና ኮሚኒስት ፓርቲን ለማውገዝ የሚደረገው ዘመቻ፣ በተጨማሪም ካርሎስ ራፋኤል ሮድሪጌዝ የተባለው የኩባ ምክትል ሊቀመንበር በኒው ዴልሂ ከተማ በ13/7/79 በሰጠው መግለጫ ''በአንጐላና በኢትዮጵያ ምድር የሰፈሩት የኩባ ወታደሮች የሚነሱት እነዚህ አገሮች ራሳቸውን በራሳቸው ለመከላከል ሲችሉ ብቻ ነው''በማለት የተናገረው ለኢትዮጵያ አብዮታውያንና አገር ወዳጆች ብሔራዊ ክብራችንና ነፃነታችን ለመደፈሩ ማስረጃ ነው::

የብሔራዊ ነፃነታችን በኃይለ ሥላሴ ከሃዲነት በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ተደፍሮና ተረግጦ የነበረውን ያህል ዛሬ በኢት. ህዝቦች ትግል ተገደ ከኃይለ ሥላሴ መውደቅ ጋር ተጽእኖው እየተቀነሰ የመጣውን ይሸን የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምን በደርጉ ከሃዲነት ተከቶ አገራችንን በመዳፉ ውስጥ በማስገባት ብሔራዊ ክብራችንን ከላይ በጠቀስነው መንገድ መርገጥ የጀመረው ሶቭየት ህብረት ነው::

የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምን በሚመለከተው የኃይለ ሥላሴን ፊውዳል–ፋሽስት ስርዓት በመ

ርዓትና በማጠናከር፣ በኢኮኖሚ በቦሻል በፖለቲካ ሀገሪቱን ጥገኛ አድርጓት ለብዙ ዓመታት ሲበዘብዛት ቆይቷል፡፡ የኢት. ሰፊ ህዝብ ባካሄደው ረጅም ጊዜ ትግል የፊውዳሉ ሥርዓት ቁንጮ ኃይለ ሥላሴ ሲወድቅ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን መፈንቅለ መንግሥት ለማድረግ በመሞከር የኢትዮጵያን ህዝቦች ትግል ለመገታት ተፍጨርጭሯል፡፡ ሆኖም አብዮቱ እስከአየለበት ጊዜ ድረስ ይህ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ተግባር ሂደ ነበር፣ ነገር ግን ደርግ/ሰደድ ከቢሮክራሲው ጋር ባለው መመሳጠር አሁንም ቢሆን አሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በዚህ ቢሮክራሲ አማካይነት ለማንሰራራት ምቹ ሁኔታ ስላለው በዚህ በኩል አብዮታውያንና ሰፊው ህዝብ ነቅተው መጠበቅ እንዳለባቸው ማህበራችን ያምናል፡፡

ሶቭየት ህብረትን በሚመለከተው የእነዓለማየሁ ኃይሌ የተለባሸ ቡድን እስከተመታበትና ኢህአፓ በሰፊው ህዝብ በመተፋት ተስፋ የሚቆርጥበት መሆኑ እስካከተመ ድረስ በኢምፔሪያሊስቶች በአድሃሪ ጎረቤት አገሮች እየተረዳ በኢት. አብዮት ላይ ከፍተኛ ደባ ይፈጽም ከነበረ ከኢህአፓ ጋን ተሰልፏል፡፡ በኢት. ላይ ጦርነት በማንሳት የአገራችንን ብሔራዊ ነፃነትና የግዛት አንድነት የተዳፈረችውን ሶማሊያን ኢትዮጵያን ለመውረር ለ10 ዓመታት ያህል ያደረገችውን ዝግጅት በማስታጠቅና በማቀድ ረድቷል፡፡ ወረራው እንደጀመረ የኢትዮጵያን መንግሥት "በምክር" ስም በኦጋዴን ሰፍሮ የነበረውን የኢትዮጵያ ወታደር እንዲያነሳና ወደ ሰሜን እንዲዛወር በሶማሌ ወራሪ ሃይሎች በሩ ክፍት እንዲሆንላቸው አድርጓል፡፡ ሁለቱን አገሮች ጦርነት ውስጥ አስገብቶ "በአስታራቂነት" የሁለቱም የበላይ "ጓደኛ" በመሆን ሁለቱንም በቁጥጥሩ ሥር ለማዋል ባወጣው እቅድ ሶማሊያ ከሶቭየት ህብረት ጋር ያላትን ግንኙነት እስካቋረጠችበት ጊዜ ድረስ በመሣሪያና በምክር ያደረገችውን ወረራ ሲደግፍ ቆይቷል፡፡ በሶማሊያ ወራሪ ሃይሎች በአገራችን ላይ ለተፈጸመው ወረራና ለብዙ ንብረት እንዲሁም የሰው ህይወት መጥፋት ሶቭየት ህብረት ታሪክ የማይረሳው ተጠያቂነት አለበት፡፡

በዚህ መንገድ በኩባው መሪ ሶማሊያንና ኢትዮጵያን "አስታርቆ" ሁለቱንም በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ ለመያዝ ያደረገው ጥረት ሲከሽፍበት ሶቭየት ህብረት ያለ የሌለውን ኃይልና ዘዴ በመጠቀም በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ያለውን አስትራቴጂክ ቦታ ላለመልቀቅ የመጨረሻና "አስተማማኝ" ቦታ ወደ ሆነችው ኢትዮጵያ ፊቱን አዞረ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሶቭየት ህብረት ፖሊሲ "ከ3 ሚሊየን የሶማሊያ ህዝቦች በ30 ሚሊየን የኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ ማተኮር ይበልጣል" የሚል ሆነ፡፡

ሶቭየት ህብረት ለዚህ አላማው መሳካት ዋና ዘዴ አድርጎ የወሰደው የኢትዮጵያን ችግሮች በተለይም በኦጋዴንና በኤርትራ ያሉትን በማባባስ ኢትዮጵያ በጦር መሣሪያና በኢኮኖሚ በእርሱና በተከታዮቹ ላይ በማያወላውል መንገድ ጥገኛ እንድትሆን ማድረግ ነበር፡፡

"ዕርዳታን" እንደ መሣሪያ በመገልገል ሶቭየት ህብረትና ተከታዮቹ በተለይም ምሥራቅ ጀርመን ባለፉት ሁለት ዓመታት ባደረጉት ጥረት ኢትዮጵያን በኢኮኖሚና በጦር መሣሪያ ረገድ በእነርሱ መዳፍ ውስጥ እንድትገባና ጥገኛቸው እንድትሆን አድርገዋታል፡፡ በልዩ ልዩ ዕዳዎችና ውሎች በመተብተብ ከአገር ውጭም ሆነ በአገር ውስጥ ነፃ የሆነ ዕርምጃ እንዳትወስድ በእነርሱ ዞር ውስጥ እንድትሽከረከር እጅና እግሯን አስረዋታል፡፡ ይህ "በዓለም አቀፋዊነት" ስም የገባው ዕርዳታ፣ አብዮታውያንም ሆኑ ማህበራችን "ራስን በራስ መቻል" "ዕርዳታ ድጋፍ እንጂ ወሳኝ አይደለም" በሚል ያስተጋቡትን አብዮታዊ መርህ የሚፃረር ነው፡፡ ይህ "በዓለም አቀፋዊነት" በሚል ስም በገባው ዕርዳታ ደርግ/ሰደድ መተማመን ከጀመረበት አንስቶ፣ ፀረ-ህዝብ ገጽታውን እያገላ



መጥቶ "ለነቃ፣ ለተደራጀ፣ ለታጠቀ ሰፊው ህዝብ አመጽ" የሚለውን መፈክር መተኪያ እንዳደረገበት፡ ፀረ-አብዮት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ ለመምጣቱ የአሁኑ የኢትዮጵያ ሁኔታ ምስክር ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ዕርዳታ ሰጪዎቹ የደርግን ፀረ-ህዝብ አመጽ በማጠናከራቸውና አብዮቱን በማስቀልበሳቸው በታሪክ ፊት ተጠያቂ ናቸው፡፡

በኃይለ ሥላሴ ዘመን የኢት. ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ትምህርታዊ ህይወቶች በኢምፔሪያሊዝም በተለይም በአሜሪካንና በጀርመን ኢምፔሪያሊዝም እንዲሁም በእስራኤል ጽዮኒዝም ተቦርቡረውና ተቀይሰው የነበረውን ያህል ዛሬ ደግሞ በምሥራቅ አውሮፓ አገሮች በተለይም በሶቭየት ህብረትና በምሥራቅ ጀርመን እንዲሁም በኩባ እየተቦረቦሩና እየተቀየሱ ናቸው፡፡

በሶቭየት ህብረት መሪነት እነዚህ አገሮች ኢትዮጵያ የውጭ ፖሊሲዋ የሆነውን "የገለልተኛ ፖሊሲ" እንዳትከተል አድርገዋታል፡፡ የውስጥ ፖሊሲዋንም ከአብዮታዊ ወደ ፀረ-አብዮታዊ እንድትቀይር አድርገዋታል፡፡ የአሁኑን ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በ"ካፒታሊስት-አልባ የዕድገት ጎዳና" እንድትተካ አድርገዋታል፡፡ በዚህ መንገድ ጊ.ወ.መ. ለዴሞክራሲ፣ ለብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ሥራ ላይ መዋል በሚታገሉ ሃቀኛ ተራማጆች ላይ የግድያ፣ የእስራትና የክትትል እርምጃዎች እንዲወሰዱ ሁኔታዎች ከመፍጠራቸውም ሌላ እርምጃው እንዲባባስ በየደረጃው እየረዱ ናቸው፡፡ ዛሬ በኢት. ለሰፈነው የፖለቲካ ጭቆና ምክንያቶች አራማጆች ኢትዮጵያ በመዳፋቸው ውስጥ እያገባች ከመሄዷ ጋር ተያይዞ ተጽእኖአቸውን በኢት. የውስጥ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ ለመግባት ሙሉ መብት የተጎናጸፉት የፖለቲካ "አማካሪዎች" ናቸው፡፡ ዛሬ እነዚህ ኃይሎች ከደርግ አንስተው እስከ ህዝባዊ ድርጅቶች /መኢሠማ፣ መኢገማ፣ ወዘተ/ ላይ የፖለቲካ ቁጥጥር አግኝተዋል፡፡ ደርግን እንዳለ ወደ "ወዝአደር ፓርቲ" ለመለወጥም የሚደረገውን ዝግጅት በመምራት ላይ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያን ወታደራዊ ህልውና በሚመለከት በኩል የሶቭየት ህብረትና ግብረአበሮቹ አሁንም በእርዳታ ስም ሁለት ቢሊየን የሚያወጣ የጦር መሣሪያ ካጎረፉ፣ የጦር መሣሪያ አቀባይነት ሞኖፖሉን ከያዙ፣ የጦር ባለሙያተኞቻቸውን በልዩ ልዩ ወታደራዊ ክፍሎችና ማሠልጠኛ ት/ቤት ከሰገሰጉና ውላቸውን ካስፈረሙ በኋላ በኢት. ወታደራዊ ህይወት ውስጥ የበላይነትና የአዛዥነት ቦታ የሚይዙበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡ የኢትዮጵያን ወታደር በፈለጉት መንገድ ለመምራትና በፈለጉት ቦታ ለማዘመት የሚችሉ ፈላጭ ቆራጭ ሆነዋል፡፡ ለምሳሌ የምስጢር "አስትራቴጂያዊ ወታደራዊ ኮሚቴ" በተባለው የከፍተኛ የጦር መኮንኖች ቡድን ውስጥ ሰባቱ ኢትዮጵያውያን ሲሆኑ ስምንቱ ከሶቭየት ሶስቱ ደግሞ ከኩባ ናቸው፡፡ የምሥራቅ ጀርመን በበኩሏ የፖሊስንና የደህንነትን ጥበቃ ክፍሉን በቁጥጥሯ ሥር አድርጋለች፡፡

ከዚህም ሌላ እነዚህ በአማካሪ፣ በአሠልጣኝና በተዋጊ ደረጃ በአገራችን ምድር ላይ የሰፈሩት የሶቭየት ህብረትና የግብረአበሮቹ ወታደሮች በኢት. ወታደሮች ላይ የሚፈጽሙት የበላይነትና የትምክህተኝነት በደልና ወንጀል ቅኝ ገዥዎች በሚገዟቸው ህዝቦች ላይ ከሚፈጽሙት የሚለይ አይደለም፡፡ መብቱን ለማስከበር የሚታገለውንም የኢት. ወታደር ሲያስፈልጋቸው "አድሃሪ" ነው በማለት ለደርግ አሳልፎ በመስጠት እንዲረሸንና እንዲታሰር ማድረግ አለበለዚያ ደግሞ ችሎታ የለውም በማለት ከሥራ እንዲባረር አድርገዋል፡፡ እያደረጉም ናቸው፡፡ የኢት. ወታደርም በዚህ በሚፈጸምበት ደባ ሳይሸበር ከእነዚህ ትምክህተኞች ጋር ተገቢ ትንቅንቅ እያደረገ ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ እነዚህ የባእዳን ወታደሮች ጊ.ወ.መ. "ማንም እንዳይደፍራቸውና የፈለጉትን እንዲያደርጉላቸው" ያስተላለፈላቸውን ትእዛዝ በመጠቀም በሕብረተሰቡ ውስጥ የሰ

ፊውን ህዝብ ንብረት በመዝረፍ፣ የአገሪቱን ስርዓትና ወግ በመጣስ ፣ በሴቶች ላይ ልዩ ልዩ የበልግና ዉፍረቶችን በመፈጸም፣ ወዘተ የቅኝ አገዛዝ ድርጊቶችን እየተለማመዱ ናቸው፡፡ የሰፊውን ህዝብ የዕለት ተዕለት ኑሮ እስከመረበሽና እስከመፃፈር ደርሰዋል፡፡ በውጭ ሃይሎች መደፈርንና መናቅን የማይቀበለው ሰፊው የኢት. ህዝብ በዚህ የትምክህተኛ ድርጊታቸው የተሰማውን ቅሬ የጊ.ወ.መ. የጥየና መኪና ባያቆመው በየቦታው በማሰማት ላይ ነው፡፡ እነዚህ የባእዳን ወታደሮች ለሰፊው ህዝብ ጥቅም ሊውሉ የሚችሉ የመኖሪያ ቤቶችን፣ ሆስፒታሎችን፣ ሆቴሎችን፣ ማገዶን፣ የምግብና የኢንዱስትሪ ሸቀጦችን ወዘተ በመሸማት በኢት. ለተፈጠረ ኢኮኖሚያዊና ማህበረዊ ችግሮች ተጨማሪ ምክንያቶች ሆነዋል፡፡ ለእነዚህ ወታደሮች በደመወዝና በአበል መልክ የሚከፈለውን ገንዘብ በገበርና በመጫ የሚከፍለው ሰፊው ህዝብ በእነዚህ ወታደሮች በኢት. መስፈር እጅግ አድርጎ ተጉዷል፡፡

የኢትዮጵያን ትምህርታዊና ባህላዊ ህይወቶች በሚመለከት በኩል በሶቪየት ህብረት ዛሬ የኢትዮጵያን የትምህርት ካሪኩለም "በሶቪየት መንገድ ለመቀየስ" በሚል በተጣጣሩ አድርጉታል፡፡ የባህሉንም ሁኔታ አንደዚሁ በፊልሞች፣ በስነጽሑፎች፣ በእስፖርቶች፣ ወዘተ አማካይነት የአርሱ ተቀጢላ እያደረገው ነው፡፡

ኢኮኖሚውንም በሚመለከት በኩል በልዩ ልዩ በውሎችና እርዳታዎች በመተብተብና የኢትዮጵያን ብሔራዊ ፕላን በተጣጣረችው ሥር በማዋል ሁሉም ነገር በኮሚኮንና በኪፒታሊስት አልባ የዕድገት ጎዳና" አንጋጋዝ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ ለዝርዝር ሁኔታው "የኢኮኖሚና የማህበረዊ ኑሮ ጉዳይ" በሚል ርዕስ ስር የተሳለፈውን ወብነ መመልከት ነው፡፡

ባጭሩ ሶቪየት ህብረትና ገብረአበሮቿ ለኢት. የምትሰጠው "ዕርዳታ" ከአንዱ አውሃሪ ወደ ሌላው አውሃሪ እየተቀያየረ የመጣና በየጊዜው የፀረ-አብዮታውያን ሃይሎች የሚያጠናክር እንጂ ለሰፊው ህዝብና አብዮት ጥቅም የሚደረግ አይደለም፡፡ በመጀመሪያ ለኢት. አብዮት ጠላት ኢህአፓ ከዚያ በኋላ ደግሞ እነዚህ እየተዳከሙ ሲሄዱ እየተገሸረተተ ለመጣው ፀረ-አብዮታውያን፣ ፀረ-ብሔራዊ ነፃነት፣ ፀረ-ብሔረሰቡ ደርግ ተሰጠ እንጂ የሶቪየትና ገብረአበሮቿ "ዕርዳታ" ለሰፊው ህዝብና ለሃቀኛ ተራማጆች ደርሶ አያውቅም፡፡

በአሁኑ ወቅት በሶቪየትና በግብረአበሮቿ የሚሰጠው "እርዳታ" የደርግን ፀረ-አብዮታዊ ትግል የሚያጠናክር፣ አገራችንን ጥገኛ የሚያደርግና ብሔራዊ ነፃነቷ ይበልጥ እየተደፈረ እንዲሄድ የሚያደርግ፣ የብሔረሰቦችን ትግል ለመደምሰስ የሚውል፣ ሃቀኛ ተራማጆችና ሰፊው ህዝብ የሚያካሂዱትን ዕውነተኛ አብዮት ለመቀልበስ የሚያገለግል እንደሆነ ለማንም ግልጽ ነው፡፡

ዛሬ ይህንን ሃቅ በመረዳት ለዴሞክራሲ፣ ለብሔራዊ ነፃነትና ለብሔረሰብ እኩልነት በመታገላቸው የፀረ-አብዮትና የፀረ-ኢት ሃይሎች ጥቃት የወረደባቸው ተራማጆች፣ ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች ቁጥር ስፍር የላቸውም፡፡

ከሠረዊቱ አንስቶ በየሥራው መስክ የተሰማሩ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ይህንን አቋም /ማለትም የሀገራችንን ተቀጢላ መሆን መቃወም/ ሲያስተጋቡ ፣ ከውጭ ኃይሎች ጥቅም ጋራ ግጭት በተፈጠረ ቁጥር የሀገራችንን ጥቅም በማስቀደማቸው "ፀረ-አብዮት" "ፀረ-ወዝአደር ዓለም አቀፍ" "የኢምፔሪያሊስት ቡችላ" እየተባሉ በመሰቃየት ላይ ናቸው፡፡ በዚህ ሂደት ከአብዮታችን መቀልበስ ጋር ብሔራዊ ነፃነታችንም ከዕለት ዕለት እየተደፈረ እንደሚሄድ ባይታለም የተፈታ ነው፡፡ ይህንን ሂደት የሚያቆመው አንዱ ነገር ብቻ ነው፡፡ ይኸውም ዛሬ ከመቼውም ይበልጥ የአብዮታችንና የብሔራዊ ነፃነታችን ጉዳይ የተያያዙ መሆናቸውን በትክክል በመረዳት አብዮታውያን ወደተፋት አገር ወዳዶች፣ አገር ወዳዶች ደግሞ ወደ አብዮታውያን ፊታቸውን አዙረው ለማይነጣጠል ገበቻው ትግላቸውን ሲያስተባብሩ ብቻ ነው፡፡ስለሆነም ማህበራችን፣



1. በ.ሚ.ኢ.ፓ. ላይ የተተለመው የብሔራዊ ነፃነትና ከኃያላን መንግሥታት ውጭ የሚካሄደው የኢት. ገለልተኛ ፖሊሲ ከሥራ ላይ እንዲውል ይታገላል፡፡

2. ከዚህ ፕሮግራም አንፃር የሚካሄደውን ማንኛውንም መንሸራተት ከፕሮግራሙ ውጪ የሚደረገ የሀገራችንን ተቀጢላነት የሚያጠናክርና የሚያፀድቅ ማንኛውንም የፖለቲካ የኢኮኖሚ ሆነ የሚሊተሪ ውልና ቃል ኪዳን ይቃወማል፡፡ ያጋልጣልም፡፡

3. ከማንኛውም የውጭ መንግሥት ጋር በሚደረገ ውልና ድርድር የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅም እንዲቀድም ይታገላል፡፡ ለዚህም ሲታገሉ ከአውሃሪ ቢሮክራሲም ሆነ ከውጭ ሃይሎች ጥቃት የሚሠነዘርባቸውን ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ይደገፋል፡፡ ከጎናቸውም ይቆማል፡፡

4. ሶቪየት ህብረትና ገበረ አበሮቹ ፀረ-አብዮት ትግል ለሚያካሂደው፣ የኢትዮጵያን ታጋይ፣ ምሁራን፣ ወዛደሮች፣ አርሶአደሮች፣ወታደሮች፣ ወጣቶች፣ ጭቁን ብሔረሰቦች፣ ሴቶች ወዘተ እያደነ ለሚረሽነውና ለሚያሰረው ጊ.ወ.መ. የሚሰጡትን ማንኛውንም "ዕርዳታ" ፀረ-አብዮትን የሚያገዝና የሚያጠናክር በመሆኑ በፅኑ ይቃወማል፡፡

5. ሀገራችንን በወታደራዊ፣ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በባህል ተፅዕኖ ሥር በማድረግ ጥገኛ እንዲትሆን ብሔራዊ ነፃነቷን በአዲስ እንዲደፈር የሚያደርጉትን ማንኛውንም ዘገጅት አጥብቆ ይቃወማል፡፡ በሰፊው ህዝብና በዓለም ህዝቦች ፊትም ያጋልጣል፡፡

6. በኢት. ምድር ላይ በልዩ ልዩ ሰበቦች ሰፍረው የሚገኙት የባዕድ ወታደሮች በኢት. ወታደሮችና በሰፊው ህዝብ ላይ የፈፀሟቸውንና የሚፈፅሟቸውን ትምክህተኛ ወንጀሎች እንዲሁም በህብረተሰቡ ውስጥ ያስከተሉትን ኢኮኖሚያዊና ማህበረዊ ውጤቶች እያወገዘ ከኢት. ምድር እንዲለቁ ይጠይቃል፡፡ ይታገላልም፡፡

7. የብሔራዊ ነፃነታችን መደፈር ከአብዮታችን መቀልበስ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ዴሞክራቶችና ሀገር ወዳዶች ሁሉ ይህንን ተገንዝበው ለአብዮታችን አንገብጋቢ ጥያቄዎች ማለትም ለዴሞክራሲና ለብሔረ-ሰቦች እኩልነት ቆመው በፅኑ እንዲታገሉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

8. ሀገራችንን በፖለቲካ በኢኮኖሚና በሶሻል ለሶቪየት ህብረት ተቀጢላ የሚያደርጋት፣ በጊ.ወ.መ.ና በሶቪየት ህብረት መሃል ለ20 ዓመት የተፈረመው ውል እንዲፈርስ ይጠይቃል፡፡ ለዚህም ይታገላል፡፡፡

## 4. ስለ ብሔረ-ሰቦች ጥያቄ

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ብዙ ብሔረ-ሰቦች በሚገኙባትና "የህዝቦች እስር ቤት" ተብላ ትታወቅ በነበረችበት ሀገር ጭቁን ብሔረሰቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው ለመወሰንና ሙሉ መብታቸውን ለማስከበር የሚያካሂዱት ትግል ከታሪክ ሂደት ጋር የሚጣጣም ትክክለኛና አብዮታዊ ትግል ነው።

በቀድሞ አብዮት ኢትዮጵያ ይህ የብሔረሰቦች ጥያቄ ከመሬትና ከዲሞክራሲ በጠቅላላው ከኢት. ጭቁኖች ፀረ-ፊውዳልና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግል ጋር በጠበቀ ሁኔታ ተያይዞና ከዚሁ ትግል ጋር እየተጋገዘ በማደጉ የፊውዳሉ ቡርዣውን የኃይለ ሥላሴን መንግሥት መውደቅ ቀን ካቀረቡት ክስተቶች አንዱ እንደነበር የማይካድ ሃቅ ነው። በተለይ በሰሜን ኢት. የኤርትራ ጭቁን ሕዝቦች ያካሄዱት ተጋድሎ፣ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ የኦሮሞ ብሔረሰብ በባሌ፣ በኦጋዴንና በሲዳሞ ክፍለ ሃገራት የለኮሱት ትግል ለጠቅላላው ለኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች አብዮታዊ እንቅስቃሴ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል።

የየካቲት ህዝባዊ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ከፈነዳ በኋላ ይህ ብሔረሰቦች የገዛ ዕድላቸውን በራሳቸው ለመወሰን ያደረጉት ተጋድሎ ከሌሎች የአብዮቱ አንገብጋቢ ጥያቄዎች ጋር አብሮ የቀረበ ጉዳይ ሆኗል። በዚህም የተነሳ የኢት. አብዮት ትክክለኛ ፈር ይዞ ወደፊት ይገሠግሥባቸው በነበረባቸው ዓመታት ለዚህም ለብሔረሰቦች ጥያቄ ተገቢ መልስ ለማስገኘት ብዙ ጥረት ተደርጎ ነበር። ብዙ የማይናቅ ዉጤቶችም ተገኝተው ነበር። ይህ የአብዮታዊ ትግልና ትንንቅ ዘመን ለጠቅላላው የኢት. ጭቁኖችም ሆነ ለጭቁን ብሔረሰቦች እንደዚሁም በተግባር ተፈጻሚነት ለተሰለፉ ሃቀኛ አብዮታውያን ሁሉ ከፍተኛ ትምህርት የመቀሰሚያ ዘመንም እንደነበር አይካድም። በዚህ ትንንቅ ውስጥ የአብዮቱ ጠላቶች ሁሉ ዘር ሃይማኖትና ብሔረሰብ ሳይሉ በአንድነት በአብዮቱና ይህ አብዮት ባስገኛቸው ዉጤቶች ላይ ተነስተዋል። በዚህ ትንንቅ ውስጥ ጭቁን ህዝቦችና ሃቀኛ ተራማጆች የአብዮቱን ዉጤቶች ሳለማስነጠቅ ሆነ ሌሎች አዳዲስ ዉጤቶችን ለመጎናፀፍ ዘር ሃይማኖት ብሔረሰብ ሳይሉ እጅ ለእጅ ተያይዘው የጋራ ጠላቶችን እየተጋፈጡ ተሰውተዋል። ባጭሩ በነዚህ የአብዮት ችቦ እያንበገበጉ ወደፊት ይጓዙባቸው በነበረባቸው ዓመታት ሃቀኛ አብዮታውያን ያካሄዱት ፍሬያማ ተጋድሎ በመደቦች ትግልና በብሔረሰቦች ትግል መሀከል ያለው ሚዛናዊ ግንኙነት በሚገባ ተጠብቆ የአብዮቱ ምሰሶ የሆነው ሰፊ ሕዝብ ከትምክህተኝነትና ከጠባብ ብሔረተኝነት ጠንቆች ተጠብቆ ነፃነትና ዕኩልነት ወደሰፈነበት የሕዝቦች አንድነትና ክብር ወደጠነከረበትና ብሔረሰቦች ሁሉ በእኩልነት ወደአበቡባት ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊ ኢትዮጵያ መገፋቱን ቀጥሎ ነበር።

በዚህ የአብዮት ሂደት ውስጥ የመሬት ጥያቄ በየካቲት 25ቱ አብዮታዊ አዋጅ ቢፈታ በኢት. ሳለው የብሔረሰቦች ችግር አንዱ እርምጃ ወደፊት ሆኖ ቀርቦ ነበር። ከዚሁም ጋር ተያይዞ የመሬት ጥያቄ በዋናነት ቢሆን ከዲሞክራሲ ጥያቄ ጋር የተያያዘ በመሆኑ የብሔረሰቦችም ጉዳይ ከዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ ጋር እጅግ አድርጎ ለመያያዙ የኢት. አብዮት ሂደትና ዛሬ የሚታየው ተጨባጭ ሁኔታ በገልፅ አድርጎ አሳይቷል።

የኢት. አብዮት አፍላ ላይ ሆኖ ወደፊት ይገሠግሥ በነበረበት ወቅት በሌሎች መስኮች ዉል እንደተገኘ ሁሉ በዚህም በብሔረሰቦች ጥያቄም ላይ በተለይ በኢትዮጵያ ብ.ሬ.አ.ፓ. መውጣት አንዱ ትልቅ ዉል ተገኝቶ ነበር። እርግጥ ይህ ፕሮግራም በተለይ በ



ዚህ ጥያቄ ላይ የብሔረሰቦችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ካወቀ በኋላ በዚያው ውስጥ "ሪጂናል አውቶኖሚ" በሉ ገደብ ማበጀቱ አንዱ ትልቅ ጉድለት ነበር። እርግጥ ማህበራችንም ሆነ ሌሎች አብዮታውያን "የብሔረሰቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት መገንጠልንም የሚጨምር መብት" እንዲታወቅ ከወሰዱት አቋም ይህ ፕሮግራም አንዱ እርምጃ ወደኋላ ነበር። ነገር ግን ቀደም ሲል ደርግ ያስተጋባ ከነበረውና አሁንም መልቦ ከያዘው ትምክህተኛ አቋም ጋር ሲነፃፀር አንዱ የወደፊት እርምጃ በመሆኑ፣ ሁለተኛ ደግሞ ዘር ዘር የኢት. ሕዝቦች በትግላቸው ገፍተው የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ከግቡ ማድረስ የሚቻልበት ደረጃ ከደረሱ ይህ የመገንጠል ወይም ያለመገንጠል ተጨባጭ ጥያቄ ነፃ በወጡት ሕዝቦች መሃከል የሚጨረስ ጉዳይ በመሆኑ አብዮታውያን በዚህ ፕሮግራም ሥር ተሰለፉ። በዚህ ፕሮግራም ላይ የተጠቀሱት ነጥቦች ሁሉ አንቀጽ በአንቀጽ ከሥራ ላይ እንዲውሉ ከየአቅጣጫው ከሚፈሉት ትምክህተኞች ጠባብ ብሔረተኞችና ፀረ-አብዮት ኃይሎች ጋር ከፍተኛ ትግል አካሄዱ።

በብሔረሰቦች ጉዳይ ፕሮግራሙ የያዘውን ተራማጅ አቋም በመቀበል አንዳንድ ብሔረሰቦችና የብሔረሰብ እንቅስቃሴዎች /የአፋር ብሔረሰብ ነፃ አውጪ ንቅናቄ፣ የኦሮሞ ብሔረሰብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ፣ የሃድያ ከምባታ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ.. ወዘተ/ በጠቅላላው ከተቀሩት የኢት. ጭቁን ሕዝቦች ጉን ተሰልፈው ለእኩልነትና ለአብዮት ትግላቸውን ቀጠሉ። ሌሎች እንደ ኤርትራ ግንባሮች፣ የምዕራብ ሶማሊያ ነፃ አውጪ ግንባር፣ ይህን ፕሮግራም ሙሉ በሙሉ በመቃወም ከተቀሩት የኢት. ጭቁኖች ጋር ትግላቸውን ለማስተባበር ፈቃደኛ ባለመሆን የመገንጠል ትግላቸውን ቀጠሉ። ሌሎች ደግሞ የትግራይ ሕዝባዊ ነፃ አውጪ ግንባር፣ የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ወዘተ በገልፅ የመገንጠል ዓላማ ባያስቀምጡ ነገርግን ደግሞ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በይፋ ተቀብለው ከተቀሩት የኢት. ጭቁኖች ጋር ትግላቸውን ባያስተባብሩ ቀጠሉ።

ይህ በዚህ እንዳለ ዜኔያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ከአድሃሪ ቢሮክራሲው ጋር ገጥሞ የኢ.ብ.ሬ.አ.ፓ. ከዳ። በተለይ በጭቁን ብሔረሰቦች የእኩልነት ትግል የህይወት እስትንፋስ የነበረውን የዲሞክራሲ ጥያቄ በማፈንና የቀድሞው የነፍጠኞች ቢሮክራሲ እንደገና በተለይ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ ክ/አገሮች ተመልሶ የጭቆና ቡሩን እንዲያደራ በማድረጉ ለኢት. ጭቁኖች አንድነት እጅግ አስጊ የሆነ ሁኔታ ተፈጠረ። ከፀረ-አብዮት ማዕል ጋር አብሮ ትምክህተኝነት አደገ። የፀረ-አብዮት ማዕል ለተራማጅ ኃይሎች በየመልኩ አስቸጋሪ ሁኔታን ይፈጥራልና የነፍጠኞች ትምክህተኝነት ያበራታው ጠባብ ብሔርተኝነት በሀገሪቱ አንሰራራ። በየብሔረሰቡ ለሚገኙ አብዮታውያን እጅግ ጥንቃቄና ብልህነት የተሞላበት ትግል የሚጠይቅ አዲስ የፀረ-አብዮት ወቅት ተከፈተ።

ይህም ሆኖ ዛሬ የኢት.ን ጭቁን ብሔረሰቦች በአንድነት አስተባብሮ ለመብታቸውና ለኢት. አብዮት ለማሰለፍ ያለው ሁኔታ አመቺ ነው። ምንም እንኳ በፀረ-አብዮት ሂደት ትምክህተኝነትና ጠባብ ብሔረተኝነት ተያይዘው ቢያድጉም የኢት. ጭቁኖች ባለፉት አምስት የትግል ዓመታት የቀሰሙቸው አብዮታዊ ትምህርቶች በቀላሉ የሚገመቱ አይደሉም። የቀድሞ አልጋወራሽ፣ ከመንገሻ ሥዩም፣ ከሡስማን ባለህ ባቢ፣ ከአሊ ሚራህ ጋር ተሰልፍ ቢዮጋቸው የጨቋኞችን [illegible] የመደብ አንድነት ልብ ብለው ተመልከተዋል። ጓዱ ከበደ መንገሻ ከነጓዱ ደንቢ ደባበ፣ ጋር በደርግ ጥይት ተመተው ሲወድቁ፣ ጓዱ አበጉሳኒ የቡና ከነጓዱ ፍቅሬ መርዕድ፣ ከነጓዱ መኮንን ጀቴ ከነጓዱ ገብረእግዚአብሔር ሃጉስ፣ ከነጓዱ በከሪ አብደል መጅዱ ጋር አብሮ በአድሃሪያን ጥይ

ት ሰጦት የነዘሠንና የሌሎች ስፍር ቍጥር የሌላቸው ከኢት. ልዩ ልዩ ብሔረሰቦች ተውጣተው በአብዮቱ ሠፈር ብቻ ሳይሆን በመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ ባንዲራ ስር የወደቁ ጓዶች ደም በከንቱ የፈሰሰ ደም አይደለም:: የኢት. ጭቁን ብሔረሰቦችን ለአብዮቱና ለአዲስ ኑሮ በአንድነት እንዲሰለፉ መንገዱን ጠርጓል:: ስለሆነም የአብዮቱን ትግል ለመገታት ያልቻለው ፀረ-አብዮት አመጽ በታጋይ ኢትዮጵያውያን ደም የተገነባውንና ወደፊትም እየጠነከረ የሚሄደውን የትግል አንድነት በምንም ዓይነት ሊያፈርሰው አይችልም:: ከዚህ ሃቅ በመነሳት ማህበራችን ለኢት. አብዮታውያን በጠቅላላው ለጭቁን ብሔረሰቦች እንቅስቃሴዎች በተለይ የሚከተለውን አቋሙንና ጥሪውን ያቀርባል::

ዛሬ በኢት. ምድር እያገበረረ ከመጣው ፀረ-አብዮት ጋር አብሮ ትምክህተኝነትም አናቱን እያየለ እንደመጣ ገሃዱ ነው:: በዚህም የተነሳ በሰሜን ኢት. ባለው የብሔረሰቦች ችግር ምንም ዓይነት ወታደራዊ መፍትሄ የህልም እንጀራ መሆኑ እየታወቀ በብዙውን ጊዜ ሰላማዊውን ህዝብ የሚገፋ ጭፍጨፋ እየተካሄደ ይገኛል:: በመሃል አገርም በሚገኙ ልዩ ልዩ ብሔረሰቦች ላይ የሚካሄደው ጭቆናና ጭፍጨፋ እያየለ እንጂ እየበረደ አልመጣም:: በደቡብ "የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር" አባል በመባል በአደባባይ መረሸን፣ ይህ ነው የማይባሉ የጭቁን ብሔረሰቦች አባላት በየእስር ቤቱ መታጎራቸው ወዘተ ለዚሁ ለትምክህተኝነት ማደግ አይነተኛ ምልክቶች ናቸው:: ይህ ጉባዔ ይህንን የትምክህተኝነት ጭፍጨፋና እስራት በተጨማሪም በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ብሔረሰቦች እንዲሰደዱ መደረጉን እያወገዘ፣ በኢት. የሚገኙ ብሔረሰቦች ሁሉ "የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያላቸውን መብት" ያለማወላወል የሚያውቅ መሆኑን አሁንም እየገለፀ ይህ መብት እንዲታወቅ፣ እንደዚሁም የኢት. ጭቁን ብሔረሰቦች በጋራ ጠላታቸው ላይ ድልን ለመቀዳጀት የሚያስፈልጋቸውን የትግል አንድነት እንዲጠነክር የየየ ትግሉን ያፋፍማል::

1. <u>በኤርትራ ክፍለ አገር ስለአለው ሁኔታ</u>

በዚህ ክፍለ አገር ስላለው ችግር ማህበራችን ባለፈው ዓመት በሐምሌ ወር የኤርትራ ግንባሮች "ያለአንዳች ቅድመ ገደብ ውይይት እንጀምር" ብለው ያቀረቡትን ሃሳብ መደገፉን እያስታወሰ ደርግ /በደቡ ስለኢት. ጭቁን ብሔረሰቦች አንድነት ደንታ በሌላቸው የውጭ ኃይሎች እየተገዛ የሚያካሂደውን ጭፍጨፋ ይቃወማል:: ይህ "ወታደራዊ መፍትሄ ብቻ" የሚለው ትምክህተኝነት እንኳ የኤርትራን ችግር በምንም ዓይነት ሊፈታው እንደማይችል ያለውን እምነት በድጋሚ እየገለፀ፣ በሁለቱ ኃይሎች መሃል የሚደረገው ስምምነት የኤርትራንና የኢትዮጵያን ህዝቦች መሠረታዊ ጥቅም እስካልተፃረረ፣ ብሔራዊ ነፃነታችንን እስካላፈረሰ ድረስ፣ ለኤርትራ ህዝቦች ዲሞክራሲ ፍትህ እስካስገኘና ያለውጭ ኃይል ጣልቃ ገብነት እስከተፈጸመ ድረስ ማህበራችን የሚደግፈው መሆኑን ይገልፃል:: የኤርትራ ተራማጅ ኃይሎች በበኩላቸው የኤርትራ ችግር መፍትሄ የሚገኘው ከኢት. አብዮት መጎሩት ጋር ተያይዞ መሆኑን በማመን ከተቀሩት የኢት. ተራማጆች ጋር የትግል አንድነት እንዲመሠርቱ ከዚህ ቀደም ያደረገውን ጥሪ ይህ ጉባኤ እንደገና ያሳስባቸዋል::



2. <u>የኦሮሞ ብሔረሰብ ጉዳይ</u>

በያዝነው ዓመት የትምክህተኝነት ማየል ካስከተላቸው አስከፊ ውጤቶች አንዱ በኦሮሞ ብሔረሰብ ታጋዮችና ጓዶች ላይ የወረደው ጭፍጨፋ ነው:: ለኦሮሞ ብሔረሰብ ጭቁኖች የአብዮቱ መገፋት ይታይ በነበረበት ጊዜ በትግላቸው የተጎናጸፏቸው ድሎች በዲሞክራሲ መብቶች መነፈጉና በትምክህተኝነት ማየል የተነሳ ተነጥቀዋል:: በአብዮቱ ሰፈር ጠንተው በቆዩት ላይ "ጠባብ ብሔረተኛ"፣ "የኦሮሞ ነፃ አውጪ ድርጅት አባል" እየተባለ ከፍተኛ ጭፍጨፋ ተካሂዷል:: እየተካሄደም ነው:: ማህበራችን በኦሮሞ ብሔረሰብ ታጋዮችና ህዝብ ላይ የሚደረገውን ይህንን የትምክህተኝነትና የፀረ አብዮተኛ አመጽ አጥብቆ ይቃወማል:: ባስቸኳይ እንዲቆምም ይጠይቃል::

ይህንን በኦሮሞ ብሔረሰብ ላይ የሚደረገውን አሰቃቂ ጭቆና ለመቋቋም የኦሮሞ ብሔረሰብ ግንባር ቀደም ሀይሎች ሰፊውን የኦሮሞ ሕዝብ ለዲሞክራሲና ለእኩልነት በማታገል የሚያደርጉትን የማንቃት የማደራጀትና የማስታጠቅ ተግባር ማህበራችን ሙሉ በሙሉ ይደግፈዋል:: በትግላቸውም ከጎናቸው እንደሚሰለፍ ያረጋግጥላቸዋል::

በዚህ ረገድ "የኦሮሞ ነፃ አውጭ ግንባር" የተባለው ድርጅት በብሔረሰብ ላይ የሚደርሰውን ጭቆና ለመቋቋም የሚያደርገውን ትግል ይደግፋል:: ይህ ግንባር በይፋ በብሔራዊ ዲሞ. አብዮት መድረክ ላይ መሰለፉን በማስታወቅ ከሌሎች የኢት. አብዮት ኃይሎች ጋር የትግል አንድነት እንዲመሠርት ማህበራችን አብዮታዊ ጥሪ ያቀርብለታል:: እንዲሁም "የኦሮሞ ብሔረሰብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ" እስካሁን የተከተለው ግልጽ የሆነ አብዮታዊ ፖለቲካ ለኦሮሞ ብሔረሰብ እኩልነትና ዲሞክራቲክ መብቶች ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው የኢት. አብዮት ወደፊት የሚያራምድ በመሆኑ ለዚሁ ንቅናቄ ማህበራችን ከዚህ በፊት የሰጠውን ድጋፍ አሁንም ያድስለታል:: በዚህ ንቅናቄ ታጋዮች ላይ ደርግ/በደቡ የሚያደርገውን ፀረ ህዝብ አመጽ አጥብቆ ያወግዛል:: ይህ ፀረ አብዮት ድርጊት እንዲቆም ይታገላል:: ፀረ አብዮት ኃይሎችና ፀረ ጭቁን ብሄረሰብ ኃይሎች አይለው በአብዮታችን ላይ ጥቃት በማድረሳቸው በኦብዲን ላይ ድርጅታዊ መዳከም ደርሶበታል:: ማህበራችን ይህ ድርጅት፣ ድርጅታዊ መዋቅሩን አጠናክሮ የኦሮሞን ተራማጆች ሰብስቦ የብዔአኝን ፈር ሳይለቅ ተገቢ አስተዋጽኦውን እንዲያደርግ አብዮታዊ ጥሪውን ያቀርባል::

3. <u>ስለ አፋር ብሔረሰብ</u>

የአፋር ብሔረሰብ ታጋዮች ከጠባብ ብሔርተኝነት ስሜት ተላቀው ከበዝባዥ አሊሚራህ ራባቸውን ያለአንዳች ማወላወል በመለየት ለአፋር ሕዝብ እኩልነትና ለኢትዮጵያ አብዮት ተሰልፈው ሲታገሉ ብዙ መስዋዕትነት ተቀብለዋል:: ይህ በተለይ "በአፋር ብሔረሰብ ነፃ አውጪ ንቅናቄ" የተመራውና በግልጽ የፖለቲካ መስመር ላይ የተመሠረተው ትግላቸው እስከአሁን ብዙ ድሎችን አስገኝቶላቸዋል:: በብሔረሰቡ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በጠቅላላው ብሔረሰቡን የሚወክሉ 500 መልዕክተኞች በተገኙበት በ1969 ዓ.ም. በገዋኔ ከተማ የተደረገው "የአፋር ብሔረሰብ ጉባኤ" የአፋር ህዝብ በትግሉ ከተቀዳጃቸው ድሎች አንዱ ነበር:: ነገርግን እንደተፈራ የኢት. ጭቁን ብሔረሰቦችና እንደጠቅላላው የኢት. ህዝብ ከሁለት ዓመት ወዲህ ብዙ ድሎችን መነጠቅ ጀምሯል:: በተለይ በብሔራዊ ሸንጎ ላይ ጠይቆት የነበረው የክፍለ-ሃገር የአስተዳደር ነፃነት /ሪጂናል አውቶኖሚ/ ጉዳይ እንኳ መልስ ሊያገኝ ቀርቶ መሠረታዊ የሆኑት መብቶችን በትምክህተኝነት በመነጠቅ ላይ ነው::

የአፋር ብሔረሰብ ታጋዮች የኢት. ብ.ዲ.አ.ፓ. በሚፈቅደው የሪፎርሚስ አውተኖሚ መብ
ታቸውን ከሥራ ላይ ለማዋልና የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው ለመወሰን የሚያደርጉትን ት
ግል ማህበራችን ሙሉ በሙሉ ይደግፋዋል:: እንደማንኛውም የአብዮቶ ጥያቄ ይህ የራ
ስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ሊገኝና ሊረጋገጥ የሚችለው የኢት. ጭቁን ህዝቦች
በሙሉ ኃይላቸውን አስተባብረው ሲታገሉ ስለሆነ የአፋር ብሔረሰብ ታጋዮች ከተቀሩት
የኢት. ተራማጆች ጋር የትግል አንድነታቸውን እንዲያጠነክሩ ይህ ጉባኤ አብዮታዊ ጥ
ሪ ያደርግላቸዋል::

4. <u>ስለ ትግራይ ብሔረሰብ ጉዳይ</u>

የትግራይ ብሔረሰብ ከየካቲት በፊትና በኋላ ለኢት. አብዮት ይህ ነው የማይባል አስ
ተዋጽኦ ያደረጉ ታጋዮች ያፈራ ብሔረሰብ ነው:: በዚህ ብሔረሰብ ላይ ያለው ድርብ
ጭቆና በጠቀሳሳው በኢት. ለነፃነትና ለእኩልነት ከሚደረገው ትግል ጋር ያለው ዲያሌ
ክቲካዊ አንድነት ጠንቀቀው በመረዳት ስፍር ቁጥር የሌላቸው ጓዶች በአንድ በኩል አ
ገደመንገሽ ሥዩምና ተከታዮች ካሉ የትግራይ ህዝብና የኢት. ህዝብ ጠላቶች በሌላ በ
ኩል ደግሞ እንደ ኢህአፓ ዓይነት ፀረ-አብዮት ኃይሎችን በየግንባሩ ሲዋጉ ከባዱ ፈ
ተናና መስዋዕትነት ተቀብለዋል:: ከሁለት ዓመት ወዲህ በኢት. እያየለ የመጣው ፀ
ረ-አብዮት በሌሎች ጭቁኖች ላይ የደረሰው ጭቆናና ጥፋት በትግራይ ብሔረሰብ ላይ ደ
ርሷል:: የትግራይ ብሔረሰብ ታጋይ ጓዶች በፀረ-አብዮት ኃይሎች "ቶፓ መንገደኛ"
"ፈርጣጭ" ወዘተ እየተባሉ ታስረዋል፣ ተገርፈዋል፣ ተረሽነዋል:: በክህደተኞች
ደግሞ "ጠባብ ብሔርተኛ" እየተባሉ ይህንኑ የገፈ ፅዋ ቀምሰዋል:: ነገርግን ይህ
የፀረ-አብዮት ኃይሎችና የክህደተኞች ጭፍጨፋ የትግራይ ብሔረሰብን ታጋዮች ይበልጥ
ለትግል ጠራቸው እንጂ ትጥቃቸውን አላስፈታቸውም:: ወደፊትም ቢሆን ብዙ ታጋዮች
በብሔረሰቦች ትግልና በመደቦች ትግል መካከል ያለውን ዲያሌክቲካዊ ግንኙነት ጠንቀቀ
ው በመረዳት ነፃና እኩልነት ለሰፈነባት ኢት. ለአ.ብ.ዲ.አ.ፓ. መዋደቃቸው እንደ
ሚቀጥል እንጠራጠርም::

በትግራይ ብሔረሰብ ውስጥ ለዚህ ብሔረሰብ መብት ተደራጅቶ በመታገል ላይ የሚገኘው
የትግራይ ህዝባዊ ነፃ አውጪ ድርጅት ባለፉት ዓመታት ይህንን ጭቁን ህዝብ ለእኩልነ
ት እንዲታገል ለመቀስቀስ ከፍተኛ ትግል አካሂዷል:: ይህ ግንባር ምንም እንኳ በ
ይፋ የኢት. ብ.ዲ.አ.ፓ.ን ባይቀበልም፣ የመገንጠልን ጥያቄ ባያቀርብ ለትግራይ ብ
ሔረሰብ የእኩልነት መብት ሲታገል ቆይቷል:: በዚህ ግንባር ውስጥ ለኢ.ብ.ዲ.አ.
ፓ. የተሰለፉ እጅግ ብዙ የሆኑ ታጋይ ጓዶች እንደሚገኙ ይታመናል:: በሌላ በኩል
ደግሞ ይህ ግንባር በትግራይ ክፍለ ሀገር በሚካሄደው የትጥቅ ትግል እስከአሁን ድረ
ስ አድሃሪያቹን የመንገሸ ሥዩም "የትግሬ ነፃ አውጪ ግንባር" ተከታዮች ያለማወላወ
ል ሲዋጋ ከመቆየቱ በላይ ኢህአፓ አሰልፌአለሁ ይለው የነበረውን "ሠራዊት" ተዋግቶ
ከክፍለ ሀገሩ እንዲባረር አድርጎታል:: ህዝባዊ ነፃ አውጪ ግንባር በአካባቢው ያ
ሉትን አድሃሪ ኃይሎች ለመደምሰስ የወሰደውን ቆራጥ እርምጃ ለትግራይ ህዝብ እኩልነ
ት አሁን በማካሄድ ላይ ያለውን የትጥቅ ትግል ማህበራችን ይደግፋል::

የትግራይ ህዝብ እኩልነት ሊረጋገጥ የሚችለው በብ.ዲ.አ.ፓ. ወደፊት መገፋት ብቻ
እንደሆነ ማህበራችን ያምናል:: ይህ ፕሮግራም ከግቡ እንዲደርስ ደግሞ በኢት. የ
ሚገኙ ጭቁኖች በሙሉ የትግል ኃይላቸውን አስተባብረው መታገል አለባቸው:: ስለሆነ
ም በትግራይ ህዝባዊ ነፃ አውጪ ግንባር ውስጥም ሆነ ከዚያም ውጭ የሚገኙ የትግራይ



ብሔረሰብ ታጋዮች ለብ.ዲ.አ.ፓ. ሲታገሉ የወደቁትን ጓዶች ዓርማ አንስተው እንዲጓ
ዙ ይህ ጉባኤ አብዮታዊ ጥሪ ያደርግላቸዋል::

5. <u>ስለ ሲዳማ ብሔረሰብ ጉዳይ</u>

በቀድሞ አብዮት ኢት. እጅግ ከተረገጡት ብሔረሰቦች አንዱ የነበረው የሲዳማ ብሔረሰ
ብ ከየካቲት ወዲህ ባካሄዳቸው ትግሎች የኢት. ጭቁኖች ጋር ብዙ ድሎችን ተቀዳጅቶ
እንደነበር ይታወቃል:: የሲዳማና የአካባቢው ሌሎች ብሔረሰቦች ታጋዮች እነዚህ በ
ትግል የተገኙ ድሎች ተመልሰው እንዳይነጠቁ፣ በኢት. ብ.ዲ.አ.ፓ. ባንዲራ ስር በ
ይፋ ተሰልፈው ብዙ ትግሎች አካሂደዋል:: ከሁለት ዓመት ወዲህ የፀረ-አብዮትና የ
ክህደተኝነት አደጋ እየጠነከረ መሄዱ የዚህን ብሔረሰብ ታጋዮች ለእኩልነታቸውና ለ
ነፃነታቸው በይበልጥ ተደራጅተው መታገል እንዳለባቸው አስረድቷቸዋል:: በዚህ መሠ
ረት በተለይ ከአንድ ዓመት ተኩል ወዲህ በሲዳማ ክፍለ ሀገር ገጠሮች ህዝቡን እየቀ
ሰቀሱና እያደራጁ ትግላቸውን ወደፊት ማራመድ ችለዋል:: በአንዳንዱ በታያቸም የአ
ብዮቱን ድሎች ለመከላከል የትጥቅ ትግል እየተካሄደና ከዕለት ዕለት እየተስፋፋ በ
መሄዱ ላይ ይገኛል::

በሲዳማ ብሔረሰብና በሌሎች ጭቁን ብሔረሰቦች ባካባቢው የሚደረገው ትግል ለብዙኃ
ገብ መምታት የሚደረግ ትግል በመሆኑ ማህበራችን ይደግፋል::

ባካባቢው ያሉት ጭቁን ብሔረሰቦች የትግል አንድነታቸውን እንዲያጠናክሩ ማህበራችን
ጥሪ ያደርግላቸዋል::

6. <u>ስለ ሱማሌ ብሔረሰብ ጉዳይ</u>

የሱማሌ ብሔረሰብ በቀደመ የካቲት ኢት. እጅግ ከባድ የሆነ ጭቆና ሲወርድበት የኖረ
ብሔረሰብ ነው:: ስለሆነም የየካቲትን አብዮታዊ እንቅስቃሴና ያስከተላቸውንም ለው
ጦች በታላቅ ደስታ ተቀብሎ ነበር:: በትግሉም ውስጥ ሙሉ በሙሉ ተባብሯል:: የአ
ብዮቱ ወደፊት መገፋት፣ በብሔረሰቡ ውስጥ የነበሩትን የኃይለሥላሴ ቡችሎች ከጫንቃው
ላይ ከማውረዱም በላይ፣ በ1967 ዓ.ም. የታወጀው የመሬት ሥሪት አዋጅ ሰፊውን የ
ሱማሌ ብሔረሰብ እንደቀረው የኢት. ህዝብ ሁሉ የመሬቱ ባለቤት አደረገው:: በአብ
ዮታዊ ዘማቾችና ሃቀኛ ታጋዮች ቆራጥ ተጋድሎ ዲሞክራሲያዊ የሆኑ የገበሬ ማህበራት
በብዛት ተቋቋሙ:: ሰፊው የሱማሌ ብሔረሰብ ህዝብ ራሱን በራሱ ማስተዳደር ጀመረ::
የየካቲቱ አብዮት በዚህ አካባቢ ባለው የብሔረሰብ ጥያቄ ተገቢ መልስን መስጠት ጀ
ምሮ እንደነበር የሚያጠራጥር አይደለም::

ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ ድል ከ1969 ዓ.ም. አጋማሽ በኋላ፣ ባንዱ በኩል በውስጥ
እያየለ በመጣው ፀረ-አብዮትና ክህደተኝነት፣ በሌላ በኩል የሱማሌ መንግሥት በከፈ
ተው የወረራ ጦርነት እንዳልነበር ሆኖ ተቀለበሰ:: የሱማሌ ወረራ ይህ ነው የማይ
ባል የማቴሪያል ጥፋት ከማድረሱም በላይ፣ የኢትዮጵያን ህዝቦች አብዮት መቀልበስና
የአድሃሪያችንና የክህደተኞችን መጠናከር በማገዝ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል:: በዚሁ
አንፃር፣ የኦጋዴን አካባቢ ከሁለት ወገን ስለተመታ፣ ምናልባት ዛሬ ከሁሉ ይልቅ አ

በየቶ የተቀለበሰበት አካባቢ ነው፡፡ ከሁሉ ይልቅ ፀረ-ዴሞክራሲና ትምክህተኝነት የነገሠበት አካባቢ ነው፡፡ ከሁሉ ይልቅ ኢኮኖሚው ደቀቀ፣ ሰፊው ህዝብ በችግር የሚሰቃይበት አካባቢ ነው፡፡ በሌላው በኩል ደግሞ፣ በተራማጆች አካባቢ ባይቶር ከፍተኛ ውዥንብር የፈጠረ ሁኔታ ነው፡፡

በአ.ኢ.ተ.ማ. 19ኛ ጠቅላላ ጉባኤ፡-

1. የሶማሌ መንግሥት የፈፀመውን ወረራ ያወግዛል፡፡
2. በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የሚገኘው የሶማሌ ብሔረሰብ የራሱን ዕድል በራሱ ለመወሰን የሚያደርገውን ትግል ይደግፋል፡፡
3. ፀረ-ዴሞክራቲክና ትምክህተኛ ኃይሎች በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በሚገኘው የሶማሌ ብሔረሰብ ላይ የሚፈፅሙትን ጭቆናና ግፍ ያወግዛል፡፡
4. በኢትዮጵያ ምድር ላይ እኩልነት፣ ፍትህ፣ ዴሞክራሲ፣ ብልፅግናና ሰላም ሊሰፍኑ የሚችሉት፣ የሀገሪቱ ጭቁኖች በሙሉ ለዴሞክራሲያዊትና ህዝባዊት ኢትዮጵያ በአንድነት ሲታገሉ ስለሆነ፣ የሶማሌ ብሔረሰብ ታጋዮች ከኢትዮጵያ ህዝቦችና ሃቀኛ ታጋዮች ጋር የትግል አንድነት እንዲመሠርቱ ጥሪ ያደርግላቸዋል፡፡

7. <u>ስለ ሌሎች ብሔረሰቦች</u>

ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት የብሔረሰቦች እንቅስቃሴዎች በተጨማሪ ሌሎች ጭቁን ብሔረሰቦች በኢት. በማንሠራራት ላይ ያለውን ፀረ-አብዮትና ትምክህተኝነት ለመቋቋም እየተደራጁ ናቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥ ቀደም ሲል የተደራጀው የሀዲያ ብሔረሰብ ዴሞክራቲክ ንቅናቄ ቢገኝ ከሱ በተጨማሪ በተለይ በደቡብ ኢትዮጵያ እንደዚሁ በብሔረሰቦች ጥያቄ አካባቢ እየተሰበሰቡና እየተደራጁ ናቸው፡፡ ከፍ ብለን እንደጠቀስነው ብሔረሰቦች ለእኩልነታቸውና ለብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት መደራጀታቸውን ማህበራችን ይደግፋል፡፡ ስለሆነም ከብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ጋር ወደፊት ለመራመድ እነዚህ ልዋ ልዋ የብሔረሰብ እንቅስቃሴዎች የሚያደርጉትን ትግል ማህበራችን ይደግፋል፡፡



5. <u>ስለ ሴቶች ጥያቄ</u>

ሴቶች በፆታ የሚደርስባቸውን ጭቆና በመቃወም መነሳታቸው የየካቲቱን አብዮታዊ እንቅስቃሴ ዓይነተኛ ከሚያደርጉት መልኩ አንዱ ነው፡፡ የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮታዊ ፕሮግራም ከታወጀ ወዲህ አብዮቱ አጥቂነት ደረጃ እስከነበረበት ጊዜ ድረስ፣ ጭቁን ሴቶች ባካሄዱት ትግል አያሌ ድሎች መጎናፀፋቸው ይታወቃል፡፡ በተለይም በህዝብ ድርጅት ጊዜያዊ ጽህፈት ቤት፣ በሴቶች ጉዳይ ኮሚቴ አማካይነት ሴቶችን በቀበሌ፣ በገበሬ፣ በፋብሪካ ማደራጀት ተጀምሮ ነበር፡፡ ሆኖም ስደዱ የብዝኣኑን ከከፃ ወዲህ በታጋይ ሴቶች ላይ ከፍ ያለ ፀረ-ህዝብ አመፅ ተካሂዶባቸዋል፣ የድርጅታቸውም አመራር በቀኙ አድርባይ ሴቶች ተጥለቅልቋል፡፡ ለሴቶች መብት፣ ለዴሞክራሲ፣ ለብሔራዊ ነፃነት፣ ለእኩልነት... በጠቅላላ ለብ.ዲ.ፕ. ዓላማዎች ሥራ ላይ መዋል የታገሉ አያሌ ሴቶች ተረሸነዋል፣በብዙ ሺህ የሚቆጠሩት በየእስር ቤቱ ታጉረዋል፡፡

በአ.ኢ.ተ.ማ. 19ኛ ጠቅላላ ጉባኤ፣

1. በታጋይ ሴቶች ላይ የሚደረገውን ፀረ-ሕዝብ ዐመጽን አጥብቆ ያወግዛል፡፡ ይህ ፀረ-ህዝብ ተግባር ባስቸኳይ እንዲቆም ይጠይቃል፡፡

2. የታሰሩና ታጋይና አብዮታዊ ሴቶች ባስቸኳይ እንዲፈቱ ይጠይቃል፡፡ ለዚህም ይታገላል፡፡

3. ብሔራዊ ክብራችንና ነፃነታችንን የደፈሩ የውጭ ኃሎች በሀገራችን ሴቶች ላይ የሚፈፅሙትን ኢሰብአዊ ድፍረት አጥብቆ ያወግዛል፡፡ ይህም አሳፋሪ ድርጊት ባስቸኳይ እንዲቆም ይታገላል፡፡

## 6. ስለ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ኑሮ ጉዳይ

ፊውዳሊዝም ኢምፔሪያሊዝምና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም የኢትዮጵያን እርሻ ኢንዱስትሪ፣ ማእድን፣ ንግድና ባንክ በቁጥጥራቸው ሥር በማዋል ባካሄዱት የረጅም ዘመን አሰቃቂ ጭቆናና ብዝበዛ የምርት ኃይሎች እድገት እንዲታፈን፣ በሙሉ ኢኮኖሚያ እንዲቆረቆዝና ሰፊው ህዝብ በድንቁርና፣ በረሃብ፣ በእርዛትና በበሽታ እንዲማቀቅ አድርገውታል።

የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦችና ተራማጆችም የምርት መሣሪያዎችን ከእነዚህ ምንደኛ ጠላቶች እጅ በመንጠቅ በህዝብ ቁጥጥር ስር አውሎ የምርት ሃይሎች እንደልብ በነፃ ሊያድጉ የሚችሉበትን ሁኔታ በመፍጠር የአገሪቱን ኢኮኖሚ ለማበልጸግ፣ በሙሉ ድንቁርናን፣ ረሃብን፣ እርዛትን፣ በሽታንና ሥራ አጥነትን አስወግዶ ሰዎች የተሟላና የፈካ ኑሮ የሚኖሩባት ኢትዮጵያን ለመገንባት ለመሬት፣ ለደመወዝ፣ ለትምህርት፣ ለጤና፣ ወዘተ ለረጅም ጊዜ ሳያቋርጡ ታግለዋል። በዚህ አቅጣጫ ባደረጉት ትግል በተለይም ከየካቲት 1966 ወዲህ በታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የሚይዙ አያሌ ድሎች ተጎናጽፈዋል። ፊውዳሊስቶች፣ ኢምፔሪያሊስቶችና ቢሮክራት ካፒታሊስቶች የመሬት፣ የኢንዱስትሪ፣ የማእድን፣ የንግድና የባንክ ባለቤትነታቸውን እንዲያጡና ለምርት ሃይሎች እድገት በሙሉ ለኑሮአቸው መሻሻል የተወሰነ አመቺ ሁኔታ እንዲፈጠር አድርገዋል።

ይሁን እንጂ እነዚህ የተገኙት ኢኮኖሚያዊ ለውጦች በምርት ሃይሎችና በአገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት በሙሉ በህዝቡ ማህበራዊ ኑሮ መሻሻል ላይ ያስከተሉት ውጤት በተጨባጭ ሲታይ ይህን ያህል የጎላ አይደለም። በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያችን ዛሬም እንደቀድሞው በኢኮኖሚ እድገቷ ወደኋላ የቀረች ናት። የኢኮኖሚያ ዋና መሠረት አሁንም እርሻ ያውም ወደኋላ የቀረ እርሻ ነው። 90 % የሚሆነው የኢት. ህዝብ አሁንም የሚተዳደረው ከእርሻ በሚገኘ ምርት ላይ ነው። የአገሪቱ ጠቅላላ አመታዊ ምርት 50 % እና የአገሪቱ የውጭ ንግድ 95 % የሚሆነው ምርት የሚገኘው ከዚሁ ወደኋላ ከቀረው እርሻ ነው።

ለዚህ ለአገራችን ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ለሆነው እርሻ ወደኋላ መቅረት አይነተኛው ምክንያት ጥቂት የመሬት ከበርቴዎች ለብዙ አመታት መሬትን በቁጥጥራቸው ስር በማድረግ በአምራቹ ሃይል በአርሶ–አደሩ ላይ አሰቃቂ ጭቆናና ብዝበዛ በመፈጸም የምርት ማምረቻ መገልገያዎችን የማሻሻል ፍላጎቱንና ችሎታውን አፍነውት ስለነበር ነው።

ሰፊው አርሶአደር ለረጅም ጊዜ ባካሄደው መራራ ትግሉ በየካቲት 1967 ዓ.ም. መሬትን ከባላባቶች ቢነጥቅምና የምርት ማምረቻ መሣሪያዎችን እያሻሻለና አዳዲሶችን እየፈጠረ ምርቱን ለማሳደግ አዲስ መንፈስና አመቺ ሁኔታ ቢፈጠርም በአጭር ጊዜ ውስጥ የብዙ ዘመናት ወደኋላ መቅረትን ሊወጣና የተጠበቀውን ያህል ምርት ሊያሳድግ አልቻለም። ከዚህም ሌላ ከአብዮታዊው የመሬት አዋጅ ጋር የሚስማማ አብዮታዊ የፖለቲካ ለውጥ ባለመደረጉና በጊ.ወ.መ. ወሳኝነት የተነሳ የመሬት አዋጁ አጥጋቢ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ አልዋለም። ጊ.ወ.መ. የመሬት ክፍፍሉ እንዲቆም ከማዘዙም በላይ አርሶአደሮች የምርት መሣሪያዎቻቸውን እያሻሻሉ አዳዲሶች እየፈጠሩና እየገዙ ምርታቸውን ለማሳደግ ይችሉ ዘንድ አስፈላጊውን እርዳታ ለማድረግ በተጨባጭ የወሰደው እርምጃ የለም።

ኢንዱስትሪዎች በገጠር ካለመስፋፋታቸው የተነሳ አርሶአደሮች ለእለት ተእለት ኑሮአቸው የሚያስፈልጋቸውን ሸቀጦች ለማግኘት አለመቻላቸው ብቻ ባይሆን ከቀለብ የሚተርፋቸውን እህልም እንዳይሸጡና ይበልጥ እንዳያመርቱ አድርጓቸዋል። የጊ.ወ.መ. ፀረ–



ዲሞክራሲያዊነት፣ ወሳኝነት፣ አርሶአደሮችን እያስገደደ ወታደር ማድረግ፣ በልዩ ልዩ ሰበቦች ግብሮችንና መዋጮዎችን ማስከፈል፣ የኢንዱስትሪ ሸቀጦች ዋጋ እየጨመረና የእርሻ ሸቀጦች ዋጋ እየቀነሰ እንዲሄድ ማድረግ አርሶአደሮችን ከድካማቸው ትርፍ እንዳያገኙና ተስፋ እንዲቆርጡ አድርጓቸዋል።

በነዚህና በሌሎች ምክንያቶች የተነሳ የእህል ምርት ከመሬት አዋጁ ወዲህ ከ1968 የምርት ዘመን በስተቀር በየአመቱ እየቀነሰ መጥቷል። የህዝቡ ቁጥር በ2.8 % እያደገ ሲመጣ የእህል ምርት በ1.4 % ተገቧል። ባለፉት ሁለት ዓመታት በአገሪቱ በጠቅላላው በተለይም በከተማው ክፍል የደረሰው ጠቅላላ የሆነ የምግብ ሸቀጥ እጥረት ምክንያቱ በልዩ ልዩ ችግሮች ይህ የእህል ምርት እድገት ከሰዎች ቁጥርና ፍላጎት እድገት ጋር ተመጣጥኖ አለማደጉ ነው።

ጊ.ወ.መ. የከተማው በተለይም የአዲስ አበባ ሠርቶ አደር ህዝብ የእለት ዳቦ በማጣት "በዳቦ" ረሀብ ሲሰቃይ ወይንም ዳቦ ለማግኘት በየዳቦቤቱ በር ላይ 12 ሰዓት ሲቆምና አንዳንዴ አገኝቶ አብዛኛው ጊዜ ደግሞ ባያገኝ ሲመለስ፣ በጦርነትና በድርቅ ምክንያት የሐረርጌ፣ የኤርትራ፣ የትግራይና የወሎ ህዝቦች በይፋ ተርበው እንደቅጠል ሲረገፉ እያወቀ ኃይለ ሥላሴ የወሎ ረሀብ ያስከተለውን እልቂት ለመደበቅ እንደሞከረው አገሪቱ በጥጋብ እንደተጥለቀለቀች አድርጎ ለማቅረብ ለረጅም ጊዜ ጥሯል።

ይሁን እንጂ መደበቁ የትም እንደማያደርሰው ተረድቶ በ1970 መጨረሻ ገደማ በተለይም በመስከረም ሁለት 1971 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ በኢት. ጠቅላላ የኢኮኖሚ ቀውስ መኖሩን በይፋ ካሳወቀ በኋላ "ከሶሻሊስት ኢኮኖሚ ለመገንባትና የህዝቡን ጊዜያዊ ችግሮች ለመፍታት" "የአረንጓዴ ዘመቻ" ማካሄድ ጀምሯል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ "በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሶሻሊስት ህብረተሰብ ለመመስረት" በሚል "የአርሶአደሮች የአምራቾች የህብረት ሥራ ማህበር" ለማቋቋም መመሪያ አውጥቷል።

ከኢት. ተጨባጭ ሁኔታ ተነስተን ስንመለከተው ሁለቱም "ዘመቻዎች" ሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉና አርሶአደሩን ምርቱን እንዲያሳድግ የሚያበረታቱና የሚረዱ ሆነው አናገኛቸውም። እንዲያውም አሉታ ውጤት ያስከትላሉ። ጊ.ወ.መ. ከሰፊው ህዝብ ጠላቶችን በተሰለፈበትና የሰፊውን ህዝብ ጥቅሞች የሚፃረር ሃይል ሆኖ በወጣበት፣ "የዘመቻዎቹ" የበላይ አስፈፃሚ አድሃሪው ቢሮክራሲ በሆነበት፣ የሰፊው ህዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶች በተነፈጉበትና የሰፊው ህዝብ አብዮታዊ ተሳትፎ በታፈነበት በአሁኑ ወቅት ሰፊውን ህዝብ ሊጠቅም የሚችል ምንም ዓይነት አብዮታዊ እርምጃ ከሥራ ላይ ይውላል ብሎ ለማመን ይቅርና ለመገመት እንኳ ያስቸግራል። አርሶአደሩን "ሰነፍና ጉበዝ"፣ "ነሰበቂና ጋራተኛ"፣ "ካፒታሊስትና ሶሻሊስት"፣ "አሻጥረኛና አብዮታዊ" ብሎ በመከፋፈልና "በማወዳደር" እርሻን ማሻሻልና ምርትን ማሳደግ አይቻልም። "ማቆጥቆጥ የጀመረውን ካፒታሊዝምን በእንጭጩ በመቅጨት ሶሻሊስት ኢኮኖሚን ለመገንባት" በሚል የሚያስተጋባውም ከኢት. ተጨባጭ ሁኔታ ጠርቦ የራቀ የንዑስ ከበርቴ ትምኒታዊ ምኞትም በአርሶአደሮች ዘንድ ውዥንብርንና ተስፋ መቁረጥን እንጂ ጥረትንና ጥንካሬን ፈጥሮ ምርት እንዲያሳድጉ ለማድረግ አይቻልም።

የኢንዱስትሪ ክፍሉንም ወስደን የተመለከትን እንደሆ በመንግሥት ቁጥጥር ስር መዋሉ ብቻ ብዙ አወንታዊ ውጤት እንዳላስከተለ እንረዳለን። በኢት. ያሉት ኢንዱስትሪዎች አሁንም ያው ቀላል ማለትም ለእለት ተእለት ጥቅም የሚውሉ ሸቀጦች የሚያመርቱ ናቸው። በአገሪቱ 435 ፋብሪካዎች ሲገኙ ከ30 % በላይ የሚሆኑት በኤርትራ 57 % ደግሞ በሸዋ ክፍለ ሀገሮች ይገኛሉ። ከእነዚህ በመንግሥት የተወረሱት 129 ናቸው።

የኢንዱስትሪ እድገት እጅግ በጣም ወደኋላ የቀረ ነው:: ከአገሪቱ ጠቅላላ ብሔራዊ
ምርት የሚይዘው 13 %.ብቻ ነው:: ከየካቲት አብዮት ወዲህም በኢንዱስትሪ ክፍሉ
ምንም ዓይነት መሠረታዊ መስፋፋት አልተደረገም:: ጊ.ወ.መ. ምንም ዓይነት ኢንቨ
ስትመንት ስላላደረገ የተቋቋመ አዲስ ፋብሪካ የለም::

ከድሮ ጀምረው ያሉትም ፋብሪካዎች የሚገለገሉባቸው መኪናዎች ጥንታዊና በጣም ያረጁ
በመሆናቸው የማምረት ችሎታቸው ዝቅተኛ በመሆኑ፣ በብዙ ፋብሪካዎች አያሌ መኪናዎች
እየተበላሹ በመገጣጠሚያ መጥፋት የተነሳ ሥራ ፈት በመሆናቸው፣ በጦርነት ምክንያት
በተለይ በኤርትራ ክፍለ አገር የሚገኙት ለተወሰነ ጊዜ ከሥራ ውጪ በመሆናቸው በጥሬ
ዕቃ እጥረት የተነሳ አንዳንዶቹ ለጊዜውም ሆነ ለዘለቄታ በመዘጋታቸው፣ ወዘተ የኢን
ዱስትሪ ምርት እየቀነሰ መጥቷል:: ባለፉት አመታት በአገሪቱ ለደረሰው ጠቅላላ የ
ኢንዱስትሪ ሸቀጥ እጥረትና የዋጋ መናር ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች እነዚህ ነበሩ::
አሁንም ቢሆን ምንም እንኳን ጊ.ወ.መ. "ያሉትን ኢንዱስትሪዎች በሙሉ ሃይል እንዲ
ሰሩ ለማድረግና ለማስፋፋት" መዘመት ቢጀምርም አሁን ባለንበት ማቴሪያላዊና ፖለቲካ
ዊ ሁኔታ እነዚህን ችግሮች ለማስወገድና የኢንዱስትሪ ሸቀጥ ምርትን አሳድጎ በአጭር
ጊዜ ውስጥ የህዝቡን ችግሮች ለመፍታት ከቶ አይችልም:: ምክንያቱም በአሁኑ ወቅት
በየፋብሪካው የወዝአደሩ ልሳን ታፍኗል:: በአስተዳደር ምንም ተሳትፎ ለማድረግ ዲ
ሞክራሲያዊ መብት የለውም:: ከሚያመርተው ምርትም በደመወዝ መልክ የሚደርሰው ድር
ሻ ከሸቀጦቹ ዋጋዎች መናር ጋር ሲወዳደር ለወር ቀለብ እንኳን የማይበቃ ነው::
እንዲሁም በወዝአደሩ ጫንቃ ላይ የሚጠፍር ቢሮክራሲያዊ አስተዳደር በየፋብሪካው ሰፍ
ኗል:: የወዝአደሩ የሙያ ማህበራትም ተዳክመዋል:: በእነዚህና በሌሎች ምክንያቶ
ች የወዝአደሩ የማምረትና የመፍጠር ችሎታ ተዳክሟል:: በሌላ በኩል ደግሞ በየፋብ
ሪካው የተበላሹን የማምረቻ መኪናዎች ለመተካትና አዳዲስ ፋብሪካዎች ለማቋቋም ካፒታ
ል ብቻ ባይሆን መኪናዎችን እራሳቸውን ለማግኘት ረጅም ጊዜ መጠበቅን ይጠይቃል::

የአገሪቱን የውጭ ንግድም ወስደን የተመለከትን እንደሁ ተመሳሳይ ሁኔታ እናገኛለን::
የኢት. ኢኮኖሚ መሠረቱ እርሻ እንደመሆኑ መጠን የውጭ ንግዷም ዋናው ክፍል ውጤት
በተለይም የቡና ምርት ነው:: ይህ ወደውጭ የምትልከው ሲሆን ከውጭ የምትገዛው ደ
ግሞ አብዛኛው ክፍል የኢንዱስትሪ ሸቀጥ በተለይም የጦር መሣሪያ ነው::

የንግዱ ደንበኞቿ የተወሰኑ አገሮች እንደመሆናቸው መጠን የውጭ ንግዷ ዲቨርሲፋያዊ
ስርጭት በጣም ውስን ነው:: በመሆኑም አገሪቱ በዝቅተኛ ዋጋ ለመግዛትና በከፍተኛ
ዋጋ ለመሸጥ ያላት እድል የተወሰነ ነው:: የመከራከር እድሏ በመወሰኑ የሰጧትን
መቀበልና የጠየቋትን መስጠት ብቻ ነው::

ከዚህም ሌላ ኢትዮጵያ የምትሸጣቸው ሸቀጦች ዋጋዎች በየጊዜው እየቀነሱ፣ የምትገዛቸ
ው ደግሞ እየጨመሩ በመሄዳቸው የውጭ ንግዷ ባልተመጣጠነ ልውውጥ ላይ የተመሰረተ ነ
ው:: በዚህም ምክንያት የኢት. የውጭ ንግድ ሚዛን ባለፉት አምስት ዓመታት ከአመ
ት ወደ አመት እያደገ በሚሄድ ጉድለት እየተዛባ መጥቷል:: ይኸውም የውጭ እዳዋ እ
የጨመረ እንዲሄድ አድርጓል:: አብዛኛው የውጭ ንግድ የሚሄደውም የውጭ እዳ በተለ
ይም በጦር መሣሪያ ግዥ የመጣ እዳ ለመክፈል ነው::

የአገሪቱን ኢኮኖሚ በሚመለከተው በኩል የሚታየው ሌላው ሁኔታ በአዲስ የውጭ ሃይሎች
በተለይም በሶቭየት ህብረትና በምሥራቅ ጀርመን ላይ ጥገኛ መሆን መጀመሩ ነው::

ባለፉት ዓመታት በተለይም ከ1969 ዓ.ም. አጋማሽ ጀምሮ ከሶቭየት ህብረት፣ ከምሥ



ራቅ ጀርመን ከኩባና ከሌሎች የምሥራቅ አገሮች ጋር በየወቅቱና በየደረጃው ኢትዮጵያ
ያደረገቻቸውን ውሎች ስንመለከት እነዚህ አገሮች የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በሶቭየት ህብ
ረት በሚመራው "ኮሜኮን" ስር ለማምጣትና "ዓለም አቀፋዊ የሥራ ክፍፍል" ለመስጠት
ከፍተኛ ዘገባት እንደሚያደርጉ እንረዳለን::

ኢትዮጵያ ከእነዚህ አገሮች በተለይም ከሶቭየት ህብረትና ከምሥራቅ ጀርመን ጋር የም
ታደርጋቸው ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች በጣም ፈጣን በሆነ መንገድ እያደጉ መጥተዋል::

ምንም እንኳን እስከአሁን ድረስ ኢንዱስትሪዎች ለማቋቋም ባይደርስም ለዚህ ጥሩ መን
ገዱ ሊጠርጉላቸው የሚችለውን የኢትዮጵያን ብሔራዊ ኢኮኖሚ ፕላን በምሥራቅ ጀርመን
ወኪልነት በቁጥጥራቸው ስር አድርገዋል:: የብሔራዊ ኢኮኖሚ ፕላኑን በቁጥጥር ስር
ማዋል ማለት ምን ዓይነት ኢንዱስትሪዎች እንደሚቋቋሙ፣ ምን ዓይነት የእርሻ ምርት
ላይ አተኩሮ ማድረግ እንደሚያስፈልግ፣ ሸቀጦችና የምርት ማምረቻ መኪናዎች ከየት እ
ንደሚገዙና የት እንደሚሸጡ፣ ብድሮች ከየት እንደሚጠየቁ፣ በእያንዳንዱ ክፍል ላይ
ምን ያህል ካፒታል እንደሚመደብ፣ ምን ዓይነት ባለሙያተኞች እንደሚያስፈልጉ፣ ወዘተ
ለመወሰን መብት መጠበቅ ማለት ነው:: በሌላ አነጋገር ምሥራቅ ጀርመን አሁን ባላ
ት ቦታ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በፈለገችው መንገድ ልታስኬደው ትችላለች ማለት ነው::
ዛሬ በዋናው የፕላን መስሪያ ቤትና በእየኢኮኖሚ ዘርፉ ተበታትነው የሚገኙት የምሥራ
ቅ ጀርመን የኢኮኖሚ ባለሙያተኞችና በእነርሱ በኢትዮጵያም ሆነ በምሥራቅ ጀርመን በ
መሰልጠን ላይ ያሉት ኢትዮጵያውያን ቢሮክራቶች ዘገባታቸው የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በፈ
ለጉት አቅጣጫ ለማስኬዱ ያላቸውን ዓላማ ለማረጋገጥ መሆኑ አያጠራጥርም::

ኢትዮጵያ ከነዚህ አገሮች ጋር የምታደርገው የንግድ ልውውጥ በአጭር ጊዜ ውስጥ በሚ
ያስገርም ፍጥነት አድጓል:: ከየካቲት አብዮት በፊት ወደእነዚህ አገሮች የምትልከ
ው ሸቀጥ ከውጭ ንግዷ 7 %ይይዝ ነበር:: አሁን ግን 28 %.ደርሷል:: የምትገ
ዛው ደግሞ ከ7 %.ወደ 10 % .አድጓል:: ከእነዚህ ቁጥሮች ስንመለከት እንኳን የ
ምትገዛቸውና የምትሸጣቸው ዋጋዎች ምን ያህል ያልተመጣጠኑ እንደሆኑ እንረዳለን::
ለጥቂት የኢንዱስትሪ ሸቀጥ ብዙ ጥሬ እቃ እንደሚያስፈልግ እናያለን::

እነዚህ አገሮች ለኢት. የሚሸጡላት ዕቃዎች አርጌዎችና ጥንታዊ ቢሆኑ ዋጋቸው ግን
ያለመጠን ከፍተኛ ነው:: ከእነዚህ አገሮች ኢት. የምትገዛቸው ሸቀጦች አብዛኛው
ክፍል የጦር መሣሪያ ሲሆን የምትከፍለው ደግሞ በዓይነት በተለይም በቡናና በቅባት
እህሎች ነው:: በአሁኑ ወቅት ምሥራቅ ጀርመን ከሰሜን አሜሪካ ቀጥሎ ሁለተኛዋ ት
ልቅ የኢት. ቡና ገዥ ሆናለች:: ይህንን ያልተመጣጠነ ንግድ ለማፋጠንም በሶቭየት
ህብረትና በኢት. መካከል የአየርና የባህር የግንኙነት መስመሮች ተዘርግተዋል::

ከዚህም ሌላ የኢትዮጵያን የማአድንና የእርሻ ሀብቶችን በቁጥጥራቸው ሥር ለማዋል በ
የዘርፉ ሰፊ ጥናቶችንና ምርምሮችን ማካሄድ ጀምረዋል:: አንዳንዶችንም ለመቆጣጠር
ችለዋል:: ለምሳሌ ሶቭየት ህብረት የአይሳውን የወርቅ ማእድን "በዘመናዊ መንገድ
ለማውጣት" በሚል ሰበብ ወስዷል:: የወተት ማምረቻ ኢንዱስትሪውንም ለመቆጣጠር ባ
ለው ዓላማ መሠረት ሁለት እንዲህ ዓይነት ኢንዱስትሪዎች በባህር ዳር አቋቁሟል::
ኩባም በስኳር ምርትና በከብት እርባታ በኩል ባለሙያተኞቿን አሰማርታለች:: ሌሎች
ም በየበኩላቸው እንደዚሁ የተደረገላቸውን የሥራ ክፍፍል በመከተል በኢት. ኢኮኖሚ
ልዩ ልዩ ዘርፎች ውስጥ ተሰማርተዋል::

ብድርን በሚመለከት በኩል ኢት. "በእርዳታ" ስም ከነዚህ አገሮች በዓይነትም ሆነ

በገንዘብ የምትቀበለው ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ ነው። ለጦር መሣሪያ ብቻ ኢት. ከ2 ቢሊዮን ብር በላይ የሚሆን የሶቭየት ህብረት እዳ እንዳለባት ይነገራል። አሁን በቅርቡ ደግሞ ከምሥራቅ ጀርመን 20 ሚሊዮን ብር ከሶቭየት ህብረት ደግሞ 85 ሚሊዮን ብር የሚሆን ተበድራለች።

የኢት. ኢኮኖሚ "ከኮሚኮን" ፖሊሲ መቀየሩን ከቀጠለና ኢት. ከእነዚህ አገሮች በብድርም ሆነ "ከእርዳታ" ስም የምታገኘው ፋይናንስና ሸቀጥ እየጨመረ መሄዱን ከቀጠለ የአገራችን ኢኮኖሚ በአዲስ መልክ ጥገኛ መሆኑን ይቀጥላል። ለአገራችን እድገትና ለሰፊው ህዝብ ጥቅም ባይሆን ለውጭ ሃይሎች አገልግሎት የሚውል ይሆናል።

ከኢኮኖሚው እድገት ወደኋላ መቅረት ጋር ተያይዞ የሰፊው ህዝብ ማህበራዊ ኑሮ ጉዳይም በሚያሳዝን ሁኔታ ውስጥ ይገኛል።

የእያንዳንዱ ሰው አመታዊ ገቢ /ኢንካም ፐር ካፒታል/ ቢገመት በአብዮቱ ከተገኙት ለውጦች ወዲህም 200 ብር ብቻ ነው። የአብዛኛው የወዛአደር ደመወዝ በወር አምሳ ብር ነው። የእርሻና የኢንዱስትሪ ሸቀጦች እጥረት ማዘውተርና የዋጋዎች መናር ለሰፊው ህዝብ ኑሮ መቆርቆዝ ዓይነተኛ ምክንያቶች ናቸው።

በትምህርትም የሄዱን እንደሁ ምንም እንኳን "ዘመቻውን" ተመስሶ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ አርሶአደሮችና ወዛደሮች የማንበብና የመፃፍ እውቀት ለማግኘት ቢችሉም 90 % የሚሆነው የኢት. ህዝብ አሁንም የዚህ ዓይነት ችሎታ የሌለው ነው። የት/ቤቶች በገጠር አለመስፋፋት፣ በከተሞች ያሉትም ቀጥረቸው ማነስ እያደገ የሚሄደውን የህዝቡን ቁጥርና የመማር ፍላጎት ለማሟላት አልተቻለም። የተማሪዎች በሦስት ፈረቃዎች ሁረስ እየተከፈሉ መማር የዚህ ሁኔታ ውጤት ነው። ኢ.ወ.ፓ. በዚህ በኩል የሚያወጣውን በጀት እየቀነሰ የሚሄድ ይመስላል። ለምሳሌ ለደህንነትና ለመከላከያ በ1968 ከወጪው 22 % በ1970 31% ሲያድግ ለትምህርትና ለባህል ያወጣው ከ17 % ወደ 14 % ቀንሷል።

የትራንስፖርትና የሌሎች መገናኛዎች፣ የሆስፒታሎች፣ የመኖሪያ ቤቶች፣ የማገዶ፣ የውሃ፣ ወዘተ እጥረቶች በሰፊው ህዝብ ማህበራዊ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ውድቀትን ያስከተሉ ሌሎች ችግሮች ናቸው።

ማህበራችን በኢ.ወ.ፓ. አገዛዝ ሥር የኢት. ኢኮኖሚ ለማደግና የሰፊው ህዝብ ማህበራዊ ችግሮች ለመፈታት ትልቅ እድል ይኖራቸዋል የሚል ተስፋ የለውም። እንዲያውም የተገኙት ለውጦች በዚህ አቅጣጫ ብዙ መሻሻሎችን ሊያስከትሉ ያልቻሉት ኢ.ወ.ፓ. የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ለማሳደግና የማህበራዊ ኑሮ ለማሻሻል በብ.ዲ.አ. ፕሮግራም ውስጥ የተጠቀሱትን ነጥቦች አንዱ ባንዱ ስለከዳቸው ነው።

የኢት. ኢኮኖሚ የህዝቡን ፍላጎት ሊያረካ በሚችልበት መንገድ ሊያድግና የሰፊው ህዝብ ማህበራዊ ችግሮች ለዘለቄታው በአስተማማኝ ሊፈቱ የሚችሉት የዴሞክራሲ አብዮት ግቡን መትቶ በሰፊው ህዝብ በወዛአደሩ መደብና ፓርቲ የሚመራ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሲያቋቁምና ከዚያም የወዛአደሩ አምባገነንነት ሲመሰረት ብቻ ነው። የማህበራችን እምነት ይህ ነው።

ይህ ማለት ግን ማህበራችን ጊዜያዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች መፍትሄ እንዲያገ



ኙ አይታገልም ወይንም ኢ.ወ.ፓ.ን አይጠይቅም ማለት አይደለም። በጥገናዊ ለውጦች ሳይወሰን ለአብዮቱ የወደፊት እርምጃና ለሰፊው ህዝብ ጊዜያዊ ችግሮች መፍትሄ ለሚያስገኙ ጥገናዊ ለውጦች ይታገላል።

ስለሆነም ማህበራችን፣

1. በገጠርና በከተማ መካከል የሚደረገው የንግድ ልውውጥ የተዛባ እንዳይሆንና አርሶ አደሩንና ወዛአደሩን በሚጠቅምና አንድነታቸውን በሚያጠነክር መንገድ እንዲካሄድ የዋጋ ቁጥጥር እንዲደረግ፣

2. የኢንዱስትሪና የእርሻ ሸቀጦች፣ የት/ቤቶች፣ የሆስፒታሎች፣ የመኖሪያ ቤቶች፣ የመገናኛዎች፣ የማገዶና የውሃ እጥረቶችን በገጠርም ሆነ በከተማ ለማስታገስ መንግሥት ለጦር መሣሪያ መግዣ፣ የመጠየና ተቋሞችን ለማጠናከሪያና ለልዩ ልዩ ቅንጦቶች የሚያወጣውን ወጪ ለሰፊው ህዝብ ኑሮ አስፈላጊ በሆኑት በእነዚህ ላይ የበለጠ ካፒታልና የሰው ኃይል እንዲያሰማራ፣

3. ሰፊው ህዝብ በተለይም የከተማው ሠርቶ አደር እያደገ የሚሄደውን የሸቀጦች ዋጋ ለመቋቋምና ኑሮውን ለማሸነፍ የሚያስችለው የደመወዝ ጭማሪ፣ የገበርና ለአለት ኑሮ የሚያስፈልጉ ሸቀጦች ዋጋ ቅናሽ እንዲደረጉለትና በልዩ ልዩ ዘዴዎች በመንግሥት እየተገደደ የሚከፍላቸው መዋጮዎች እንዲቀነሱለት፣

4. የመሬት አዋጁ ሰፊውን አርሶአደር በሚጠቅምና የአገሪቱን ኢኮኖሚ በሚያገለግል መንገድ ሥራ ላይ እንዲውል፣ በዚሁ አንፃር ደርግ /በደዱ በሰፈራ ስም የጦር ስልት እያስተማረና መሣሪያ እያስታጠቀ ከሰሜን ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ የሚያካሂደው ሠፈራ እንደ ኒዎምኒልክ ፖሊሲ የሚታይ ፀረ-ህዝብና ፀረ-አንድነት ሴራ ነው። ጉባዔው በዚህ መንፈስ የሚደረገውን ሠፈራ ይቃወማል። ያወግዛል።

5. ብሔራዊ የኢንዱስትሪና የንግድ ከበርቴው በተለይም ዝቅተኛው ክፍል በብ.ዲ.አ. ፕሮግራም መሠረት እየተበረታታና አስፈላጊው እርዳታ እየተሰጠው በአገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ተገቢ ቦታውን እንዲይዝ፣

6. ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ በተደረጉት ልዩ ልዩ ውሎች የተነሳ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአዲስ ሃይሎች መዳፍ ውስጥ እንዲገባ፣ ጥገኛ እንዲሆንና የአገሪቱን ባይሆን የውጭ ሃይሎችን ጥቅም በሚያሟላ መንገድ እንዲቀየስ የተደረገ መሆኑ በሰፊው ህዝብ ዘንድ እንዲታወቅ፣

7. ሰፊው ህዝብ የማምረትና የመፍጠር ችሎታውን እያሻሻለ ምርቱን በየዘርፉ እንዲያሳድግና በአገሪቱ ኢኮኖሚ ህይወት ውስጥ በልዩ ልዩ ደረጃዎች /በቁጥጥር፣ በአስተዳደር፣ ወዘተ/ ተሳትፎ እንዲኖረው ዴሞክራሲያዊ መብቶች ያለገደብ ባስቸኳይ እንዲለቀቁለት ይታገላል።

8. ማህበራችን በአገራችን ኢኮኖሚ እድገትና ለሰፊው ህዝብ ኑሮ መሻሻል ሲታገል የቆየና የሚታገልም በመሆኑ ኢ.ወ.ፓ. የሚያካሂደውን "የምርት ዘመቻ" የሰፊው ህዝብ ትግል ውጤት አድርጎ ይመለከተዋል። አገሪቱ ከገባችበት ጠቅላላ የኢኮኖሚ ቀውስና በሰፊው ህዝብ ላይ ከደረሰው የማህበራዊ ኑሮ ውድቀት አንፃር ሲታይ

''ዘመቻው'' ጊዜያዊና አስፈላጊ ነው::

ይሁን እንጂ፣ ደርግ/በደዱ በፀረ-አብዮት ጎን በተሰለፈበት፣ የበላይ ሥራ አስፈፃሚው አድሃሪው ቢሮክራሲ በሆነበት፣ በዲሞክራሲ መብቶች አለመከበር የተነሳ የሰፊው ህዝብ ተሳትፎ በታፈነበት በአሁኑ ወቅት የሚደረገው ዘመቻ ጠርቦ ሥራ ላይ ሊውል የሚችል አይደለም:: ጊ.ወ.መ. አሁን ከሚያደርገው ተደላደሉ የመገዛት ዘገጅት አንፃር ሲታይም የሰፊውን ህዝብ ጥያቄ በአጭሩና በባዶ ልፈፋ ለማስታገስ የተደረገ ሽንገላ ነው ለማለት ይቻላል:: በሌላ አነጋገር የደርግ/በደዱ ''የምርት ዘመቻ'' ከማታለያነት አያልፍም::

የኢት. ህዝብ ከደረሰበት የእድገት ደረጃ አንፃር ስንመለከተው ደግሞ የደርግ ''የምርት ዘመቻ'' ከተጨባጭ ሁኔታ የራቀ የንዑስ ከበርቴ ተምኔታዊ ምኞት ሆኖ እናገኘዋለን:: ኢትዮጵያ ገና ከፊል ፊውዳል ከፊል ከበርቴ በሆነችበት፣ የዲሞክራሲያዊ አብዮት ገና ፍፃሜ ባልደረሰበት፣ የወዝአደሩ ፓርቲ በሌለበትና የወዝአደሩ አምባገነንነት ባልተመሠረተበት በአሁኑ ወቅት ''ካፒታሊዝምን በአንዴው ለመቅበርና ሶሻሊዝምን ለመገንባት'' የሚደረገው መፍጨርጨር ውዥንብር የሚነዛ፣ ትጥቅ የሚያስፈታና ከትግል የሚያዘናጋ እንጂ ለኢት. አብዮት እርምጃ ኢኮኖሚ እድገትና ለሰፊው ህዝብ ኑሮ መሻሻል የሚያበረክተው ነገር አይኖርም:: ከብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ውጭ የሚደረግ ነው:: በመሆኑም ማህበራችን በሰፊው ህዝብ ፊት ያጋልጠዋል::

9. ማህበራችን የአርሶ አደሮችን የህብረት ሥራ ማህበራት እንዲቋቋሙ የሚታገልና የሚደግፍ ቢሆንም ይኸን እርምጃ በማንኛውም ሁኔታና ጊዜ አይደግፍም:: የአርሶአደሮች የህብረት ሥራ ማህበራት ደረጃ በደረጃ፣ በአርሶአደሮች ፈቃደኝነት፣ ከብዙ የፖለቲካና የሙያ ትምህርት እንዲሁም ከብዙ ማሳያ መከራያች በኋላ አስፈላጊ ሁኔታዎች ሲሟሉና ጥያቄው የራሱ የአርሶአደሩ መሆን ሲጀምር በአብዮታዊ አመራር ሥር የሚቋቋሙ እንጂ በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ በአዋጁ አንደዳብዳ የሚባል ነገር አይደለም::

በአሁኑ ወቅት በኢት. በዚህ መንገዱ የአርሶአደሮች የህብረት ሥራ ማህበራት ለማቋቋም የማቴሪያላው ሆነ የፖለቲካ ሁኔታዎች አይፈቅዱም:: አርሶአደሩ የፖለቲካ ትምህርት በበቂ አልተሰጠውም:: አርሶአደሩ አወንታ ውጤት ያበቁ የሠርቶ ማሳያ መከራያች አላየም:: እንዲያውም ከመሬት አዋጁ ጋር ተያይዞ ከተቋቋሙት ''የህብረት እርሻዎች'' ያገኘው ትምህርት አሉታ ነው:: ሙሉ ተሳትፎ ለማድረግ የሚያስችለው ዲሞክራሲ መብት የለውም:: ከዚህም ሌላ በራሱ ማቴሪያላዊ ተጨባጭ ሁኔታ የህብረት እርሻዎችን ለእድገቱ አማራጭ አድርጎ ሊወስድና ጥያቄው ሊያደርገ የሚችልበት ደረጃ ላይ አልደረሰም::

ስለሆነም፣ ተጨባጩ ሁኔታ ይህ ሆኖ ''ኮሚኒስት ህብረተሰብን በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ለመመስረት''በቅርቡ የወጣው የደርግ ባዶና አወናባጅ መመሪያ አርሶአደሮችን በጠመንጃ አፈሙዝ ባይወዱ በግድ ለጊ.ወ.መ. አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉበት መንገድ ለማደራጀት እንጂ ምርትን ለማሳደግና ኑሮአቸውን ለማሻሻል የሚደረግ አለመሆኑን ማህበራችን ያጋልጣል::



## ክ ፍ ል 2

### 7. ስለ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት

ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ንዑስ ከበርቴ መንግሥት እንደመሆኑ መጠን ከተቋቋመበት ወቅት አንስቶ የዚህን መደብ ወላዋይ ጠባይ በሚገባ ሲያንፀባርቅ የቆይቷል:: ከዚህም በላይ ተራማጆች ደጋግመው እንዳሳሰቡት በዚሁ በመደባዊ ጠባዩ የተነሳ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ከግቡ ሊያደርስ የሚችል ሃይል አልነበረም:: ይህንንም በተለይ ከ1969 ዓ.ም. ወዲህ ባሳየው ያልተቋረጠ ፀረ-ህዝብ ተግባራቱ በሚገባ አረጋግጧል::

ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት በህዝብ ግፊት አንዳንድ ተራማጅ እርምጃዎችን ለመውሰድ ቢገደድም ቅሉ፣ በዚያው መጠን ደግሞ በአድሃሪ ሃይሎች በተለይ በአድሃሪው ቢሮክራሲ ቁጥጥር ሥር በወደቀ ቁጥር በኢት. አብዮት ላይ ታሪክ የማይረሳቸው ጥፋቶችን አድርሷል:: አሁንም እያደረሰ ነው::

በታህሳስ ወር 1969 ዓ.ም. እነዓለማየሁ ሥልጣን ከጨበጠበት ወቅት አንስቶ /ምናልባት አብዮቱ በአጥቂነት ደረጃ ከነበረባቸው ከጥር-መጋቢት 1969 ዓ.ም. በስተቀር/ ጊ.ወ.መ. በፀረ-አብዮት ሠፈር እየተረጋጋ ሄዷል:: በዚሁም ልክ ደግሞ ተራማጅነቱንም ሆነ አገር ወዳድነቱን እያጣ፣ በውስጥ የአድሃሪው ቢሮክራሲ መሣሪያ በውጭ ደግሞ የባዕድ ኃይሎች ቅጥ መንግሥት የሆነበት አሳፋሪ ደረጃ ላይ ደርሷል::

የኢት. አብዮታዊና አገር ወዳድ ሃይሎች በመጀመሪያ በነዓለማየሁና ተፈሪ ባንቲ ክሊክ መሪነት ደርግ ከአድሃሪው ቢሮክራሲ የገጠመበትን የመጀመሪያውን የቀኝ ሃይሎች ህብረት ሙሉ በሙሉ ተቃውመው ተዋግተውታል:: ከመጋቢት 1969 ዓ.ም. በኋላም ይኸው የነዓለማየሁ ፖለቲካ በሰደዱ/ደርግና በአድሃሪው የሲቪልና የሚሊተሪ ቢሮክራሲ አማካይነት ሲያንሰራራ እነዚህ የቀኝ ሃይሎች ህብረት በኢት. ህዝብ ትከሻ ላይ ሲጫን ተራማጆችና ሰፊው ህዝብ ይህንን ሁኔታ አሜን ብለው አልተቀበሉትም:: ምንም እንኳን ዛሬ በጥቅም በሸጡት የአብዮት ሠፈር ሙሉ በሙሉ ተተፍተው ወደታሪክ ትቢያነት የወረዱት የቀኝ አድርባይ ድርጅቶች በጊዜው ''ደርግ አሁንም ተራማጅ ነው'' የሚል አቋም ይዘው ህዝቡን ለማደናገር ቢሞክሩም ሃቀኛ አብዮታውያን የዚህን የደርግ መንሸራተት አደጋ መዝነው በወቅቱ ሊዋጉትና ሊያጋልጡት ተነስተው፣ እስከአሁንም በመዋደቅ ላይ ይገኛሉ::

ሶቭየት ህብረትና ገብረአበሮቿ ወደ ኢትዮጵያ በእርዳታ ስም መግባት ሃቀኞች እንደጠበቁት የዚህን የደርግ መንሸራተት አገዘታል::

ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ጋር ህብረቱን ባጠናከረ መጠን በህዝቡ እየተተፋ፣ በህዝቡ እየታለፈ፣አብዮታዊነቱ እያከተመ፣ ከኢት. አብዮት እንገብጋቢ ጥያቄዎች አንዱንም መመለስ እየተሳነው ከውጥረት ውስጥ እየገባ በዚህም ሁሉ የተነሳ የህዝቡን ተቃውሞ እያስነሳ በመሄድ ላይ ነው:: ይህንንም ተቃውሞ በፀረ-ህዝብ እመቃ ለማውደም በሚወስዳቸው እርምጃዎች ደግሞ በቢሮክራሲው ቁጥጥር ውስጥ ይበልጥ ለመውደቅ ይገደዳል:: በሶቭየት ህብረትና በሌሎች የውጭ ሃይሎች መመካቱም ሌላ

ራሱን የቻለ አደገኛ አዙሪት ውስጥ ይከተዋል እንጂ የኢት. አብዮትም ሆነ ብሔራዊ ክብሯ ለሚያተርፏቸው ጥያቄዎች ለአንዴም መልስ ሊያስገኙለት አይችሉም። በመጀመሪያ የሀገሪቱን የውጭ ጦር ኃይሎች መሰፈሪያ መሆን፣ የፖለቲካ፣የኢኮኖሚና፣ የማህበራዊ ህልውናዋ ገበና ለውጭ ኃይሎች መጋለጡና የሀገሪቱ የውጭ ኃይሎች ተቀጣሪነት የተደነቀ የሀገር ፍቅር ታሪክ ላለው የኢት. ህዝብ እጅግ አስከፊ የሆነ ሁኔታን መፍጠሩን በገሐድ የምናየው ነገር ነው። በዚህም የተነሳ ይህ የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የውጭ ኃይሎች ቅጥር መንግሥት እየሆነ መሄድ አብዮታዊና አገር ወዳድ የሆኑ ኃይሎችን ይበልጡን እያስነሳበት ይሄዳል። እነዚህን ኃይሎች ለመደምሰስ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ጥይቶችን ጥቅምና ክብር ለጥቂቶች ስልጣን ጥም ለጠማ ጥቅሙን ለማረጋገጥ ያነጠጠው ደርግ በለየለት ፀረ-ህዝብ አመጽ ከመሰማራት ሌላ አማራጭ አይኖረውም።

ተራማጆችና አገር ወዳድ ኃይሎች በሙሉ ከዚህ የአደሃሪ ቢሮክራሲ መሣሪያና የውጭ ሃይሎች ቅጥር ከሆነው ጊ.ወ.መ. ጋር እየከረረ በሚሄድ ቅራኔ ውስጥ ወድቀዋል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት ጊ.ወ.መ. ሥልጣኑን ለማደላደል በመመኘት ብቻ በታሪክ ፊት የሚያስጠይቁትን ብዙ ፀረ-አብዮት፣ ፀረ-ኢትዮጵያ ክብር እርምጃዎች ወስዷል። በውስጥ ሰፊው የኢት. ህዝብና መላው ህዝባዊና መደበኛው ሠራዊት ቃል ኪዳን የገባለትን የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም አንቀጽ በአንቀጽ ሸርሯል። ይህንን ክህደት የተቃወሙትን፣ ለኢት. ብሔራዊ ክብርና አብዮት የሚታገሉትን ስፍርና ቁጥር የሌላቸው የኢትዮጵያ አርሶ አደሮችና ወዝአደሮች፣ መለዮ ለባሾችና ወጣቶች፣ ምሁራንና አገር ወዳድ የጦርና የፖሊስ መኮንኖች፣ ታጋይ ሴቶችና የጭቁን ብሔረሰቦች ግንባር ቀደሞች፣ ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶችን ረሽኗል፣ አስረሽኗል። ስፍር ቁጥር የሌላቸው በእስርቤት አጉሯል፣ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን አገር ጥለው እንዲሄዱና የስደት መከራን እንዲቀምሱ አድርጓል። በወሰደው ፀረ-ምሁር እርምጃ የተነሳ ታጋይና አገር ወዳድ ምሁራን ወደሀገር እንዳይመለሱ "ፋካሪ ቡድኖች" እያላከ የማስፈራራት ቅስቀሳ አካሂዷል፣ በኢት. ብሔረሰቦች መሃከል መፈጠር ጀምሮ የነበረውን የትግል አንድነትና መተባበር የሥልጣን ጥሙን ለማርካት ብቻ በማሰብ ትምክህተኝነት እንዲነግሥ ዓይነተኛ መሣሪያ ሆኗል፣ በስንት ሃቀኞች ደም የተገነቡትን ህዝባዊ ድርጅቶች ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ጋር በማበር ካፈረረሰ በኋላ በቦታቸው ተራ ወታደራዊ ሹምሽር በማድረግ አድርባዮችን ተክቶ በኢት. አብዮት ላይ ይህ ነው የማይባል በደል ፈጽሟል።

በውጪም እንደዚሁ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በመክዳት በሺና በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ጥይቶች ለአገራቸዉ ለመታገልና ለመሞት ትጥቅ እየጠየቁ ባለ እነሱን ባለማመን ከነሱ ይልቅ የውጭ ወታደሮች ለኢትዮጵያ ይበልጥ ይታገሉ ይመስል ባዕድ ወታደሮችን አስገብቶ ብሔራዊ ክብራችንን አጉድፏል። "የወዳጅነት ውል ተፈቀለኩ" በሚል ሰበብ የኢትዮጵያን የጦር የፖለቲካ የባህል አውታሮች ከውጭ ቁጥጥር ሥር እንዲውሉ አድርጓል። የውጭ ኃይሎች ተቀጣሪነቱን በማስመስከር በዓለም አቀፍ ጥያቄዎች ላይ ከኢት. ጥቅም ውጭ ለብሔራዊ ነፃነቱ መደፈር ምልክት የሚሆኑ ተቀጣሪ እርምጃዎች ወስዷል።

ደርግ/ስደድ ይህንን ሁሉ እያደረገ ሥልጣኑን ለማደላደል ከምንም ፀረ-አብዮት ድርጊት እንደማይመለስ ባለፉት ሁለት ዓመታት በሚገባ አሳይቷል። ወደህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚወስደው ጉዳና በገልጽ በብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ላይ በክፍል 4 አንቀጽ 1 ላይ "ሰፊው ህዝብ ተደራጅቶና ገፍቶ አብዮታዊ ህዝባዊ ግንባሩ እንደ



ተቋቋመ በትግሉ ውስጥ የተባበሩት የግንባሩ አባል ፓርቲዎችና የፖለቲካ ድርጅቶች ከሚያቀርቧቸው ምልምሎች መሃከል ህዝቡ በሙሉ ነፃና ምስጢራዊ በሆነ ምርጫ እንደራሴያችን መርጦ የመንግሥቱን ከፍተኛ ሥልጣን ወደሚይዘው አብዮታዊ ህዝባዊ ሸንጎ ይልካል። የህዝብ ወኪሎች አጥንተው ባጸደቁት ህገ መንግሥት መሠረት የመንግሥቱን መዋቅሮች ዘርፎችና የሥልጣን ክፍፍሎች ተወስነው በወዝ አደሩ ፓርቲ መሪነት ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚቋቋም" ይላል።

ይሁን እንጂ፣ ደርግ/ስደድ የራሱንና የአጋሪውን አድሃሪ ቢሮክራሲ ድርጅት "የወዝ አደር ፓርቲ" በማለት፣ ሌሎች ፓርቲዎች እንዳይደራጁና ህዝባዊ አብዮታዊ ግንባር እንዳይፈጠር ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በማፈን ጊዜያዊ ሥልጣኑን ወደቋሚነት ለመለወጥ ሽር ጉድ በማለት ላይ ይገኛል።

ይህንን ሁሉ በመመልከት ማህበራችን ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ ደርግ የተከተለውን ፀረ-አብዮት ሂደት ከመረመረና በመጪው ጊዜ ይህ ደርግና አድሃሪው ቢሮክራሲ ሥልጣናቸውን በማደላደል በኢት. አብዮት ላይ የሚጠነስሱትን ሴራ በመገንዘብ ማህበራችን ለጊ.ወ.መ. በ15ኛው ጠቅላላ ጉባዔው ሰጥቶት የነበረውን "ሂሳዊ ድጋፍ" በዚህ በ19ኛው ጉባዔው ማንሳቱን በይፋ ያስታውቃል።

ተራማጆች የከበርቴ መደብ ሰፊውን ህዝብ በአብዮታዊ መንፈስ ለማስተማርና ለማደራጀት እስከፈቀደላቸው ድረስ ከእርሱ ጋር "ጊዜያዊ ህብረት" ፈጥረው መስራት አለባቸው። በአብዮታዊ መንገድ ከመሠረት ሲያገዳቸው ግን ሊያጋልጡትና ሊታገሉት ይገባቸዋል። ማህበራችን ይህንን ትክክለኛ አብዮታዊ መርህ በመከተል የኢት. ተራማጆች ሰፊውን ህዝብ በአብዮታዊ መንገድ እንዲያነቁና እንዲያደራጁ በህዝብ ትግል ተገዶ ለጊዜውም ቢሆን አመቺ ሁኔታዎችን ለፈጠረው ጊ.ወ.መ. "ሂሳዊ ድጋፍ" ሰጥቶ ቆይቷል። በዚህ ፖሊሲውም ጊ.ወ.መ. በአንድ በኩል አድሃሪ እርምጃዎች እንዳይወስድ ሲታገልና በወሰደ ቁጥርም ሲያወግዘው ቆይቷል። በሌላ በኩል ደግሞ ተራማጅ እርምጃዎች እንዲወስድ ሲታገልና በወሰደ ቁጥርም ሲደግፈው ቆይቷል። ይሁን እንጂ አብዮቱ እያደገ ሲመጣ፣ በተለይ ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ ጊ.ወ.መ. ተራማጅነቱ እያሟጠጠና አድሃሪነቱ እየጠነከረ በመሄዱ የኢት. ተራማጆች ሰፊውን ህዝብ ነፃና አብዮታዊ በሆነ መንገድ ሊያነቁና ሊያደራጁ የሚችሉባቸው ሁኔታዎች ሁሉ በኃይሉ አፍኗል። እንዲያውም በትግላቸው ያነቋቸውና ያደራጇቸው ህዝባዊ ድርጅቶችን በማፈራረስ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ታጋይ የህዝባዊ ድርጅት ተጠሪዎች አስሯል፣ረሽኗል። ባጭሩ ጊ.ወ.መ. ዛሬ የፀረ-አብዮትና የፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች መሣሪያ ሆኗል።

1ኛ ማህበራችን በጠቅላላ ከኢት. ማሌያዎች ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች ጋር በመሆን ባለፉት ዓመታት ደርግ የወሰዳቸውን ፀረ-አብዮትና ፀረ-ብሔራዊ ክብር ድርጊቶች በሙሉ ያለአንዳች ማወላወል ያወግዛል።

2ኛ ከጠቅላላው ከኢት. ማርክሲስቶች ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች ጋር በመሆን ከደርግ/ስደድ ባሻገር ለሚቋቋመው ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት አስፈላጊ የሆኑትን የንቃት የድርጅትና የትጥቅ መበሳሎች ለመዘርጋት ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋል።

3ኛ አብዮቱን ከድቶ ወደ ፀረ-አብዮትና ፀረ-ኢት. ኃይሎች የተደባለቀው ደ

ርግ በየጊዜው ከብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም አንፃር የሚያደርገውን ክህደት በኢት. ጭቁን ህዝቦች ፊትና በዓለም ተራማጆች ፊት ለማጋለጥ ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋል::

4ኛ የወጣቶችን አብዮታዊ ንቅናቄ በሚመለከተው በኩል በስሙ ቀይ ሽብር በኢት. ወጣቶች ላይ ያወረደውን ጭፍን ጭፍጨፋ፣ በውጭ የተማሪዎች አብዮታዊ እንቅስቃሴ ለመከፋፈል በቡችሎቹና በአንዳንድ ተባባሪ መንግሥታት በኩል የሚጠነስሰውን ሴራ በሙሉ ያወግዛል::

## ክፍል 3

## 8. ስለ የወዛደር ፓርቲና የኢማሌድህ ጥያቄ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ግቡን እንዲመታ በጠቅላላው በሀገሪቱ የሚገኙ ፀረ-ፊውዳል ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ሃይሎችን አስተባብሮ የሚመራ ሃቀኛ የወዛደር ፓርቲ አስፈላጊ መሆኑ ተደጋግሞ ተነግሯል:: በተለይ ባለፉት አምስት ዓመታት ይህ የወዛደር ፓርቲ እንዲመሠረት ሀቀኛ የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ከፍተኛ ትግል አካሂደዋል:: የወዛደሩ ፓርቲ በጠቅላላው የሠርቶ አደሩን ህዝብ አብዮታዊ ትግል አስተባብሮ የመምራት ሃላፊነት ያለበት በመሆኑ ለዚህ ታሪካዊ ተልእኮው ብቁ የሚያደርጉት ዓይነተኛ ጠባዮች አሉት::

የወዛደሩ ፓርቲ ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ጠንቅቀው በሚያውቁ ትክክለኛ የመደብ ትንተና ሊያደርጉ የሚችሉና የህብረተሰብ እድገት ህጋጋትን እንዲሁ ጠንቅቀው የሚያውቁ ወዛደሮችንና ምሁራንን እንዲሁም ሌሎች ግለሰቦችን የሚይዝ የነቃውና ከፍተኛው የወዛደሩ መደብ አካል ነው:: ይህ ግንባር ቀደም ድርጅት ከወዛደሩ ልዩ ልዩ ድርጅቶች ሁሉ ከፍተኛውና የነዚህን ሁሉ ትግል አቀነባብሮ የመምራት ሃላፊነት ያለበት ድርጅት ነው::

ሃቀኛ የኢት. ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ባለፉት ዓመታት ሲታገሉና ሲጥሩ የቆዩት እንዲህ ዓይነቱን ፓርቲ ለመመሥረት ነው:: እንደዚህ ዓይነቱን ፓርቲ ለመመሥረትም አብዮታዊ ምሁራን የሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን ቲዎሪ ይዘው ወደ ወዛደሩ መሄድና ከሰፊው የሞያ እንቅስቃሴ ጋር በግንባር ቀደምነት መዋሃዳቸው አስፈላጊ መሆኑን ስለአመነበት በአለፉት አምስት ዓመታት በዚህ አቅጣጫ ከፍተኛ ትግል ተካሂዷል::

የወዛደሩን ፓርቲ ለመመሥረት ከዚህ መደብ መዋሃድ ብቻ ሳይሆን ለዚህ ፓርቲ መፈጠር የሚታገሉ ልዩ ልዩ ቡድኖችን ማስተባበርና ማዋሃድ እንደሚያስፈልግም ተደጋግሞ የተነገረ ሃቅ ነው:: በዚህም በኩል በኢትዮጵያ የነበሩት ልዩ ልዩ ማርክሲስት ሌኒኒስት ቡድኖች በአንድ የጋራ መድረክ ላይ ተሰብስበው ህብረት እንዲፈጥሩ ከዚያም በ



መሃከላቸው ሃቀኛ የርዕዮተዓለም ትግል አካሂደው ወደ ውህደት እንዲሸጋገሩ ብዙ መስዋዕትነት የጠየቀ ትግል ተካሂዶ እነዚህ ልዩ ልዩ ቡድኖች የመተባበሪያቸው የጋራ መድረክ የሆነውን መጋቢት 1969 ዓ.ም. የጋራ መርሃ ግብር አውጥተው እንደነበር የሚታወስ ነው::

ባለፉት ሁለት ዓመታት በፀረ-አብዮት ማዕበል የተነሳ በነዚህ በሁለት መስኮች ማለት በወዛደሩ መደብ መዋሃድና ከማሌ ድርጅቶች ከህብረት ወደ ውህደት መሸጋገር ሂደት ላይ ብዙ መሰናክሎች ተፈጥረዋል:: በመጀመሪያ ደረጃ በወዛደሩ ውስጥ ሆነው ይታገሉ የነበሩ አብዮታዊ ምሁራንና ግንባር ቀደም ወዛደሮች ከፍተኛ ጭፍጨፋ፣ እስራትና ርሸና ስለወረደባቸው የመደራጀት ጥረታቸውን በጥብቅ ህቡዕነትና በዝግታ ለማካሄድ ተገደዋል:: ሁለተኛ ደግሞ የማሌ ቡድኖች ከህብረት ወደ ውህደት መሸጋገር በሚመለከተው ጉዳይ የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄና ኢጭአት ለመጋቢቱ መርሃ ግብር ታማኝነታቸውን አጥብቀው ሲይዙ ሌሎች በተለይ ሰደድ ወዝና ማሌሪድ እንኳን የማርክሲስቶን መርሃ ግብር ቀርቶ ዝቅተኛውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምን ማክበር አቅቷቸው ወደ ታሪክ አተላነት ዘቅጠው ቀርተዋል:: በዚህም የተነሳ እነዚህ ድርጅቶች ከፖለቲካ ክስረታቸው፣ ከሰፊው ህዝብ ከመተፋታቸው ጋር ተያይዞ የድርጅት ክስረት ደርሶባቸዋል:: በኢማሌድህ ውስጥ ተስፋፍቶ በመጣው የሰደድ አምባገነንነት የዴሞክራሲያዊ ውይይቶችን በማፈንና የጉልበት ፖለቲካን በመከተል የሌሎችን ድርጅቶች ህልውና በመናድ ይህ ህብረት የሚባለው በስም እንጂ በይዘት የሰደድ መሣሪያ እንደነበረ ይታወቃል:: ኢማሌድህ የሚባለው ማርክሲስት ሌኒኒስት መሆኑ ካከተመለት በኋላ "የድርጅቶች ህብረት" የተባለበትም አነጋገር ቀርቶ ከህብረት ወደ ክስረት ተሸጋግሯል:: ተበታትኗል:: ባጭሩ ወደ ወዛደር ፓርቲ መፈጠር የሚደረገው ጉዞ በአድሃሪዎች ማዕበልና በአድርባዮች ክህደት የተነሳ ዛሬ ሂደቱ በመጠኑም ቢሆን ተገትቶ ይታያል::

በዚህ አንፃር ደግሞ የአድሃሪዎችና የንዑስ ከበርቴ አድርባዮች የሚጥበረበር መከራ በኢትዮጵያ የወዛደር ፓርቲው መፈጠሪያ ቀን የተቃረበ አስመስሉ ለማሳመን እየተፍጨረጨረ ነው:: ለብዙ ጊዜ "ኢማሌድህ ከህብረት ወደ ውህደት በማሸጋገር" የወዛደር ፓርቲ እንፈጥራለን እያሉ ያሸቃብጡ የነበሩ ንዑስ ከበርቴ አድርባዮች ዛሬ እንቡረባቸው ባጠናከሩት ቢሮክራሲ እንዲፈረፈሩ ከታዘዙ በኋላ አሁንም ለዚሁ ቢሮክራሲ ፊታውራሪዎች በመሆን "የወዛደሩን ፓርቲ ከግለሰብ ኮሚኒስቶች ህብረት እንመሠርታለን" የሚል ፈሊጥ አምጥተዋል:: ይህ አዲስ መፈክር ንዑስ ከበርቴ አድርባዮች ሀገራችንን ለፀረ-አብዮት ሃይሎች ከመታቹ በኋላ ረባቸው በለየላቸው አድሃሪዎች ተጠራርገው ወደ ታሪክ ትብያነት ለመወርወር የተቃረቡ መሆናቸውን እንጂ ወደ ኢትዮጵያ ወዛደሮች ፓርቲ መፈጠር መቃረባችንን የሚያሳይ መፈክር አይደለም::

በመሠረቱ የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ሃይሎች ከመኢሶን ዙሪያ ያሉትም ሆነ በአድርባይ ድርጅቶችም ውስጥ የነበሩት ሃቀኛ ማርክሲስቶች ዛሬ እየተረሸኑ፣ በየእስር ቤቱ እየታጎሩና በህቡዕ መራራውን ትግል እያካሄዱ ናቸው:: የወዛደሩ ፓርቲ ገዳማም ሆነ ምሰሶ የሚሆኑት በሺ የሚቆጠሩ ግንባር ቀደም ወዛደሮች እንደዚሁ ተረሽነዋል፣ ተሰደዋል:: የወዛደሩንም ፓርቲ ከንዑስ ከበርቴው ደርግ ቁጥጥር ውጭ ለመመሥረት ብዙ መስዋዕትነት የሚጠይቅ ትግል በህቡዕ እያካሄዱ ናቸው:: ሃቀኛ የኢትዮጵያ ወዛደሮች ፓርቲ በማርክሲስቶችና በግንባር ቀደም ወዛደሮች አባልነት እንጂ ንዑስ ከበርቴውና አድሃሪው ቢሮክራሲ እንደሚያውናብዱት በአብዮቱና በአብዮት ሃይሎች ላይ በመጡ ፀረ-ህዝቦች አይመሠረትም::

አሁንም በሆነ የኢትዮጵያን ወዝአደሮች ፓርቲ የሚመሠርተው ማርክሲስት ሌኒንስቶች በግንባር ቀደምነት ከወዝአደሩ መደብ ትግል ጋር ሲዋሃዱና የተለያዩ ማርክሲስት ሌኒንስት ሃይሎች ወይም ቡድኖች በማሃከላቸው ሃቀኛ የርዕዮተዓለም ትግል አካሂደው ሲዋሃዱ ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ የተቋቋመው ኢማሌድህ ከየካቲት 1969 ዓ.ም. የጋራ መርሃ ግብር ተንሸፈቶና አዝቅጦ ከቀረ በኋላ ከዚህ ከሳሬ ህብረት ተጸንሶ ይወጣል ተብሎ የነበረውን "የወዝአደር ፓርቲ" ማህበራችን ወርቦ አንደማይቀበለው ግልጽ ነበር። አሁንም በሆነ የባሰውን ከከሰረና በለየለት ፀረ-አብዮት መድረክ ላይ ከቆመ፣ አድርባዮች ለአድሃሪው ቢሮክራሲ ተንበርክከው ካቋቋሙት "ማዕከል" ይፈልቃል የተባለውን የወዝአደር ፓርቲ የኢትዮጵያ አብዮታውያን በምንም ዓይነት አንደማይቀበሉት ግልጽ ነው። ስለሆነም ፤

1ኛ በአድሃሪው ቢሮክራሲ የበላይነት በንዑስ ከበርቴ አድርባዮች ተባባሪነት በታጋይ ወዝአደሮች አብዮታዊ ምሁራን አስከሬን ላይ ተመስርቶ፣ በከሠረ ፀረ-ወዝአደርና ፀረ-ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መድረክ ላይ የቆመ፣ በሺ የሚቆጠሩ ወዝአደሮችንና አብዮታዊ ምሁራንን በየአስርቤቱ አጉሮ የሚቋቋመውን "የወዝአደሮች ፓርቲ" የኢትዮጵያ አብዮታውያን አይቀበሉትም፣ በሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብና በዓለም ተራማጆች ፊት ያጋልጡታል፣ ይዋጉታል።

2ኛ ቀደም ሲል በተተለመው ሳይንሣዊ የወዝአደር ፓርቲ አመሠራረት ትልም በመከተል አንደኛ በወዝአደሩ መደብ ውስጥ በይበልጥ በመግባትና በየፋብሪካው፣ በየቀበሌው፣ በየጦር ሠፈሩ፣ በየት/ቤቶችና በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ለሃቀኛ የወዝአደር ፓርቲ መመሥረት ለሚያደቅ ማንኛውም አብዮታዊ ግለሰብ ወይም ቡድን ማህበራችን ያልተቆጠበ ድጋፉን ያደርጋል።

3ኛ አድርባይ ድርጅቶች በንዑስ ከበርቴው ደርግ ፀረ-ህዝብ ትዕዛዝ ፈረሱ ከተባሉ ወዲህ የውርደት ማቅ ለብሰው ወደ ታሪክ ትቢያነት ወርደዋል። በነዚህ ድርጅቶች ውስጥ ሆነው ይታገሉ የነበሩት ሃቀኞች ከሁሉ በፊት ለአብዮቱና ለእናት አገራችን ክብር በሚቆረቆር መንፈስ ካለፈው ስህተት ተገቢውን ትምህርት መቅሰም አለባቸው። ከታሪክ አተላ መሪዎቻቸው አልፈውና የነሱን ክህደት አሻፈረን በለው ወደ አብዮቱ የተመለሱ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ታጋዮች የፈረረሰ የህቡዕ መዋቅራቸውን አንደገና መስርተው በሃቀኛው ሂደት በሃቀኛ የወዝአደር ፓርቲ መመሥረት የሚያደርጉትን ትግል አንዲቀጥሉ አብዮታዊ ጥሪ ያደርግላቸዋል።

4ኛ በተከተለው ህዝባዊና አብዮታዊ መስመር የተነሳ ይህ ነው የማይባል ግፍና ስቃይን ተቋቁሞ አሁን ለሃቀኛ የወዝአደር ፓርቲ በመዋደቅ ላይ ለሚገኘው መኢሶን ማህበራችን ያልተቆጠበ ድጋፉን ይሰጣል። በአሁኑ ወቅት ይህ ድርጅት ከአንጋፋነትም አልፎ በሀገሪቱ ውስጥ ለሃቀኛ የወዝአደር ፓርቲ መቋቋም የሚታገል ግንባር ቀደም ድርጅት ሆኖ ይታያል። ይህ ሁኔታ በመኢሶን ትከሻ ላይ የሚጥለውን ይህ ነው የማይባል ከባድ ሃላፊነት ማህበራችን አጥብቆ ይረዳዋል። ስለሆነም በዚህ ጥያቄ አስፈላጊ የሆነውን ማንኛውንም ድጋፍ ለመስጠት ማህበራችን ቃል ኪዳኑን አንደገና ያድሳል።



## 9. ስለ ህዝባዊ ድርጅቶች

ባለፉት አምስት ዓመታት የኢት. አብዮት አስገኝቷቸው ከነበሩት ዋና ዋና ድሎች አንዱ በተለይ የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ከተቋቋመ ወዲህ በድርጅት መስክ የተከናወነው ተግባር ነበር። በኢት. የአብዮት ትግል የማይናቅ መሣሪያና የዚሁ ትግል ፍሬ የሆኑት ህዝባዊ ድርጅቶች አንዲፈጠሩና አንዲያብቡ ከኢሠአፓና ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ጋር ከዚያም ደግሞ ከቀኝ አድርባይ ድርጅቶችና ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ጋር ይህ ነው የማይባል ትግል ተካሂዷል።

ባለፉት አመታት በኢት. ያበቡት ህዝባዊ ድርጅቶች ከሁሉ ሥር ሰደው የነበረበትን የ1969 ዓ.ም. አንጻሽ ሁኔታ ዛሬ ካለው ሁኔታ ጋር ስንመለከተው ፀረ-አብዮት ምን ያህል አንዳየለ መረዳት አንችላለን። ባጭሩ ግን በነዚህ ዓመታት አብበው የነበሩት ህዝባዊ ድርጅቶች ዲሞክራሲያዊ መሪያቻቸውን አጥተው፣ የቢሮክራሲው ተሿሚያች ተጭነባቸው ጠውልገዋል። አንዳንዶቹ ደግሞ በሃቀኛ የህዝብ ወገኖች ምትክ በተተከሉባቸው አድርባዮችና በዘኔ "ካድሬዎች" አመራር ሥር በቀጥታ በህዝቡ ላይ የአድሃሪውን ቢሮክራሲ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ማካሄጃ አካላት ሆነዋል።

የኢት. አብዮት ሶስት አመት ሙሉ ያለአንዳች ማቋረጥ ወደፊት አየተጓዘ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰበት 1969 ዓ.ም. ሁኔታ አንዴት ነበር?

በገጠር ከ25ሺ በላይ የገበሬ ማህበራት ሲኖሩ አነዚህ ደግሞ በ600 የወረዳ የገበሬ ማህበራት፣ አነዚህ ደግሞ በተራቸው 100 በሚሆኑ የአውራጃ የገበሬ ማህበራት ተጠቃለው ይገኙ ነበር። በይዞታቸው ከመደብ አንፃር የተመሠረቱት አነዚህ የገበሬ ማህበራት በጊዜው በነበራቸው ዲሞክራሲያዊ ስልጣን የተነሳ ከቀድሞው ሥርዓት አድሃሪ ቢሮክራሲና በጠቅላላው ከፀረ-አብዮት ሃይሎች ጋር "የአጥፊና ጠፊ" ግጭት ነበራቸው። በነዚህ ለነገዪቱ ኢትዮጵያ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሥልጣን መሠረትና ጥንስስ በነበሩት ድርጅቶችና በበሰበሰው አድሃሪ ቢሮክራሲ መካከል የተካሄደው ትግል አንዱ አንዱን ባይደመስስ የማይቆም ትንንቅ ነበር። ህዝባዊ ድርጅቶችና በነሱ ስር የሚንቀሳቀሱት ጭቁኖች ለአዲሱ ሥልጣን ጥንስስ መፋፋትና ማደግ፣ በቀድሞው ቢሮክራሲ ላይ የበላይነትን ለማግኘት ባጭሩ ለዲሞክራሲ መብቶች ሲታገሉ፣ የቀድሞው ሥርዓት ሥልጣን አውታር የሆነው አድሃሪ ቢሮክራሲ ደግሞ የራሱን የበላይነት ለማረጋገጥ ፀረ-ዲሞክራሲ ትግል ያካሄደው ለዚህ ነው። በጊዜው ለዲሞክራሲያዊ መብቶች በመኢሶን ግንባር ቀደምነት የተካሄደው ትግል አነዚህ የአዲሱ ዲሞክራሲያዊ ሥልጣን ጥንስሶች አንዲፋፉና ብሎም የቀድሞውን ሥርዓት የሥልጣን አውታሮች አንዲደመስሱ ለማስቻል ነበር።

በከተሞችም 2000 የከተማ የህብረት ሥራ ማህበራት አንደዚሁ የትግልና የአስተዳደር መሣሪያዎች ሆነው መፈጠራቸው፣ ወዝአደሩ ከረጅም ጊዜ ትግል በኋላ በታህሳስ ወር 1969 ዓ.ም. በታሪኩ የመጀመሪያው የሆነውን ዲሞክራሲያዊ የሠራተኞች ማህበር መኢሰማ የተቋቋመበት፣ ከዲሞክራሲያዊ ምልመላ በኋላ በየፋብሪካው፣ በየቀበሌው፣ በየት/ቤቱ የአብዮት ጥበቃ ኮሚቴዎች የተቋቋሙበትና ሌሎችም የህብረተሰብ ክፍሎች አየተደራጁ ትግላቸውን ያጧጧፉ የነበረበት ወቅት ነው።

በዚህ መሠረት በገጠርም ሆነ በከተማ የህዝብ ሥልጣን መሠረትና ጥንስስ የሆኑትን ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች ሲያብቡ አድሃሪ ሃይሎች አቻቸውን አጥፈው አልተቀመጡም። በመጀመሪያ በነኢሠአፓ "ግንባር ቀደምነት" በማወናበዱ ማህበራትን ለመበተንና ለማ

ባሸት ያደረጉት መብራ ሽብር በተለይ ከመስከረም 1969 ዓ.ም. በኋላ በነዚሁ ህዝባዊ ድርጅቶች፣ በመሪዎቻቸውና በአደረጃጀታቸው ላይ በለየለት አመጽ ተስፋፋ:: ዲሞክራሲያዊ አሰራራቸውን ለማፈን ለማጥፋትና ለማኮላሸት የዲሞክራሲ መብቶችን መታወቁ አስከሳከሉ:: በዚህ ሁኔታ አድሃሪያት የሚነዙትን ነጭ ሽብር ለመደቆም ትጥቅ ለአብዮት ጥበቃ ኮሚቴዎች፣ የህዝባዊ ድርጅቶችን የበላይነት ለማረጋገጥ ዲሞክራሲ ለጭቁኖች ያለገደብ በሚሉ መፈክሮች ሥር ተራማጅ ሃይሎች ሁሉ ተሰማሩ::

በጥር ወር 1969 ዓ.ም. የነዓለማየሁ ሃይሌ መደምሰስና የትጥቅና የዲሞክራሲ ጥያቄዎች መጠነኛ መልስ ማግኘት አብዮቱን መግባት ከጀመረበት ማጥ ውስጥ አውጥቶ አንደገና ሌላ አዲስ አስትንፋስ ሰጠው:: ህዝባዊ ድርጅቶች ለጊዜው ቢሆንም ተጠናከሩ:: አብዮቱ ወደፊት ገሰገሰ:: ነገርግን ይህ ገሥጋሤ ያስደነገጣቸው ነውስ ከበርቴዎችና አድሃሪያት የአብዮቱን ጊደት ለመገታትና በሌም ለመቀልበስ ርኩስ ህብረታቸውን መሠረቱ:: በዚህ ህብረት ላይ ጥቂት ባይቶዩ በሶሸየት ህብረት የሚመሩ ሀገሮች የውጭ ዱጋፍ ተጨመረበት:: የህዝባዊ ድርጅቶች ማበብ በሌም የአብዮቱ ወደፊት መገሩት ዕድል የተያዘበት የትጥቅና የዲሞክራሲ ጥያቄ የዚያኑ ያህል ወደኋላ ተተወ:: የዚያኑ ያህልም ደግሞ እየተዳከመ በመሄዱ ከህዝባዊ ድርጅቶች አንፃር አድሃሪው ቢሮክራሲ ተደናግጦ ከሚገኝበት አዘቅት ውስጥ እየወጣ ያንሰራራና ነፍስ ይዘራበት ጀመር:: የኢት. አብዮት ተሸካሚና አራማጅ ሃይሎች እየታፈኑ፣ ተባሪዎች እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ለሀገራችንና ለአብዮታችን አሥነ አሳዛኝ የታሪክ ምዕራፍ ተከፈተ::

ከዚህን ወቅት አንስቶ የታየው የአብዮቱ መዳከም ታሪክ የህዝባዊ ድርጅቶች መዳከምም ታሪክ ነው:: የፀረ-አብዮቱ መጠናከር ታሪክ የአድሃሪው ቢሮክራሲ መጠናከርና "ህዝባዊ" ይባሉ የነበሩትን ድርጅቶች በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ ለፀረ-አብዮት አላማው ሊያውላቸው የሞከረበት ታሪክ ነው:: ከዚህን ወቅት አንስቶ በገጠር፣ የአድሃሪው ቢሮክራሲና የለየላቸው አድሃሪዎች ደመኛ ጠላቶች የነበሩት ታጋይ የገበሬ መሪዎች "በቀኝ መንገደኝነት" በየአስርቤቱ እየታፈኑና በያለበት እየተረሸኑ፣ በአድሃሪው የሶማሌ መንግሥት ወረራ ምክንያት እየተበተኑ በገጠር በብዙ ኢትዮጵያውያን ነፁህ ደም የተገነቡት የገበሬ ማህበራት ፈረሱ:: ዲሞክራሲያዊ መብቶች ታፍነው በተያዙበት ሁኔታ ደርግና የውጭ ሃይሎች አንከብክበው የያዙት አድሃሪው ቢሮክራሲ ሲጠናከር ከሱጋ በምንም ዓይነት የማይታረቅ ቅራኔ ያላቸው ህዝባዊ ድርጅቶች መዳከማቸውና መፈራረሳቸው በፍፁም የሚያስገርም ነገር አይደለም::

በከተማም እንደዚሁ ነው:: በቀበሌዎች በዲሞክራሲያዊ አሰራርና በጥንቃቄ ወደፊት ለመራመድ ይሞክሩ የነበሩት የህዝብ ተመራጮችና አገልጋዮች አንድ በአንድ እየታፈኑ ታሠሩ:: በነሱ ቦታ በከተማ ፈሪው ላይ በካድሬነት ስም አደርባዮች ፀረ-አብዮተኞችና የለየላቸው በዝባዦች ሳይቀሩ በሹም ሽር ተተኩ:: በፀረ-ህዝቦች ቁጥጥር ሥር የወደቁት ቀበሌዎች መሪዎች በሚካሄደው በስመ "ቀይ ሽብር" የኢትዮጵያን ወጣቶችና ወላጆች ለማሸበርና ለአድሃሪው ቢሮክራሲ ፀረ-አብዮት አገዛዝ መንገድ ለመጥረግ በይዘቱም ሆነ በዓላማው በዲሞክራሲያዊያን ቀበሌዎች ከተካሄደው ትግል ጠርቦ የተለየ ጭፍጨፋ ተካሄደ:: በአፈጣጠራቸው ከህዝብ የፈለቁ አካሎች በነበሩበት ወቅት የሰፊው ህዝብ አለኝታና አገልጋይ የነበሩት ቀበሌዎች ቦታ ከነዚህ ጋር በስም ብቻ አንዷ በሌላ በምንም ግንኙነት የሌላቸው የፀረ-ህዝብ ጉድኖች ተመስርተው በከተሞች የአድርባዮች የለየላቸው አድሃሪዎችና የበዝባዦች ፀረ-ህዝብ መፈንጫ መሥሪያ ቤቶች ሆኑ::

ከተመሠረተበት ወቅት አንስቶ በኢህአፓ ቅጥር ነፍስ ገዳዮች፣ በኋላም የቀኝ አድርባዮች፣ የአድሃሪው ቢሮክራሲና የበዝባዦች መረባረብ ያጠቃው መኢሶም ይህ በሌሎች ህ



ዝባዊ ድርጅቶች ላይ የጠደቀው ዕጣ አርፎበታል:: አንድ ዓመት በማይሞላው ጊዜ ውስጥ ሁለት ወታደራዊ ሹም ሽር ተደርጉበት ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የተመረጡት መሪዎች በየእስርቤቱ ታጉረው የመንግሥት ሹማምንት በመሪነት ስም ተጭነውበታል:: በዚህ መልክ ከሃቀኛ አብዮታውያን ፀድቶ ተራ የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሆነው መኢሠማ የፀረ-ወዝአደር ቅስቀሳና አመጽ ማካሄጃ አካል ሆኗል:: ይህንን የተቃወሙ ሃቀኛ ወዝአደሮችና ሌሎች ግንባር ቀደሞች ሁሉ እየታፈኑ በየእስር ቤቱ ተወርውረዋል::

ዛሬ የምንገኝበት ሁኔታ ይህ ነው:: በተደጋጋሙበት ወቅት ህዝባዊ፣ ዲሞክራሲያዊ፣ አብዮታዊ የነበሩት ህዝባዊ ድርጅቶች ጠውልገውና ፈራርሰው በቦታቸው በፀረ-አብዮት ሃይሎች ቁጥጥር ሥር የዋሉ፣ የፀረ-ህዝቦች መገልገያ የሆኑ ድርጅቶች ተተክተዋል:: የዚህ ሁኔታ አደጋ ለብዙ ጊዜ የተደከመባቸው በንፁህ ጓዶች የተገነቡት ህዝባዊ ድርጅቶች ፈራርሰው መገኘታቸው ብቻ አይደለም:: በህዝባዊ ድርጅቶች ስም በመካሄድ ላይ ያለው ፀረ-አብዮት አመፅ ህዝቡን ከመደራጀት ጥረቱ ተስፋ እንዲያስቆርጡና በፀረ-ህዝቦች የተበተነውን ሁሉ እንደገና መልሶ ለመሰብሰብ ግንባር ቀደሞች በሚያደርጉት ጥረት እንቅፋት እንዳይሆን ያሰጋል:: ስለሆነም፣

1ኛ ከሁሉ አስቀድሞ በአድርባዮች፣ በበዝባዦችና በለየላቸው አድሃሪዎች ቁጥጥር ሥር ባሉትና በአብዮት ስም ፀረ-አብዮት በሚያካሂዱት "ህዝባዊ ድርጅቶች" በተባሉት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በአንድ በኩልና በሰፊው ህዝብ ተመስርተው ለሰፊው ህዝብ ሲያገለግሉ በነበሩት ህዝባዊ ድርጅቶች መሃከል ያለውን ልዩነት ለማስረዳት በሰፊው ህዝብ መሃከል ከፍተኛ ቅስቀሳ ማካሄድ ያስፈልጋል:: ቀደም ሲል በህዝብ ተመርጠው በግንባር ቀደምነት ለህዝቡ ያገለግሉ ከነበሩት ውስጥ ወይ በኢህአፓ ቅጥረኞች ጥይት ተሰውተዋል፣ ወይ ለፀረ-ህዝቦች አናጎበድድም ብለው ታስረዋል፣ ተረሽነዋል፣ ወይ ደግሞ በወታደራዊ ሹም ሽር ቦታቸውን እንዲለቁ ተገደዋል:: ዛሬ ህዝባዊ ድርጅቶች የሚባሉት አብዛኞቹ የቢሮክራሲው ተቀጣዮች ናቸው:: ይህንን ጠንቅቆ የተረዳው ሰፊው ህዝብ ሃቀኛ ህዝባዊ ድርጅቶችን ለማምጣት አስፈላጊ ለሆነው ዲሞክራሲ የሚያደርገውን ትግል ማህበራችን ሙሉ በሙሉ ይደግፋል:: ከጐኑም በመቆም የደርግን ፀረ-ዲሞክራቲክ አገዛዝ ለማጋለጥ ሰፊ ቅስቀሳና ትግል እንደሚያደርግ ያረጋግጣል::

2ኛ ከዚሁ ጋር በመያያዝ በያለበት በፀረ-አብዮቱ ግፊት በመፈራረስ ላይ ባሉት ድርጅቶች ቦታ በህቡዕ ሃቀኛ የሆኑ፣ ሃቀኞችን የሚያስተባብሩ ቀስ በቀስ ህዝቡን ሊያንቀሳቅሱና ሊመሩ የሚችሉ የህዝባዊ ድርጅቶች ጥንስስ መጣል የጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄ ነው:: ማህበራችን የኢት. ተራማጆች በዚህ አንፃር በርትተው እንዲሰሩ አብዮታዊ ጥሪ ያደርጋል::

3ኛ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት በብዙ ታጋዮች መስዋትነት የተደጋጋሙትን የሰፊውን ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች ለማፈራረስ የወሰደውን ፀረ-ህዝብ እርምጃ በጥብቅ እያወገዘ "ህዝባዊ ድርጅቶችን ከቀኝ መንገደኞች ለማጽዳት" በሚል የሚያደርገውን ምንጠራ እንዲያቆም ይታገላል::

4ኛ በሰፊው ህዝብ ተመርጠው በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ በኃላፊነት ሲያገለግሉ በደጅ/ደርግ የወሰደባቸውን የግድያ ያስራና ያፈና ዘመቻ ማህበራችን አጥብቆ ያወግዛል:: ይህ ድርጊት ባስቸኳይ እንዲቆም ይታገላል:: በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ሰፊውን ህዝብ ሲያገለግሉ በደርግ/በደጅ እስር ቤት በመማቀቅ ላይ ያሉ ታጋዮች በአስቸኳይ እንዲፈቱ ይጠይቃል:: ለዚህም ይታገላል::

## 10. ስለ ዴሞክራቶችና ሀገር ወዳዶች መደራጀት

ተደጋግሞ እንደተገለፀው የኢት. ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት የተለመለትን ግብ እንዲመታ በወዝአደሩ ፓርቲ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ዴሞክራሲያዊ ፓርቲዎች አባልነት የሚመሠረት ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ያስፈልጋል። ማህበራችን ዴሞክራቶችና ሀገር ወዳዶች ሃይላቸውን አስተባበረው ለኢት. አብዮትና ብሔራዊ ነፃነት እንዲታገሉ በተደጋጋሚ ጥሪ አቅርቦላቸዋል። እንደዚሁም የዚህ ግንባር አባላት ሊሆኑ የሚችሉት የሙያና በፋሬ ድርጅቶች በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲቋቋሙና እንዲጠናከሩ ጥሪ ሲያደርግና ሲታገል ቆይቷል። ይህንን ጽሱመት እስካለተወጣ ድረስ የኢት. አብዮት ግቡን ሊመታ አይችልም። በተለይ ዛሬ በኢት. ለጥቂት ጊዜ በፍና የነበረው ዴሞክራሲ ደብዛው ጠፍቶ ብሔራዊ ክብሩና ነፃነቱ ተደፍሮ ሀገራችን ከፍተኛ ውርደት ላይ ወድቃ በምትገኝበት ወቅት የዴሞክራቶችና የሀገር ወዳዶች መደራጀት የአብዮታችን አንገብጋቢ ጥያቄ ሆኖ ቀርቧል።

በዚህ ሁኔታ የኢት. አብዮታውያን የቀዳሚያ ቅድሚያ የሚሰጡት ለአብዮታችን የወደፊት ግስጋሴ ወሳኝ ለሆነው ለዴሞክራሲና ለብሔራዊ ክብራችን ለሚደረገው ትግል ነው። እንኳን አሁን በሚገኝበት ሁኔታ ቀርቶ ጠንካራ የወዛደር ፓርቲ ቢኖረው እንኳን የኢት. ወዛደር መደብ ይህንን ታሪካዊ ተግባር ብቻውን ሊያያዘው አይችልም። ለዴሞክራሲና ለብሔራዊ ክብር በሚደረገው ትግል ዴሞክራቶችና በሀገር ፍቅር ስሜት ልባቸው የሚነዱ ሀገር ወዳዶች ሁሉ በሚሊዮን እየተቆጠሩ መሳተፍ አለባቸው ብንል ማንም የሚያውቀውን መድገም ነው።

ዛሬ ሀገራችን በምትገኝበት ሁኔታ እነዚህን ሃይሎች በበስበ ማደራጀት የዴሞክራትና አገር ወዳዱ ግንባር ቀደምች ተግባር ቢሆንም ማርክሲስት ሌኒንስቶችም ታላቁ ሌኒን እንዳለው "በህብረተሰቡ ውስጥ የሚገኙትን የህብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ ለማደራጀት መርዳት አለባቸው" ባለው አብዮታዊ መመሪያ መሠረት ለዚህ ጥረት መሰለፍ አለባቸው። ማህበራችን ለሚታገልለት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ የነዚህን ሃይሎች ከፍተኛ አስተዋፅዖ በመረዳት አባላት ሁሉ በያሉበት ዴሞክራቶችና ሀገር ወዳዶች እንዲደራጁ መቀስቀስና በግንባር ቀደምትነትም ማደራጀት አሳባቸው፤ ከዚህ ሀቅ በመነሳት፤

1ኛ ዛሬ ፀረ-አብዮት ሃይሎች አመፃቸውን በማጠናከሩ ላይ ያሉት በመኢሶን፣ በኢአወን፣ በኢሕአፓን፣ አባላትና ደጋፊዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው ዴሞክራሲያዊ አስተባባሪ፣ የሀገር ፍቅር ስሜትና ለአብዮቱ ተባትና ባላቸው ሃይሎች ሁሉ ላይ ስለሆነ ዴሞክራቶችና ሀገር ወዳዶች ይህን ሁኔታ እንዲቋቋሙና ትግላቸውን እንዲያፋፍሙ ማበረታታት፤

2ኛ የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ከለየላቸው ፊውዳሊስቶችና የውጭ ሃይሎች ቡችሎች በስተቀር በጠቅላላ በሀገሪቱ የሚገኙትን ሃይሎች በሙሉ ጥቅም የሚያረጋግጥ መሆኑን ለመረዳት በተለይ ፕሮግራሙን ገና ሙሉ በሙሉ ባልተቀበሉ ዴሞክራቶችና ሀገር ወዳዶች አካባቢ የተለየ ቅስቀሳ ማድረግና እነዚህን ሃይሎች ለትግል ለመቀስቀስ የተለየ ጥረት ማድረግ፤

3ኛ በብ.ዲ.አ.ፕ. በተተለመው መብታቸው መሠረት በየአካባቢው የሚገኙ ዲሞክራቶችና ሀገር ወዳዶች ሁሉ እንዲደራጁና የራሳቸውን ድርጅት እንዲመሠርቱ መቀስቀስና ማበረታታት።



## 11. ስለ ተራማጆች ህብረት ጥያቄ

በተራማጆች ህብረት ጉዳይ የኢት. አብዮታውያን እስከዛሬ ቢያካሂዱት የቆዩት ትግል በሁለት የተያያዙ አቅጣጫዎች መሆኑ የታወቀ ነው። ግንባር ቀደም የሆኑ አብዮታውያን በሀገሪቱ የሚገኙ ማሌ ድርጅቶችና ቡድኖች ህብረት ፈጥረው ከዚያም በሃቀኛ ርዕዮተዓለም ትግል ወደ ውህደት ተሸጋገረው የኢት. ወዛደር ፓርቲ ለመመሥረት ታግለዋል። ሁለተኛ ደግሞ በሀገሪቱ የሚገኙ ሌሎች ፀረ-ፊውዳል፣ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ኃይሎች በፈርጁ በፈርጃቸው ተደራጅተው ህዝባዊ አብዮታዊ ግንባር እንዲፈጠሩ ትግል አካሂደዋል።

ምንም እንኳን ባለፉት ዓመታት በዚህ ጉዳይ ላይ የተካሄደው ትግል በዙ መስዋዕትነት የተከፈለበትና በዙ ድሎች የተገኙበት ቢሆንም ዛሬ ያለው ሁኔታ አስከዚህም አስተማማኝ ነው ለማለት አይቻልም። የማሌ ድርጅቶች ከህብረት ወደ ውህደት ተሸጋገረው "የወዛደር ፓርቲ"ን መፍጠር በሚመለከተው በኩል በመሠረት ግንባር ቀደምትነት የተደረገው ትግል ፍሬ ሰጥቶ በየካቲት ወር 1969 ዓ.ም. "የኢት. ማርክሲስት ሌኒንስት" ድርጅቶች የጋራ መገለጫና መርሀ ገበር ይፋ ወጥቶ እንደነበር ይታወሳል። ከዚያን ወዲህ ይህን ሰነዱ ከወጡት ድርጅቶች መሃከል ወዝ ማሌሪድና ሰደድ ከፕሮግራሙ እየተንሸራተቱ ከፍተኛ የፖለቲካ ክስረት ከደረሰባቸው በኋላ የማይተረው ድርጅታዊ ክበረት ተከትሉ ስለመጣባቸው ዛሬ በንዑስ ከበርቴው ደርግ እግሯ እንደፈርጡ ተደርገዋል። ምንም እንኳ ንዑስ ከበርቴ ከሃዲዎችና አድሃሪው ቢሮክራሲ በውጭ ኃይሎች አስተባባሪነትና የበላይ ጠባቂነት "የወዝ አደር ፓርቲ" በቅርቡ ልንመሰርት አዲስ ወሳኝ ምዕራፍ ጀመርን እያሉ ክስረታቸውን ለመሸፈን ቢሞክሩም በዚህ በወዝአደር ፓርቲ ጉዳይ ዛሬ በየካቲት 1969 ከተደረሰበት ደረጃ አንፃር ወደኋላ የተሄደ መሆኑ ገልፀ ነው። በሳሳ በኩል ደግሞ ለህዝባዊ አብዮታዊ ግንባር አስፈላጊ ናቸው ተብለው የተገመቱት የዴሞክራቶችና የሀገር ወዳዶች ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች እስከአሁን ገና ብቅ አላሉም። የሙያ ድርጅቶችም ዴሞክራሲያዊ አሠራራቸው በፀረ-አብዮት ሃይሎች ተኮላሽቶ በህዝብ ያልታቀፉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሆነዋል። በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቋቋሙትና ለህዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ትልቅ አስተዋፅኦ የሚጠበቅባቸው የኢትዮጵያ ሴቶች አብዮታዊ ንቅናቄ፤ የኢት. ወጣቶች አብዮታዊ ንቅናቄ ወዘተ እንዲሁም ዴሞክራሲያዊ የሆኑት የብሔረሰቦች ንቅናቄዎች በፀረ-ሕዝቦችና በትምክህተኞች አመፅ ታፍነው አስቸጋሪ የሆነ ትግል በማካሄዱ ላይ ናቸው።

ይህም ሆኖ መጪው ጊዜ በሁለቱም ግንባር የኢት. ተራማጆችን ህብረት ለመፍጠር ይበልጥ አመቺ እየሆነ እንደሚሄዱ ማህበራችን ሙሉ እምነት አለው። በጠቅላላው በኢት. የሚገኙት ተራማጅ ኃይሎች፣ ዴሞክራቶች ሀገር ወዳዶች፣ የወጣቶች፣ የሴቶች፣ የተለያዩ የብሔረሰብ እንቅስቃሴዎች፣ የሙያ ማህበራት ወዘተ በብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መሠረት ላይ እንዲሰበሰቡ፣ የኢት. ማርክሲስት ሌኒንስቶች ደግሞ ከዚህ በተጨማሪ በየካቲት 1969 ዓ.ም. የጋራ መርሀ-ገብርን ተወያይተው በውስጡ የሚገኙ ስህተቶችን አሻሽለው በሚያወጡት ተጨማሪ ፕሮግራም ተመርኩዘው አንድነታቸውን ማጠንከር አለባቸው።

እነዚህ የተሰበጣጠሩ ሃይሎች ህብረትን እንዲፈጥሩ የግድ በሁሉ ነጥቦች ላይ ስምምነት መድረስ አለባቸው ብሎ ማህበራችን አያምንም። በመሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ በኢት. አብዮት አንገብጋቢ ጥያቄዎች ላይ ዛሬ በኢት. ተጨባጭ ሁኔታ ያለፉትን ዓመታት ዱካ

ች ለመጠበቅ አስፈላጊነትን እስከመጨረሻ ድረስ በትግል የታከቡ ጥያቄዎች ላይ የሚነሱ ልዩነቶች ተራማጆችን እንዳያሥሩ ሊከፋፍሏቸውና ሊያዳክሟቸው አይገባም ብሎ ያምናል:: በነዚህ ልዩነቶች ላይ ዴሞክራሲያዊ የሆኑ ውይይቶች እያካሄዱ አንድ ለአንድ ተያይዞ መራመድ ይቻላል:: የጋራ አቋም ይዘው እነሱን ከሥራ ላይ ለማዋል በጋራ መታገል፣ በጋራ ጠላት ፊት በአንድነት መቆም የተራማጆችን አንድነት በትግል ውስጥ ማጠናከር ይቻላል::

በዚህ መሠረት የኢት. ተራማጆች በሆነ ባልሆነው ተበታትነው በጠላት እጅ እየተመቱ ከማለቅና አብዮቱን ጉዳት ላይ ከመጣል ካለፉት ስህተቶቻቸው እየተማሩና የፖለቲካ መስመሮቻቸውን እያስተካከሉ በአዲስ መንፈስ የተራማጆች ህብረት እንዲፈጥሩ ማህበራችን አብዮታዊ ጥሪውን ያቀርባል:: በዚህ አንፃር ለእውነተኛ የተራማጆች ህብረት መፈጠር የማያቋርጥ ጥሪና ትግል ያካሄዱት መኢሶንና ኢሕወን አብዮታዊ ድጋፉን እንደገና ያሁስባቸዋል::

## 12. ስለ መደበኛውና "ህዝባዊ" ሠራዊት ጥያቄ

ጭቁኑ መደበኛና "ህዝባዊ" ሠራዊት የወጡት ከሰፊው ህዝብ አብራክ ነው:: ከየካቲት 1966 እስከዛሬ ጭቁን ወታደር በብዙውን ጊዜ ከሰፊው ህዝብ ጋር በመቆም ለአብዮቱና ለእናት አገሩ አገልግሏል:: አብዮቱንና እናት አገሩን ከልዩ ልዩ የውስጥ የቀልበሳ ሴራዎችና የውጭ ወረራዎች በመከላከል ቆይቷል:: በዚህ በኩል ከሰፊው ጭቁን ህዝብ ጎን በመቆም በነፍስና በደም የከፈለውን መስዋዕትነት ማህበራችን ሲያስታውሰው ይኖራል::

"ህዝባዊ" ሠራዊቱም ለአብዮቱና ለእናት አገሩ ከበር ታላቅ ተጋድሎ አድርጓል:: የአገራችንን ዳር ድንበርን ያስከበረበት ታሪኩን ከሰፊው ህዝብ ተሞቶ ወደረባቸው ለማድረግ በሚጥሩት በጥቂት ወታደሮች ባይሆን በመደበኛና በህዝባዊ ሠራዊት ህይወትና ደም ነው:: አድርባዮች እንደሚለፍፉት በውጭ ሃይሎች አይደለም::

ኢ.ወ.መ. ከውጭ ሃይሎች ጋር ያለውን ህብረት ለማጠንከር ቢል የኢት. ጭቁን መደበኛና "ህዝባዊ" ሠራዊት ባደረገው ተጋድሎ ያስገኘውን ድል ለሶቭየት ህብረትና ለኩባ ወታደሮች አሳልፎ መስጠቱ በኢት. መደበኛና "ህዝባዊ" ሠራዊት ላይ የተሰነዘረ አሳፋሪ ስድብ እንደሆነ ማህበራችን ይገነዘባል::

ይህ ብቻ አይደለም:: የኢት. ጭቁን ወታደር ለዴሞክራሲ እንዳልታገለና ፀረ-ዴሞክራቲክ ሃይሎችን እንዳላንበረከከ ዛሬ ኢ.ወ.መ. በጭቁን ወታደርና "ህዝባዊ" ሠራዊት ላይ የወታደራዊ ቢሮክራሲ አስተዳደሩን በመዘርጋት ጭቆናውን በማካሄድ ላይ ይገኛል:: በሚደረገው ጭቆናም ብዙ ወታደሮች ተገድለዋል:: ታስረዋል:: ተሰደዋል:: ከዚህም ሌላ ጭቁኑ ወታደር የሚገኝበት ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ማህበራዊ ሁኔታ እጅግ የሚዘገንን ነው:: ይህን አስከፊ ሁኔታ ለመቋቋም ሰፊው ጭቁን ወታደር በአሁኑ ወቅት ከመቸውም ጊዜ የበለጠ ለዴሞክራሲ፣ ለደመወዝ፣ ለተሻለ የሥራ ሁኔታ፣ ወዘተ የሚያደርገውን ትግል አፋፍሟል:: በባእዳን የጦር መኮንኖች የሚደረገበትንም ተጽእኖና በደል ለመቋቋም እየታገለ ነው::



ስለሆነም ሰፊው ጭቁን መደበኛና "ህዝባዊ" ሠራዊት ለዴሞክራሲ፣ ለደመወዝና ለተሻለ የሥራ ሁኔታ የሚያደርገውን ትግል እየደገፈ ማህበራችን፣

1. ዛሬ ደርግ/ሰደህና የውጭ ሃይሎች በማበር መደበኛና "ህዝባዊ" ሠራዊቱን የረባቸው የፀረ-አብዮት ትግል ማጠናከሪያ ለማድረግ ያቀዱትን ዓላማ ሠራዊቱ ነቅቶ በመጠባበቅ ላይ እንዳለው ሁሉ ትግሉን አፋፍሞ ይሽን ፀረ-አብዮት ሴራ እንዲያከሽፈው፣

2. ለዴሞክራሲ፣ ለብሔራዊ ነፃነትና ለብሔረሰቦች እኩልነት በሚታገሉ ተራማጆች፣ ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች ላይ አፈሙዙን እንዳያዞር ደርግና ተባባሪዎቹ የሚያደርጉበትን ተጽእኖ እየተቋቋመ በአብዮቱ ሠፈር ሰልፉን እንዲያጠናክር፣

3. "የኢት. ብ.ዲ.አ.ፓ. በሥራ እንዲተረጉም እስከመጨረሻው የደም ጠብታ ለመታገል" የገባውን አብዮታዊ ቃል ኪዳን በሥራ ለመተርጎም ትግሉን እንዲያፋፍም ይህ ጉባኤ አብዮታዊ ጥሪውን ያቀርባል::

## 13. ስለ ልዩ ልዩ ድርጅቶች

### 1. ስለ መኢሶን

መኢሶን ከሰፊው ህዝብ ጎን ቆሞ ለኢትዮጵያ አብዮትና ለብሔራዊ ነፃነቷ በግንባር ቀደምነት ሲዋደቅ የቆየና አሁንም በመዋደቅ ላይ የሚገኝ ሃቀኛ ማርክሲስት ሌኒንስት ድርጅት ነው:: ከተመሠረተበት ወቅት አንስቶ ዕጣው ከኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ዕጣ ተለይቶ አያውቅም::

በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ በግንባር ቀደምትነት በመቆም፣ የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ከዳር እስከዳር ነቅተው ተደራጅተው ታጥቀው በህዝባዊ አመጽ ህዝባዊት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እንዲገነቡ በቆራጥነት የታገለና የሚታገል ድርጅት ነው:: ባለው የጠራ የማርክሲስት ሌኒንስት አቋም ህጋዊ መድረኮችን በመጠቀም ለአብዮቱ የማይናቅ ድሎችን አስገኝቷል:: ኢሠአፓ የኢትዮጵያን አብዮት ለመቀልበስ ከፍተኛ ውዥንብር በፈጠረበት ጊዜ በግንባር ቀደምነት ከሰፊው ህዝብ ጎን ቆሞ የተነባውን የሁለት መስመር ትግል ባደረገው የርዕዮተዓለም ትግልና ባካየው የፖለቲካ ጥረት፣ ኢሠአፓ ከሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲተፋ አድርጓል:: ዛሬም በሆን ቀኝ አድርባዮችን፣ በርዕዮተዓለም በበቂ አጋልጧቸዋል:: በፖለቲካም መስክ ከፍ ያለ ጥረት እንዲገኝ አድርጓል::

እንደሚታወቀው የነባለማየሁ ኃይሌ የቀኝ ሃይሎች ህብረት ከተመታ በኋላ፣ አብዮቱ ለጥቂት ጊዜ ያህል ወደፊት መገስገስ ጀምሮ ነበር:: ሆኖም የነባለማየሁን የተልባሽ ፖለቲካ መስመር ይዞ ሌላ አዲስ የቀኝ ኃይሎች ህብረት መጡትና፣ በጊዜው "ማርክሲስት ሌኒንስት" ተብለው የወጡ ድርጅቶች ከሰፊው ህዝብና ከብ.ዲ.አ.ፓ. መንሸራተት፣ በዚህ የቀኝ ሃይሎች ህብረት መሰለፍና፣ ወደ አጉብዓኝነት መለወጥ በተነባው የፖለቲካ ውዥንብርና የመስመር ትግል መኢሶን በግንባር ቀደምነት ከሰፊው ህዝብ ጎን በመቆ

ም ከፍተኛ ትግል አካሂዷል:: ሆኖም ከአድሃሪ ሃይሎች የሚሰነዘርበት ጥቃት ከጊዜ ወደ ጊዜ መረን እየለቀቀ መምጣትና በተለይ ከሚያዝያ 69 አጋማሽ ወዲህ የህጋዊ ትግል መስክ መመንመንና መጥበብ ምክንያት ድርጅቱ አንዳንድ በህጋዊ መድረክ የተሰለፉ አባላቱን ወደ ህቡዕ ትግል ስልት አዛወረ:: ይህም መኢሶን የወሰደው እርምጃ በተለይ በደርግና የቀኝ አድርባይ ድርጅቶች የያዙት ፖለቲካ ለአብዮታችንም ሆነ ለብሔራዊ ክብራችንና ነፃነታችን አደገኛ የሆነ መስመር በመሆኑ፣ በበለጠ ለመታገስ የሰፊውን ህዝብ ወገንነት በመምረጥ በመሆኑ ትክክለኛ የማሌ መርሆችን የተከተለ በመሆኑ ማህበራችን ደግፋታል:: ዛሬም በዚህ ጉባዔ ድጋፉን ያሁስሳታል::

ይህ እኩይ የቀኝ ኃይሎች ህብረት መኢሶንን ከሰፊው ህዝብ ለመነጠል ለማግለልና ለመከፋፈል ያልጠነሰሰው ሴራና ያልፈጸመው ፀረ-ህዝብ አመጽ የለም:: በቀኝ አድርባይ ድርጅቶች "ነገር ቀደምነት" የመኢሶንን የፖለቲካ መስመር ለመምታት የተቻለውን ያህል ቅስቀሳ ቢያደርጉም መኢሶን የሚከተለው ፖለቲካ የህዝብ መስመር በመሆኑ ፍፁም አልተሳካላቸውም:: አርግጥ ይህ እኩይ የቀኝ ሃይሎች ህብረት በድርጅቱ አባላት፣ ወዳጆችና ደጋፊዎች ላይ ከፍ ያለ የማሰር፣ የመግደል፣ የማፈን፣ የማሳደድ ዘመቻውን በከፍተኛ አኳኋን ቢያካሂድም ይህ ሁሉ ጥቃት፣ ድርጅታዊ ዲክምን አስከተለበት እንጂ ይህ ፀረ-ህዝብ አመፅ እንኳ መኢሶንን ከያዘው የህዝብ መስመር ፈቀ አላደረገውም::

ማህበራችን መኢሶን በአብዮቱ ውስጥ የሰጠውንና የሚሰጠውን አብዮታዊ አስተዋጽኦ ሊተቀል እንደሚችል፣ ከውድ ጓዶቹ ደምና መከራ የተገኘውን ትምህርት ወስዶ በማጠናከር ላይ ያለውን የህቡዕ መዋቅሩን እንዲገፋበት ማህበራችን ያስገነዝባል::

መኢሶን ካደረገው የትግል ስልት ለውጥ ወዲህ ሰደዱ የወሰደውንና የሚወስደውን የማሰርና የመግደል የማፈንና የማሳደድ ዘመቻ አጥብቆ ይቃወማል:: ይህም ፀረ-አብዮት ድርጊት በአስቸኳይ እንዲቆም ይጠይቃል:: ከህዝብ ጎን ቆመው መታገላቸው እንደ ወንጀል ተቆጥሮባቸው "ፈርጣጭ" "ቀኝ መንገደኛ" በመባል የታሰሩ የመኢሶን አባላት፣ ደጋፊዎችና ወዳጆች፣ ወዛደሮች፣ አርሶአደሮች፣ መለዮ ለባሾች፣ ወጣቶች፣ ታጋይ ሴቶች፣ የጭቁን ብሔረሰብ ታጋዮች፣ የቀበሌ ተመራጮች፣ ሃቀኛ ተራማጆች አሁኑኑ እንዲፈቱ ጉባኤው አጥብቆ ይጠይቃል:: ለዚህም ይታገላል::

ማህበራችን ከዚህ ቀደም መኢሶን በልሳኖቹ በሰሀዱ ላይ ያደረጋቸውን አብዮታዊ ጥሪዎች መደገፉ ይታወቃል:: ባለፉት ሁለት ዓመታት በአብዮቱ በፈር ሊደርስ የቻለው ጥቃት ፀረ-ህዝብ ኃይሎች ተራማጆችን ለመከፋፈል በመቻላቸው መሆኑን በመገንዘብ "መከፋፈል ይብቃ" በማለት በቅርቡ በሰሀዱ 69 ለኢት. አብዮታውያን፣ ለብሔራዊ ክብርና ነፃነት፣ ለዲሞክራሲ ለብሔረሰቦች መብት ለእኩልነት በጠቅላላ የብ.ዲ.አ.ፕ. ላይ የተጠቀሱት ዓላማዎች በሥራ ላይ እንዲውሉ የቆሙ ኃይሎች እንዲሰባሰቡ ያደረገውን ጥሪ ይደግፋል፣ ለዚህ ለተቀደሰ ዓላማ ማህበራችን ከጎኑ እንደሚቆም ይገልፃል::

በአኢተማ፣ በትግሉ ሜዳ በሰማዕታትነት የወደቁትን የመኢሶን ጓዶችና የሌሎችም አብዮታውያን የትግል ዓርማ ይዞ ለመጓዝ ቃል ኪዳኑን በድጋሚ እያደሰ ለመኢሶን ያለውን ሙሉ ድጋፍ ያረጋግጣል:: ከዚህ በፊት እንዳደረገው ሁሉ ዛሬም ለዚህ ሃቀኛ ማሌ ንቅናቄ ዓለም አቀፍ አጋሮችንና ድጋፎች ለማስገኘት የሚታገል መሆኑን እንደገና ያረጋግጣል::



2. <u>ስለ ኢሕወገ</u>

የአንጋፋው የመኢሶን ወጣት ክንፍ የሆነው ኢሕወገ እስከዛሬ ድረስ በሀቀኛ የፖለቲካ መስመር በግራም ሆነ በቀኝ አድርባይነት የፖለቲካ መስመር ሳይበረዝ በትክክለኛ ጎዳና የተጓዘ፣ የታገለና የሚታገል ግንባር ቀደም አብዮታዊ ወጣት ድርጅት ነው::

ኢሕወገ የኢህአፓን ውዥንብር ከወጣቱ ውስጥ ለማጥፋት ከፍ ያለ ርዕዮተዓለማዊ ትግል አካሂዶ ድልን ተቀዳጅቷል:: አያሌ ወጣቶች በፀረ-አብዮተኞች ተገድለውበታል:: በልሳኑ በአብዮት ሩና አማካይነት ባደረገው ቆራጥ ትግል የወጣቱ እንቅስቃሴ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ አብዮታዊ ፈር ሊይዝ ችሏል:: ፀረ-ህዝብ ሃይሎች ወጣቱን የነሱ ተቀጥላ ለማድረግ ባላቸው ዓላማ፣ በወጣቱ ውስጥ ጥራት እንዳይኖር፣ በዚህ አብዮታዊ ድርጅት ሥር እንዳይሰለፉ፣ በኢሕወገ ላይ ከፍ ያለ ጥቃት አካሂደውበታል::

በተለይም በጥርና በየካቲት 70 ወሮች "ከቀይ ሽብር" ስም ከአድሀሪ ሃይሎች ጋር ተደባልቆ፣ በወጣቱም አብዮታዊ ትውልድ ላይ የተካሄደው ጭፍንና አሰቃቂ ጭፍጨፋ ምን ጊዜም የሚታወስ ነው፣ ባሁኑም ጊዜ ብዙ አብዮታዊ፣ ተራማጅ አገር ወዳድ ወጣቶች በየእስርቤቱ ተወርውረው ይገኛሉ፣ ሆኖም ኢሕወገ ይህን ሁሉ ፀረ-ህዝብ ዐመፅ በትዕግሥት ተወጥቶ አሁንም ያለውን የጠራ መስመር እያራመደ ይገኛል::

በአኢተማ 19ኛ ጠ/ጉባዔ እስከዛሬ ይህ ድርጅት ሀቀኛ መስመሩን ያለማወላወል በማራመዱ ያሳየውን ቆራጥነት ያደንቃል:: ከዚህ በፊት ሰጥቶት የነበረውን ድጋፍ በዚህ ጉባዔ እንደገና ያድሳል::

ማህበራችን፣

— በኢሕወገ አባልነት፣ ደጋፊነት፣ እየተጠረጠሩ በየእስር ቤቱ የሚገኙት አብዮታዊ፣ ተራማጅና አገር ወዳድ ወጣቶች በአስቸኳይ እንዲፈቱ አጥብቆ ይጠይቃል:: ለዚህም ይታገላል::

— ለዲሞክራሲና ለብሔራዊ ነፃነት በሚታገሉ ወጣቶች ላይ ሰደዱ የሚያካሂደውን የእስራትና የግድያ የአፈና ዘመቻ ያወግዛል:: ይህም ፀረ-ህዝብ ዐመፅ በአስቸኳይ እንዲቆም ይጠይቃል:: ለዚህም ይታገላል::

3. <u>ስለ ኢሴአን</u>

ኢሴአን የኢት. ሴቶች በህብረተሰቡ ውስጥ ያለባቸውን ድርብ ጭቆና በመቋቋምና በአዲሱ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ውስጥ አብዮታዊ ተሳትፎ ድርሻቸውን እንዲያደርጉ በግንባር ቀደምነት ያታገለና የሚታገል ድርጅት ነው::

ማህበራችን ከዚህ በፊት ለኢሴአን የሰጠውን ሙሉ ድጋፍ ያድሳል:: በኢሴአን አካባቢ የተደራጁት ሴቶች ለዲሞክራሲና ለብሔራዊ ነፃነትና በጠቅላላ ለብ.ዲ.አ.ፕ. በሥራ መተርጎም ያደረጉትን ትግሎች ያደንቃል:: ማህበራችን ደርግ/ሰደዱ በኢሴአን ላይ የሚያደርገውን ፀረ-አብዮት ሴራ ያወግዛል፣ ያጋልጣል::

የአኢተማ 19ኛ ጠ/ጉባዔ፣

– በኢሕአፓ አባልነት ወይም ደጋፊነት እየተጠረጠሩ በደርግና የቀኝ አድርባዮች የሚያደርሱባቸውን ክትትል እስራትና ግድያ ማህበራችን አጥብቆ ያወግዛል፣

– የታሰሩት ሃቀኛ ተራማጅ ሴቶች አሁኑኑ እንዲፈቱ ማህበራችን ይጠይቃል፣ ለዚህም ይታገላል፡፡

4. <u>ስለ ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ የተማሪ ማህበራት ህብረት</u>

የኢትዮጵያ ተማሪዎች በአለም አቀፍ ደረጃ ለመደራጀት ከብዙ ጊዜ አንስቶ ታግለዋል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቋቋመው "አለም አቀፍ የኢት. ተማሪዎች ማህበር" በዚህ ትግል አንፃር በታሪክ ከፍተኛ ቦታ ይዞ ይቆያል፡፡

ማህበራችን የ"አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር" ተሸሽሎና ተጠናክሮ መላ የኢት. ተማሪዎችን ለነፃነቱ ትግል እንዲያስተባብር አጥብቆ ከፍተኛ ተጋድሎ ማድረጉ ይታወቃል፡፡ በዚህ ትግል መሠረታዊ እንቅፋት የነበረው ኢህአፓና በሱ ጥላ ስር የተደራጀው "አለም አቀፍ የኢት. ተማሪዎች ፌዴሬሽን" ተፈረካክሰው በራሳቸው ላይ ከአንድ ዓመት በፊት፡- በአኢተማ፣ በየተባበሩ ተራማጅ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች አንድነት ማህበር በሰሜን አሜሪካ፣ በቻይና የኢት. ተማ፣ በካይሮ የኢት. ተማ፣ በሱዳን የኢት. ተማ "አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ህብረት" ሊቋቋም ችለዋል፡፡

ይህ በብዙ ትግል የተመሰረተው ህብረት ዛሬ አያሌ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራትን አቅፎ አንደኛ ዓመቱን ያከብራል፡፡ ለረጅም ዓመታት የታገለለት አላማ እነሆ ዛሬ በሥራ ተተርጉሞ የሚያስደስት ውጤት በመስጠት ላይ ነው፡፡ ህብረቱም የመጀመሪያ ዓመቱን ሲያከብር ተግባሮችን ፈጽሞ ይገኛል፡፡

ይህንን ምክንያት በማድረግ፣ 19ኛው ጉባዔ፣

– የሚሰማውን በአብዮታዊ መንፈስ የተሞላ ደስታ ለህብረቱ መቋቋም ለታገሉት የተማሪ ማህበራት ያበስራል፡፡

– ለረጅም ዓመታት ለህብረቱ መቋቋም የታገለው ማህበራችን አሁንም በይበልጥ ለህብረቱ መጠናከር እንደሚታገል በድጋሚ ይገልፃል፣

– በህብረቱም ሆነ በአብዮቱ ላይ ከየአቅጣጫው የሚሰነዘረው ጥቃት የትገባችንን ውጤት እንደማያስከትል ያለውን እምነት ይገልፃል፡፡



5. <u>ስለ ኢዴህ</u>

ይህ በፊውዳሉ፣ በሚሊተሪና በሲቪሉ ቢሮክራሲ የሚወከል ፀረ-አብዮት ፀረ-ዲሞክራሲ ድርጅት ከየካቲት 66 እስከ 68 ከኢምፔሪያሊስቶችና ከአድሃሪ መንግሥታት ቀጥተኛ የማቴሪያልና የፖለቲካ ድጋፍ በማግኘት በኢትዮጵያ አብዮትና በኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ ጦርነት በመክፈት ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል፡፡ በ68ዓ.ም. በጎንደር አካባቢ በተደረገው ጦርነት ከፍተኛ ጉዳት ቢደርስበትም ዛሬ እንደገና ለመንሰራራት በአካባቢው ሀገሮችና በሌሎች አድሃሪ ሃይሎች ዝግጅት እያደረገ ነው፡፡ ከውስጥ ሆኖ በአብዮት ስም እየማለ የፀረ-አብዮት ሴራ የሚሸርበው የሲቪልና የሚሊተሪ ቢሮክራሲ ለዚህ ተባባሪ በመሆን፣ ደርግ በከፈተለት መድረክ በመጠቀምና ተደማጭ ያለው በመሆኑም በአሜሪካን የሚመራ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ለማድረግ ከውጭ ጋር የተያያዙ ሰንሰለት በመዘርጋት ላይ ነው፡፡ የኢት. ተራማጆች ይህ ፀረ-አብዮት ፀረ-ህዝብ ቡድን ተደምስሷል በማለት እንዳይዘናጉና የሲቪልና የሚሊተሪ ቢሮክራሲው በቀጥታ ከኢዴህ ጋር የተያያዙ በመሆኑ ፀረ-ኢዴህ ትግል መቀጠል ያለበት መሆኑን ጉባኤያችን ያሳስባል፡፡ ማህበራችን ይህን ፀረ-አብዮት ሃይል ለመደምሰስ በሚደረገው ትግል ያለርህራሄ ይሰለፋል፡፡

6. <u>ስለ ኢህአፓ</u>

ይህ የፀረ-አብዮት ድርጅት በኢትዮጵያ አብዮት መድረክ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ በተለይም የወጣቱን ክፍል በሚያስተጋባው የፀረ-አብዮት የፖለቲካ መስመር በማሰለፍ በግንባር ቀደምትነት የፀረ-አብዮት ሚና የተጫወተ የንዑስ ከበርቴው ቀኝ ክንፍ ቡድን ነው፡፡ አብዮታውያን ባራመዱት ትክክለኛ የፖለቲካ መስመር ከወጣቱና ከሰፊው ህዝብ እየተተፋ በመምጣቱ በደረሰበት የፖለቲካ ኪሳራ ወደ ቴሮሪስት ቡድን በመለወጥ በዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም መድረክ ላይ በተሰለፉት ሃይሎች ላይ ያደረጋቸው የነጭ ሽብር ዘመቻዎች የኢትዮጵያ አብዮት የብዙ አብዮታውያንን ህይወት እንዲያጣ ከፍተኛ በደል ፈፅሟል፡፡ ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብና ሃቀኛ አብዮታውያን የነጭ ሽብርን በቀይ ሽብር በመተካት ባካሄዱት ዘመቻ በመዳከሙ፣ በፀረ-አብዮት ፖለቲካው እየተተፋ በመምጣቱ፣ ከፍተኛ ድርጅታዊ መዳከም ደርሶበታል፡፡ በተለይም አብዮታችን ከአጥቂነት ወደ ተከላካይነት እንዲዘፍቅ ከተደረገ ወዲህ ቀኝ አድርባዮችና ደርግ/ሰደድ በከፈቱለት በር ሰተት ብሎ በመግባት በፀረ-መኢሶንነትና በሌሎች ሃቀኛ አብዮታውያን ዘመቻ በመሠማራት ለፀረ-አብዮት ሴራው አመቺ ሁኔታዎችን ከውስጥ ሆኖ በማዘጋጀት፣ ከውጭ ሆኖ ሌላ የህቡዕ መዋቅር በመዘርጋት እንደገና በከፍተኛ ደረጃ ለፀረ-አብዮት ሴራው ዝግጅት ለማድረግ ሽር ጉድ በማለት ላይ ነው፡፡ የኢት. አብዮታውያንና ተራማጆች ይህን እንደገና የመንሰራራት አዝማሚያ አደገኛነቱን በመመልከት ይህ ፀረ-አብዮት ድርጅት ህልውናው እንዲደመሰስ ከፍተኛ ትግል እንዲያካሂዱና ነቅተው እንዲጠባበቁ ማህበራችን ያሳስባል፡፡ በዚህ ፋሽስታዊ ድርጅት ሥር አሁንም "ተሰሩ" በማድረግ የተሰበሰቡና የተባባሉ ተራማጆች በትክክለኛ የፖለቲካ መስመር በመሰለፍ ለዲሞክራሲና ለብሔራዊ ነፃነት እንዲታገሉ ይህ ጉባዔ አብዮታዊ ጥሪውን ያቀርባል፡፡ ኢህአፓም እስከመጨረሻው እንዲደመሰስ ያለርህራሄ ይታገለዋል፡፡

7. <u>ስለ አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሽን</u>

አብዮታውያን ባካሄዱት የረጅም ትግል ዛሬ ኢህአፓ-ፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ተተፍቶ እንዲወጣ አድርገውታል:: ይህ የመረረ ትግል ውጤት ለረጅም ዓመታት የተሰለፍንለት አብዮታዊ መስመር እውነትም የህዝብና ለህዝብ የታገለ መስመር መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ያስመሰከረል:: በንፃሩም በፌዴሬሽን አደርባይ መስመር ላይ የተቀዳጀነው ድል ለኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ገና ለበዙ አመታት የማይረሳ ትምህርት አበርክቶ አልፏል::

ኢህአፓ-ፌዴሬሽን ተፍረከርኮ ከወደቀ ወዲህ በውስጡ ተደራጅተው የነበሩ አያሌ ወጣቶች በየበታው ተዘረከረከው ከፊሉ ከፖለቲካ አለም ርቆ ከፊሉ ደግሞ ከስህተቱ ተምሮ በጠራ መስመር ስር የሚያሰልፈውን ሃይል በመፈለግ ላይ ይገኛል::

ይህንን ሃቅ በመረዳት ማህበራችን እነዚህ ወጣቶች ከተበታተኑበት ሰብስቦ በትክክለኛው የትግል መስመር ስር የማሰለፍ ሃላፊነት እንዳለበት ይገነዘባል:: በመሆኑም ማህበራችን ለነዚህ ወጣቶች የሚያተርበው ጥሪ ከተረፈተው መስመር ተላቀው፣ ወጣቶች በኢት. ህዝቦች ትግል ውስጥ ያላቸውን ህያው ቦታ በማስታወስ ስህተታቸውን በድፍረት አርመው ከአብዮታዊ ወጣቶች በፈር እንዲቀላቀሉ ነው::

ማህበራችን በበኩሉ የተጣተበውን ሃላፊነት ለማሟላት ወደኋላ እንደማይልና በሬውን ተማሪ እንደገና መልሶ ለትግሉ ለማሰለፍ አስፈላጊውን አስተዋጽኦ ለማድረግ እንደማይቦዝን በዚህ ገሊጸው ያረጋግጣል::

<u>ክ ፍ ል 4</u>

14. <u>ስለ ፖለቲካ እስረኞች ጉዳይ</u>

ዛሬ በኢ.ወ.መ. እስር ቤቶች ውስጥ በመማቀቅ ላይ የሚገኙት አብዛኞቹ የፖለቲካ እስረኞች ከየካቲት በፊትም ሆነ በኋላ የህዝብ አገልጋዮች የነበሩና በአድሃሪዎች ጥያቄና ፍላጎት ከሰፊው ህዝብ ጉያ እየተፈለቀቁ የታሰሩ ተራማጆች፣ ዲሞክራቶች፣ አገሂህም አገር ወዳጆች ናቸው::

የተራማጁ ፖለቲካ እስረኞች በዛት እንደዚህ ከፍተኛ መሆኑ ከአብዮቱ መጠናከርና መገዘም ጋር የተያያዘ ነው::

አብዮቱ ወቅታዊ ጥያቄዎችን እናተዷም አጠቃላይ እርምጃ ባደረገበት በመጀመሪያዎቹ በስት ዓመታት በአስራት ሠራዊ በቀጥታ ስር ይውሉ የነበሩት ፀረ-አብዮታውያን ሃይሉ



ች ነበሩ:: ደርግ በዚህ አንፃር በሰፊው ህዝብና በተራማጆች ትግል እየተገደደ የወሰደው እርምጃ ተገቢና አብዮታዊ ነበር:: ማህበራችንም በእነዚህ ከየካቲት በፊት በሰፊው ህዝብ ላይ ኢሰብአዊ ጥቃትና በዝበዛ ሲፈጽሙ በቆዩና ከየካቲት በኋላም የአብዮቱን የወደፊት እርምጃ ለማገድ በሰፊው ህዝብ ላይ ሲያምፁ በነበሩ ልዩ ልዩ መልክ በነበራቸው አድሃሪዎች ላይ የተወሰደውን የእስራት እርምጃ ከሰፊው ህዝብ ጎን በመቆም ደገፍታል::

አብዮቱ ከወቅታዊ ጥያቶች አልፎ ጠቅላላ ጥያት ውስጥ ከገባበት ከ2 ዓመታት ወዲህ ግን በደርግ እስር ቤቶች ውስጥ እየተወረወሩ በመታጎር ላይ የሚገኙት በብዛት አብዮታውያን ሃይሎች ናቸው:: ደርግ በዚህ አንፃር በውጭና በውስጥ አድሃሪ ሃይሎች እየተረዳ የወሰደውና የሚወስደው እርምጃ ተገቢ ያልሆነና ፀረ-አብዮታዊ ነው:: ማህበራችን ደርግ በዚህ መንገድ በአብዮታዊ ድርጅቶች መሪዎች፣ አባሎችና ደጋፊዎችና በህዝባዊ ድርጅቶች መሪዎችና ታጋይ አባሎች፣ በጥቅሉ በሔረሰብ ታጋዮች፣ ዲሞክራቶችና አገር ወዳጆች ላይ በሰፊው ህዝብ ጠላቶች በተለይም በአድሃሪው ቢሮክራሲ እየተገፋ ያለአግባብ የወሰደውን ይህን ኢሰብአዊ እርምጃ ያለማቋረጥ አጋልጧል:: ያጋልጣልም::

በዛሬው ወቅት ለዲሞክራሲ፣ ለብሔራዊ ነፃነትና ለብሔረሰብ እኩልነት በመታገል አብዮቱን ወደፊት ለማራመድ በመጣራቸው ያለአግባብ የታሰሩት ተራማጆች፣ ዲሞክራቶችና አገር ወዳጆች በዛታቸው ከ20ሺ በላይ እንደሚሆን ይገመታል::

ተራማጅ የፖለቲካ እስረኞች ከደርግ የሚደረግላቸው ወርሃዊ ተቆራጭ የላቸውም:: ስለሆነም በተለይ መንግሥት ምግብ በማይሰጥባቸው እስርቤቶች ውስጥ የሚቆዩት ተራማጅ የፖለቲካ እስረኞች በረሃብና በእርዛት ይሰቃያሉ:: ምክንያቶቹ፣ 1. መንግሥት ቀለብ አለመስጠቱ፣ 2. አብዛኞቹ የታሰሩባቸው ቦታዎች ባለመታወቃቸውና ቤተሰብ ዘመዱና ጓደኛ ስንቅ ሊያቀብላቸው የሚችልበት ሁኔታ አለመኖሩ፣ 3. አብዛኞቹ ደግሞ ወዝአደሮች፣ ምሁራን፣ ወታደሮችና ወጣቶች በመሆናቸው ያላቸው ገቢ ለሥራቸው የሚከፈላቸው ወርሃዊ ደመወዝ ከመታሰራቸው ጋር ስለሚቋረጥ ቤተሰቦቻቸውና ዘመዶቻቸው እንኳን የሸቀጦች ዋጋዎች ጣራ ነክተውና እንጂያውም ያለማቋረጥ ስንቅ ለማቀበል ያላቸው የገንዘብ አቅም አለመፍቀዱና 4. ደርግ አንዳንዶቹን በረሃብ ለመቅጣት ምንም ዓይነት ምግብ እንዳይሰጣቸው ማድረጉ ናቸው::

ከዚህም ሌላ ተራማጅ የፖለቲካ እስረኞች ኢሰብአዊ የሆነ ዱብደባ ገርፋትና የማያቋርጥ "ምርመራ" ይካሄድባቸዋል:: በዚህም ምክንያት በዙዎቹ ሲሞቱ አብዛኛዎቹ ደግሞ የአእምሮና የአካላት መናወጽ ደርሶባቸዋል:: ከዱብደባውና ካሉበት የንጽህና ጉድለት የተነሳ በልዩ ልዩ በሽታዎች በመለከፍ የጤና ጉድለት የደረሰባቸውና በህመም የሚሰቃዩ በዙ ናቸው:: ሰው እንዳይጎበኛቸውም ይከለከላሉ:: በስንቅ አቀባዮቻቸው ላይ ማስፈራሪያችና ክትትሎች ይደረጋሉ::

ደርግ/ሰደድ የሚከተለው ፖሊሲ ተራማጆችን ያለማቋረጥ አያደኑ ማሰር፣ የእስራት ዘመናቸውን ማስረዘምና የፖለቲካ እስረኞችን "የቁም ሙታን" የማድረግ ፖሊሲ ነው:: ስለሆነም ማህበራችን፣

1. ደርግ/ሰደድ በዚህ ረገድ ከአድሃሪዎች ጋር በማበር የሚወስዳቸውን እርምጃዎች በሰፊው ህዝብ ፊት ያለመታከት ያጋልጣል::

2. ለዲሞክራሲ፣ ለብሔራዊ ነፃነትና ለብሔረሰብ እኩልነት መታገላቸውን እንደ "ወንጀል" ቆጥሮ ከሰፊው ህዝብ እቅፍ ውስጥ እየፈለቀቀ ተራማጆችን፣ ዲሞክራቶችንና አገር ወዳጆችን ለማሰር ኢ.ወ.መ. ያለአግባብ የወሰደውን ኢሰብአዊ እርምጃ አጥብቆ ይቃወማል::

3. በታሰሩት ተራማጅ የፖለቲካ እስረኞች ላይ ማንኛውንም ዓይነት ኢሰብአዊ ድብደባ፣ ግርፋት፣ የረሃብ ቅጣት፣ ወዘተ እንዳይፈጽሙባቸው ብቻ ባይሆን ባስቸኳይ እንዲፈቱ በጥብቅ ይጠይቃል፡፡

4. ተራማጆችን፣ ዲሞክራቶችንና አገር ወዳዶችን ለማሠር የሚደረገው የተቀነባበረ ክትትልና ስለላ ባስቸኳይ እንዲቆም አጥብቆ ይጠይቃል፡፡ ለዚሁም ይታገላል፡፡

5. ደርግ ተራማጆችን ለማሠርና በታሰሩትም ላይ የሚፈጽማቸውን ግፎች በአለም አቀፍ ደረጃ ለማጋለጥና በደርግ/ሰደዱ ላይ አለምአቀፋዊ ተፅዕኖ እንዲፈጠር በከፍተኛ ደረጃ ይሠራል፡፡ በዚህ መስክ ለሚሠሩ አለም አቀፍ ሰብአዊና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችም እንዲተባበሩት ጥሪ ያደርጋል፡፡

## 15. ስለ ፖለቲካ ስደተኞች ጥያቄ

ከየካቲት አብዮት ፍንዳታ ወዲህ በልዩ ልዩ መንገዶች አገራቸውን እየለቀቁ በውጭ አገር ተበትነው የሚኖሩ ከሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ስደተኞች አሉ፡፡

እነዚህ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ደርግና ቶኝ አዛርባዮች እንደሚሰብኩት አብዮቱ የመጣባቸውና አብዮትን በመቃወም የተሰደዱ ፊውዳሊስቶች፣ ቢሮክራቶችና ሌሎች አድሃሪያን ብቻ አይደሉም፡፡ እንዲያውም የስደተኞቹ መደብ ይዘት ሲመረመር ከእነዚህ መደቦች የመጡት በዛታቸው በጣም ትንሽ ከመሆኑ የተነሳ ቁጥር ውስጥ የማይገባ ነው፡፡ ከፖለቲካ ስደተኞቹ ከ90% በላይ የሚሆኑት የኢት. አብዮት ሃይሎች የሆኑት የንዑስ ከበርቴው /በተለይም ወታደር፣ መምህራን፣ የቢሮ ሠራተኞች/ የወዛደሩ /በተለይ በድንበር አካባቢዎች ከሚገኙ ዘመናዊ እርሻዎችና ከኤርትራ ከፍለአገር የተሰደዱ/፣ የአርሶአደሩ /በተለይ ከኤርትራና ከደቡብ ኢትዮጵያ ከሚገኙ ጭቁን ብሔረሰቦች የመጡ/ ክፍሎች ናቸው፡፡

በሌላ አነጋገር በስደተኝነት ከሚገኙት አብዛኛዎቹ ወይ በአደርባዮች ተወናብደውና የአብዮቱን ሂደት ባለመረዳት በተደረጉት ለውጦች ተደናግጠው ወይ ደግሞ በማንም ሳይወናበዱ ባይደናገጡ በጦርነት፣ በደርቅና በሌሎች ጭፍጨፋዎች የተነሳ ሰላምና ዓቦ በማጣት እንዲሰደዱ ሁኔታው ያስገደዳቸው ናቸው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ነቅተውና ተደራጅተው ለዲሞክራሲ፣ ለብሔራዊ ነፃነትና ለብሔረሰብ እኩልነት ሲታገሉ የቆዩና ጊ.ወ.መ. ከሚያካሂደው የእስራት፣ የግድያና የክትትል ዘመቻ ለማምለጥና ትግላቸውን በሚያመች ቦታ ለመቀጠል የተሰደዱ ተራማጆች፣ ዲሞክራቶችና አገር ወዳዶች ናቸው፡፡

የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽን አስታትስቲክ እንደሚያመለክተው ከሆነ በጎረቤት አገሮች የሚገኙት የኢት. ፖለቲካ ስደተኞች ቁጥር እንደሚከተለው ነው፡፡ በሱዳን ከ200ሺ በላይ የሚሆኑ ስደተኞች ይገኛሉ፡፡ አብዛኛዎቹ ከደቡብ ኢትዮጵያና ከኤርትራ በጦርነቱ ምክንያት የተሰደዱ አርሶአደሮች፣ መምህራን ወጣቶች የቢሮ ሠራተኞችና ወታደሮች ሲሆኑ የሚኖሩትም በመላ ሱዳን ተበታትነው ነው፡፡

በኬንያ በናይሮቢ ብቻ 6ሺ ስደተኞች ይገኛሉ፡፡ አብዛኞቹ ምሁራንና ወጣቶች ናቸው፡፡



በጅቡቲ ከሚገኙት የፖለቲካ ስደተኞች 12ሺ የሚሆኑት ኢትዮጵያውያን ናቸው፡፡ አብዛኛዎቹ ከአዲስ አበባ የመጡ ምሁራንና ወጣቶች ናቸው፡፡

በሶማሊያ 500ሺ ማለትም ግማሽ ሚሊዮን የሚሆኑ የኢት. ስደተኞች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ 145ሺ የሚሆኑት በተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች መረጃ ካምፕ ውስጥ እንደ ከብት ታጉረው ይኖራሉ፡፡ በሶማሊያ ከሚገኙት ስደተኞች አብዛኛዎቹ በኦጋዴን ጦርነትና በነፍጠኛ ጭፍን ጭፍጨፋ በደረሰባቸው ጥቃት የተነሳ የተሰደዱ ታጋዮችና አርሶአደሮች ናቸው፡፡

በአውሮፓና በአሜሪካም በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውን ስደተኞች አሉ፡፡

በዚህ መንገድ ቤተሰቦቻቸውንና ንብረታቸውን፣ ሥራቸውንና አገራቸውን እየለቀቁ በባእድ አገር ተሰደው የተንገላታ ኑሮ የሚኖሩ ጉልበታቸውንና እውቀታቸውን በከንቱ የሚያባክኑ ለአገራቸው ብዙ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ ምሁራንና ባለሙያዎች ቁጥር እጅግ ከፍ ያለ ነው፡፡ ከበጎ አድራጊ ድርጅቶችና አገሮች እንደምጽዋት የሚጣልላቸውን የእለት ዳቦ እየተጠባበቁ በለማኝነት ደረጃ ውርደትን ተከናንበው፣ አንገታቸውን ደፍተው ከባህላቸው ተለይተው በአገር ፍቅርና በዘመድ ናፍቆት እየተንገበገቡ መኖሩ በአብዛኞቹ ላይ የመንፈስ ጅና የሞራል ውድቀት አስከትሎባቸዋል፡፡ ከዚህም ሌላ በብዙ ቦታዎች ያሉት ስደተኞች በእርዛት፣ በመጠለያ እጦት፣ በረሃብና በበሽታ ይሰቃያሉ፡፡

ማህበራችን በውጭ አገር በስደትም ሆነ በትምህርት ጉዳይም በሥራ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ደህንነት የሚያስብ የሚቆረቆርና የሚከታተል ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በየአገሩ በተለይም በጎረቤት አገሮች በስደተኝነት የሚኖሩት ኢትዮጵያውያን ሁኔታ ከላይ እንደጠቀስነው እጅግ አስከፊና አሳዛኝ ነው፡፡ ስለሆነም ማህበራችን፣

1. ኢትዮጵያውያን ውድ አገራቸውን እየለቀቁ እንደመንጋ እንዲፈልሱና "አገር-አልባ"ነው በስደተኝነት ደረጃ እንዲማቀቁ ያስገደዳቸውን የደርጉን ፀረ-ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ ያወግዛል፡፡

2. ከእለት እለት እየጨመረ የሚሄደውን የስደተኞች ቁጥር ለመቀነስ ጊ.ወ.መ. በተራማጆች በዲሞክራቶች፣ በአገር ወዳዶችና ከጭቁን ብሔረሰቦች በመጡ ታጋዮች ላይ የሚያካሂደውን የግድያ፣ የእስራትና የክትትል እርምጃ እንዲያቆም ይጠይቃል፣

3. ስደተኞቹ ወደሚወዷት አገራቸው ተመልሰው የመገደልና የመታሰር ፍራቻ ሳያድርባቸው በኢትዮጵያ አብዮት ሂደትና ህብረተሰብ ግንባታ ውስጥ ተገቢውን አስተዋጽኦ እያደረጉ ሊኖሩ የሚችሉበት ሁኔታ እንዲፈጠር ይታገላል፡፡

4. ለእነዚህ በሚሊዮን ለሚቆጠሩት ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ስደተኞች አስከፊ በሆነ ሁኔታ ውስጥ እንዲኖሩ በመገደዳቸው የተሰማውን ሀዘን እየገለፀ በሚኖሩባቸው ቦታዎች ሁሉ ደህንነታቸውን፣ መብታቸውንና ባህላቸውን ለማስጠበቅ ከጎናቸው በመቆም ይታገላል፡፡

16. <u>በምሥራቅ አውሮፓ በማህበራችን አባላት፣ አገር ወዳድና ዴሞክራቶች ላይ ስለ ሚደርሰው ተፅዕኖ</u>

የደርግ/በደዱ ፀረ–ህዝብ መንግሥት በሬውይ ፋሽስቶ ኃይለሥላሴ ዘመን እንኳን ባልታየ አሰበአዊ ድርጊት ድርጅታችንን ለማዳከምና በሰው ለማጥፋት በጠነሰሰው ከንቱ ሴራ ድርጅታችንን ከየአቅጣጫው ለማጥቃት በመሯሯጥ ላይ ነው:: በኢትዮጵያ ውስጥ በየጋዜጣውና በየሬድዮው የፈጠራ ወሬዎች ከማሰራጨት አልፎ ፀረ–ህዝብ ሴራውን እስከ አውሮፓ ድረስ አስፋፍቶ ይገኛል::

የማህበራችን አባላት ፓስፖርታቸው ይነጠቃል:: ለዚሁ የሚያስፈልጓቸው ወረቀቶች ይነፈጋቸዋል:: ለእናት አገራቸው በሔራዊ ነፃነት በታገሉ ዜግነታቸው ተፍቶ በስደት እንዲገላቱ ተደርገዋል::

በተለይም በምሥራቅ አውሮፓና በሶቭየት ህብረት ያሉ የማህበራችን አባላት በቁም እስር ላይ ይገኛሉ:: ካሉበት እየተነሱ ወደ አገር ቤት በመላክና ለፀረ–ህዝቡ ደርግ/በደዱ የጥይት ራት የሆኑና ለወደፊቱም በዚህ አደጋ ላይ ያሉ ቁጥራቸው የማይናቅ አባሎቻችን አሉ:: የሃንጋሪ መንግሥት በዚህ በኩል ከደርግ/በደዱ ጋር እጅግ አስጊ ውል ተፈራርሟል:: በዚህ ውል መሠረት ኢትዮጵያውያን ከሃንጋሪ እንዲወጡና ትምህርታቸውን ሳጨርሱ ዲፕሎማቸውን ሀገር ቤት ሄደው እንዲቀበሉ ተደርጓል:: ይህ ጓዶቹን ወደ ሞት ጉድጓድ መወርወር እንደሆነ ግልፅ ነው::

ከዚህ በመነሳት 19ኛው ጠቅላላ ጉባዔ በአንዳንድ የምሥራቅ አገሮች መንግሥታት ከፀረ–ህዝቡ ደርግ ጋር በማበር በማህበራችን አባሎችና በሌሎች አገር ወዳድና ዴሞክራቶች ላይ የከፈቱትን ፀረ–አብዮት ዘመቻ ያወግዛል::

ይህ ዘመቻ የማህበራችንን አባላት ቅንጣት እንደማያንበረክክ እያረጋገጠ ዴሞክራትና ሰብዓዊ ድርጅቶች ከጎኑ ተሰልፈው፣

ሀ. በአገር ወዳድ፣ በዴሞክራትና በተራማጅ ኢትዮጵያውያን ላይ በምሥራቅ አውሮፓ የሚደረገው ተጽእኖ በአስቸኳይ እንዲቆም እንዲጠይቁ፤

ለ. በደርግና ባንዳንድ የምሥራቅ አውሮፓ መንግሥታት መካከል በተፈረመው ውል ምክንያት ችግር ለሚደርስባቸው አገር ወዳድ ዴሞክራትና ተራማጅ ኢትዮጵያውያን ማንኛውንም ዕርዳታ እንዲያደርጉ፣ጥሪውን ያስተላልፋል::

ሐ. በአኢተማ የሥ/አ/ኮ ጉዳዩን እየተከታተለ ለማንኛውም ለሚነሳው ችግር ሁሉ አስፈላጊውን መፍትሄ እየቀየሰ፣ በሥራ ላይ እንዲያውል 19ኛው ጠ/ጉባዔ ያሳስባል:: ......................................

THE ETHIOPIAN STUDENTS' UNION
IN EUROPE

## በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

ለብሄራዊ ዴሞክራቲክ አብዮት

ለብሄራዊ ነፃነትና ክብር

ለአገር ወዳጆችና ለዴሞክራቶች ህብረት

ለሰፊው ሕዝብ ዴሞክራሲ

ለብሄረሰቦች እኩልነት

ለሴቶች የእኩልነት መብት

---

ሃቀኛ ተራማጆች ፣ ወዛደሮች ፣ አርሶ
አደሮች ፣ አገር ወዳጆች ፣ ዴሞክራቶች
የጭቁን ብሄረሰቦች ታጋዮች ፣ ምሁሮች
ባለሞያዎች ፣ ወጣቶች ፣ ሴቶች ፣
ተራማጅ መለዮ ለባሾች ፣...ሕዝባዊት
ኢትዮጵያን ለመመስረት ተባበሩ ፡፡